እንደደረሱ በሕግ ሰም ቁሙ ፤ በዕድር ሰም ቁሙ ፤ እያሉ ያውጠጡ ጀመር ።

እንዲህ እያሉ ወደሰዎቹ ሲጠጉ መጀመሪያ አግራቸውን ያደናቀፈው ዶን ኪሾት ነበር ። እሱም ከተሰበረው የአልጋ እንጨት ላይ ወድቆ ሕሊናውን እንደሳተ አፉን ወደላይ እንዳንጋጠጠ ተዘርግቶ ስለነበረ ዝቅ ብሰው እጃቸውን ሰደው በዳበሳ እየተመ ተሙ እሪዙን ጨምድደው ከያዙ በኋላ ጩኸታቸውን ሳያቋ ርጡ « የሕግ ያለህ ድረሱ ሰው ተላለቀ » እያሉ እርዳታ ይጠ ይቁ ጀመር ።

ዳሩ ግን የተያዘው እሥረኛ ጥቂት እንኳ የማይንቀሳቀስ በመሆኑ የሞተ ስለመሰላቸው እና በውስጡም የሚገኙት ሰዎች ሁሉ የሱ ገዳዮች ስላደረጓቸው በዚህ ጥርጣሬ ድምጻቸውን ከቅድመ ይበልጥ አጉልተው አሰታቸውን አስተጋቡ ።

«የሆቴሉ በር ይዘጋ ! ከዚህ ቆጥ ላይ አንድ ሰው ተገድ ሏልና ግንም ሰው ከዚህ እንዳይወጣ» ብለው አሰጠነቀቁ ። በዚህ ማስጠንቀቂያ ጩኸት ተሞጊዎቹ ስለተደናገጡ ልክ ድም ጹን እንደሰሙ ወዲያው ሁሉም መሣታታቸውን አቋርጠው ፀጥ አሉ ። ሆቴለኛውም ሹልክ ብሎ ወደ መኝታ ክፍሉ ሄደ ። ነጋዴውም ወደ መደብሩ ተመለሰ ። ገረዷም ወደ ጓዳዋ ገባች። እነዚያ ሁለቱ መከረኞች ዶን ኪሾትና ሳንቾ ግን ሌላ መሄጃ ስለሌላቸው ከወደቁበትም ለመነሳት ስለማይችሉ እዚያው እወደ ቁበት ቦታ ብቻቸውን ቀሩ ። የጮበዝ አሊቃውም እስካሁን ጨብጠውት የነበረውን የዶን ኪሾትን ሬዝ ለቀቁለትና መብ ራት ፈልገው ወንጀለኛውን መርምረው ለማሰር ወጡ ። ዳሩ ግን ሆቴለኛው ወደ መኝታ ክፍሉ በተመለሰ ጊዜ በሆቴሉ መግቢያ በር ሲበራ የነበረውን ፋናስ ሆነ ብሎ አጥፍቶት ስለነበረ መብራት ለማግኘት አልቻሉም ። ስለዚህ ወደ ወጥቤቱ ምድጃ ሄደው እሳት ለማንደድ እየተንጐዳጐዱ ብዙ ጊዜ ከፊ ጀባቸው በኋላ በመጨረሻው እንዲት ኩራዝ ለማያያዝ ቻሉ ።

ምዕራፍ 17

ቆፍጣናው ዶን ኪሾት ለገዛ ጉዳቱ የመስፍን ግንብ ብሎ በሰየመው ሆቴል ውስጥ ከጋሻ ጃግሬው ከሳንቾ ፓንቻ ጋር የተቀበሉት ስፍር ቁጥር የሌለው እግርና ፍዳ መተረኩ ይቀጥላል ።

እስከዚያው ድረስ ዶን ኪሾት ነፍስ ዘርቶ ፡ ሰውነቱን ካወቀ በኋላ በመጀመሪያው ቀን « በሽመል ሸለቆ » ላይ ተደብድቦ ወድቆ በነበረበት ጊዜ ጋሻ ጃግሬው በጠራበት በዚያው ዓይ ነት ቀለስተኛ ድምጽ እንዲህ እያለ ይጠራው ጀመር ።

«ወዳጄ ሳንቾ ተኝተሃል ? ተኝተሃል ፤ የኔ ወዳጅ ሳንቾ

«እንደምን አድርገህ ነው ተኛ የሚሉኝ ! አምላክ ሞቴን ባቀረበውና ሊመሆኑ የትኛው ጨናቄ ነው የሚያሰተኙኝ እሰ ሳንቾ እንደተበሳጨና እንደበገነ በክፋት የተበከሉና የተሰበሰቡ ተንኮለኞች ሁሉ ዛሬ ሌሊት ተሰብስበው በላዩ ላይ ሲጨና ሩብኝ እየሰማኋቸው ምኑን ተኛሁት»

..... « እውን እንዳልከው ዛሬ ሌሊት የደረሰብን ሁኔታ በጂ ያብሎስ እቅድ የተመራ ለመሆኑ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ መሆን ትችላለህ» ሲል መልሰለት ዶን ኪሾት » .... ምክንያቱም ፡ ወይም እኔ ነጉላ ሆኜ ይሆናል ፡ ወይም ደግሞ ይህ ግንብ ያለጥርጥር በተበብ ኃይል የተወረረ መሆን አለበት ። የሆነው ሆኖ በተ ለይ አውን ልነግርህ ያሰብኩትን ምስጢር እኔ እስከሞትልህ ድረስ ለማንም ቢሆን እንዳታወጣው እስቀድመህ እንድትም ልልኝ እፈልጋለው » አለው ።

«በደስታ እምልልዎታለሁ» ሲል መለሰ ሳንቾ ፡

Pdf by Meysor Bro

« የመሐላ ቃልህን እንድትሰጠኝ የፈለግሁበት ምክንያት ሲል ማሰረዳቱን ቀጠለ ዶን ኪሾት በምስጢር የተደረገ ነገር ሁሉ አንድ ቀን ይፋ ወጥቶ ወሬው ተዛምቶ በመሰማቱ የማንም ክብር እንዲነካና የማንም ስም እንዲጠፋ ስለማልፈ ቅድና ደስም ስለማይሰኝ ብቻ ነው » አለው ።

እኔም ደጋግሜ የማረጋግጥልዎ « ሲል መለሰ ሳንቾ » እር ስዎ ከሞቱልኝ በኋላ ነው ። እንጂ በሕይወት እያሉ ለማንም በሆን ላለወራ መሐላው ይድረስብኝ ። ዳሩ ግን የልዩ አጋጣሚ ኃይል ሆኖ ይህን ምስጢር ነገ ዋዋት ለማውራት እንዲያበቃኝ እጸልያለሁ አለው ።

« እንዴት በል ሳንቾ ሲል ተገረመ ዶን ኪሾት .... ለመሆኑ እስከዚህ ድረስ በድያለሁ እንዴ እንዲህ በቅርብ ሞቴን ለማ የት የቸኮልከው » ....

.... «የለም ይህን ማለቴስ አይደለም ። ሲል መለሰ ሳንቾ» ዳሩ ግን እንኳንስ የሌላ ሰው ምስጢር ለመደበቅ መቻሌ ይቅ ርና የራሴንም ምስጢር ቢሆን ለረዥም ጊዜ ደብቄ ማቆየት በፍጹም ስለማያሰችለኝ መሐላየን ለመጠበቅ ስል ብዙ ጊዜ በሆዴ ውስጥ ቀብሬ በማቆየቴ ምክንያት ሥራይ እንዳይሆንብኝና ምስ ጢሩም ተበላሽቶ እንዲቀር ባለመፈለጌ ብቻ ነው ።

« በዚህ ባልከውም ሆነ ወይም በሌላ በተሠወረ ምክን ያት » ሲል ዶን ኪሾት አስተያየቱን ገለጠ ። አንተ ከምትም ልልኝ መሐላ ይልቅ ስለኔ ባለህ ፍቅርና በጐ አስተያየት ላይ የበለጠ እምነት ስለማደርግ መጠራጠሬን ትቼ ምስጢሩን ልገ ልጥልህ እፈቅዳለሁ ። ይኸውም ዛሬ ሌሊት በሕይወቴ ውስጥ ደርሶብኝ የማያውቅ እጅግ የሚያስደንቅ ጉድ የሆነ አጋጣሚ ደርሶብኛል ብልህ ምናልባት አታምነኝ ይሆናል ። ነገሩን ባጭር ቃል ልንገርህ ከጥቂት ሰዓት በፊት የመስፍኑ ልጅ እኔ ዘንድ ለማደር ፍቅር አጥወልውሏት መጥታ ነበር ። ይህችም ቤት በጠቅላላው ሁኔታዋ እንዳየኋት በዚህች ምድር ላይ ከተፈ ጠሩት ቤቶች ሁሉ በቁንጅናዋና በደም ግባትዋ ፣ በትሕትና ጠባይዋ ወደር የማይገኝላት ምልኢተ ኩሉ የሆነች ወይዘሮ

ልንገርህ

ናት ። ወዳጄ ሳንቾ ምን ብዬ ልንገርህ የሰውነቷ ፀጋና ልስላሴ የንግግሯ ለዛና ጣዕም ፣ የልቧ ኃይልና ሞገስ ፣ ሌሎችም እጅግ የበዙት የሥነ ፍጥረቷ ሽልማቶችና ጌጦች የዚህን ዓለም ተድ ላና ክብር የሚያስንቁና ፍጹም ታማኝነትን የሚያስከዱ ናቸው ። ስለዚህ ለእመቤቴ ለተበዘይቱ ዱልቼኔያ ያለኝን የጠበቀ ታማ ኝነቴን ሳላወላውል ጠብቄ ለመዝለቅ ስል የዚህችን ወይዘሮ ሁኔታ በዝምታ አደበስብሼ ማለፍ ይገባኛል ። ሆኖም በተለይ ልንግርህ የምችለው እድሌ አሳክቶ ሰጥቶኝ በእጄ የጨበጥሁ ትን ታላቅ ሀብትና ንዋይ አይቶ የተመቀኘኝ ጠላት ቀንቶብኝ ይሆን ? ወይም ደግሞ ነገሩ ይበልጥ እርግጠኛ በመሆኑ ላም ንበት እንደምችለው ፣ ቅድሞ እንደተጨዋወትነው ይህ ግንብ በአስማት የተወረረ በመሆኑ ይሆን አላወቅሁም እንጂ ከዚች ውብ ብላቴና ጋር ፍቅራዊና መዓዛዊ የሆነ የምስጢር ፣ ጭውውት ይዘን ፣ ልባችን በጥልቅ ሰሜት ተመስጠ በወዲያኛው ዓለም ውስጥ በትፍስሕት ሕይወት አልፍኝ በምንገኝበት በአፍላው ጊዜ እኔ ሳላየውና ከወዴት እንደመጣ ሳላውቀው ባንድ በሰ ማይ ጠቀስ ጃዊግ ክንድ ላይ የተጣበቀ እጅ ተሠንዝሮ ይህ ነው በማይባል አመታት መንጋጋዬን አራግፎ ስለጣለኝ ! ይኸውልህ ? እስካሁን ድረስ ባፌ ሙሉ ደም ተጉንጭቼ እገኛለሁ .... »

ከዚያም አከታትሎ ቁጥሩን በማላውቀው እርግጫና ጡጫ እንደቅሪላ ካለፋኝ በኋላ ከአልጋዬ ላይ ገልብጦ እመፊት ላይ ጥሎኝ ጠፋ ። በዚህ የተነሣ ያንን የምታውቀውን ትናንት በሮ ንዜናንቱ ከልፍልፍነት ምክንያት እነዚያ ጉረደግዎች ደብ ድበው ካቆሰሉን ይበልጥ ይህ የዛሬው ደግሞ የባሰ ሰውነቴን አሰያይቶታል ። ይህን ሁኔታ መሠረት በማድረግ ይህች የውበት አክሊል የሆነችው ወይዘሮ በምትሀት ኃይል ተሰውሮ በዚህ ግንብ የሚገኝ አንድ አረብ የሚጠብቃትና የሚከላከልላት መሆ ኑንና ለኔም ያልተፈቀደልኝ መሆኗን ለማረጋገጥ ችያለሁ ።

« በውነቱ ለርስም ብቻ ሳይሆን ለኔም ያልተፈቀደችልኝ መሆኗን ለማረጋገጥ ችያለሁ » አለ ሳንቾ ይህንንም የምለው እኔን የወገሩኝ ዓረቦች ብዛታቸው ያለጥርጥር ከአራት መቶ ቢበ ልጡ እንጂ ስለማያንሱ የዛሬውን ሌሊት እደጋ ከያንዳንዱ ሽመል

ጋር ሳወጣጣነው-የምንነሳው ሽመል ብለው። እንደ ስኳር የሚቆጠር ነው። መጀመሪያ ይጠራሉ ! አንጋሜ ይጠራሉ ! ከዚህ ይጀምራል ! ከዚህ የዓለም አቀፍ ሰዎች ሁሉ ይህን ከታች ይጀምራሉ። ከዚህ ይጀምራሉ። ከዚህ ይጀምራሉ። ከዚህ

« ታልክስ እኔም ትክሻዬን ቀርታል » አለ ዶን ኪሾት «ቢሆንም ይህ ኮቴውን የምንሰማው በምትሐት የተዳኘው ዓረብ ነው ብለን ለማረጋገጥ በቂ ማስረጃ ሊሆነን አይችልም » አለው።

ይህን በሚባባሉበት ጊዜ የጐበዝ አለቃው እየተጠጓቸው መጡ ። ዳሩ ግን ሰዎቹ በረጋ መንፈስ እርስ በእርሳቸው ሲነ ጋገሩ በመስማታቸው የሚሉት ቅጡ ጠፍቶአቸው ዲዳ ሆነው ቀሩ ። ባንድ በኩል ደግሞ ዶን ኪሾት እስካሁንም ድረስ ከወ ደቀበት ሥፍራ ለመንቀሳቀስ ሳይችል በቁስል ማሰሪያው ሻሽ እንደተተበተበ አቶን ሽቅብ እንጋጥሞ በዚያው በቅድሙ ሁኔታ ተንጋሎ ይገኝ ነበርና የጐበዝ አለቃው አጠገቡ ቀርበው እን ዲህ ሲሉ ጠየቁት ።

«ስማህ ወይ ወዳጄ ! አንተን ነው የምጠይቀው ? እረ ቅድም ምን ሆነህ ነበር? » ።

« እኔ አንተን ብሆን ኖሮ» ሲል መለሰ ዶን ኪሾት በተ ሻለ የትሕትና አነጋገር እጠይቅህ ነበር እንጂ እንዲህ እንዳንተ አልቆናጠርም ነበር ። አንተ ጅል እረኛዋ እረ ለመሆኑ እዚህ ሥፍራ ዙዋሪ ፈረሰኛችን እንዲህ ባለው አነጋገር ማመናጨቅ የተለመደ ነውን ? አለው ።

« የጐበዝ አለቃው ይህ ሁኔታው እጅግ የኰሰሰ ሰው በዚህ አኳኋን ሲያዋርዳቸው በሰሙት ጊዜ ትዕግሥታቸውን ስለጨ ረሱ በእጃቸው የያዙትን ጋዝ የተሞላች ኩራዝ አነሱና ጭን ቅላቱ ላይ ወርውረው ቢመቱት ለጥቂት ሳይፈነክቱት ቀሩ ። ከዚያም በኋላ በጨለማ ውስጥ ትተዋቸው በፍጥነት ወጥተው ሄዱ ።

ጌታዬ ሆይ ! ሲል ተጣራ ሳንቾ ይህ ስንጠራጠረው የነ በረው ነገር ያው በምትሐት የተሠወረው ዓረብ መሆኑ እነሆ ተረጋ ገጠ ። በኔ አስተያየት ይህ አዋቂ ዓረብ ገንዘብ አፍሶ መስጠ ቱን ለሌሎቹ ፥ ጡጫንና በጭንቅላት ላይ ኩራዝ ውርወራን ለኛ አዘጋጅቶ የመጣ ይመስለኛል" ። አለው ።

«እዚህ ላይ እውነት አልህ ለማለት እደፍራለሁ "፤ ሲል መለሰ ዶን ኪሾት ። ዳሩ ግን በምትሐት ጉዳይ ላይ ይህን ያህል መናደድና መደነቅ ከንቱ ነገር ነው ። ምክንያቱም ሁሉም የሰ መመን ትርኢቶች ስለሆኑ ለመበቀል ብንፈልግም እንኳ ጉም እንደመዝገንና ከጥላ ጋር እንደ መጋጠም ያህል የሚቆጠር መሆ ኑን ማወቅ አለብህ ። ስለዚህ ሳንቾ ሆይ ! የምትችል እንደሆነ ተነስተህ የግንቡ ገገር ዘንድ ሂድና ጥቂት ዘይት ፥ የወይን ጠጅና ጨው ፥ ሰናፍጭ ጭምር ለምነህ አምጣልኝ ። ይህን ካገኘሁ በኋላ ያንን ተአምራዊ አብነት እቀምማለሁ ። ከትናትናው ይልቅ ዛሬ ይህ ቀላዋጭ ሥራ ፈት የመታኝ በትር መንጋጋዬንና ጭን ቅላቴን አቁስሎ ብዙም ደም ስለአፈሰሰብኝ የአብነቱ አስፈ ላጊነት ይበልጥ የሚረዳኝ ባሁኑ ሰዓት ነው " አለው ።

ሳንቾም የታፋው ቁስልና የአጥንቱ ስብራት እየቆጠቆጠው ተንገዳግዶ ተነሳና በጨለማ እየተደናበረ ሆቴለኛው ወደተኛ በት ክፍል አመራ ። ዳሩ ግን የጐበዝ አለቃው ቅድም ኩራ ዙን ወርውረው የመቱት ሰውዬ ምን ዓይነት አደጋ ደርሶበት እንደሆነ ለማወቅ ሲሉ እበሩ ሥር ተለጥፈው ንግግራቸውን ያዳምጡ ስለነበረ ሳንቾ በሩን እንደወጣ ወዲያውኑ ፊት ለፊት ግጭት ስለተገናኙ ደነገጠና እንዲህ ሲል ጠየቃቸው ።

«ጌታዬ ሆይ ! ግን እንደሆኑ ሰይቼ ባለማወቄ ይቅርታ ያድርጉልኝና መልካም ፈቃድዎ ሆኖ ትንሽ ሰናፍጭና ፤ ዘይት ፤ ጨው ፤ የወይን ጠጅ ፤ ቆንጥረው እንዲሰጡኝ እለምንዎታለሁ ። ይህንንም የፈለግሁበት ምክንያት በምድር ላይ ከነበሩት ከም ርጥ ዙዋሪ ፈረሰኛ አንዱ የሆነው ጌታዬ ዶን ኪሾት በምት ሐት የተሠወረ ዓረብ እዚህ ሆቴል ውስጥ አግኙትና በብርቱ አቁስሎት እዚያ እቆጡ ላይ ወድቆ የሚገኝ ስለሆነ እሱን ለማከሚያ የሚሆን አብነት ለመቀመም ነው " አለው ።

የጐበዝ አለቃውም ይህን አነጋገር በሰሙ ጊዜ እስካሁን ድረስ በከንቱ ሲዳረቁ የቆዩት ከእበዱ ሰዎች ጋር መሆኑን አሰቡ ። መቸም ጊዜው ወደ መንጋቱ ተቃርቦ ነበርና የሆቴሉን በር ከፍተው ሆቴለኛውን ከጠሩለት በኋላ ይህ የቀሀ ሰው የሚ

ፈልገውን ነገሩለት ። ሦቴለኛውም የተጠየቀውን ነገር ለሳንቾ ስለሰጠ ተቀብሎ ለዶን ኪሾት ወሰደለት ።

ያም ከወደቀበት ተነስቶ በሁለት እጁ እራሱን ይዞ ተቀምጦ በኩራዙ የተመታውን ግንባር እየዳበሰ መቺውን ይራገም ነበር ። ይህም ኩራዝ ሁሰት ቦታ ላይ ቀንድ ሊያበቅል ያጐነቆለ ወይፈን አስመስሎ ግንባሩን ከማሳበጡ በስተቀር በጣም አላቆሰለውም ነበር ፤ እሱ ግን ደሙ የፈሰሰ የመሰለው በፊቱ ላይ የሚን ቆረቆረውን ላብ ዓይቶ ነው እንጂ ደም አልነበረም ። በመጨረሻም የተላከለትን መመጠኛ ተረክቦ በግምት እየለካ ቀይጦ ካማሰለው በኋላ በትክክለኛው መዋሃድ ላይ የደረሰ እስኪመስለው ድረስ እሻት ላይ ጥዶ አፈሳው ። ቀጥሎም የሚገሰብጥበት አንድ ብልቃጥ እንዲሰጠው ጠየቀ ። ዳሩ ግን በሦቴሉ ውስጥ ብልቃጥ በፍጹም የሌለ ስለሆነ ሦቴለኛው አንድ ባዶ የዘይት ጣሳ ፈልጐ በቾ ሮታው ሽለመውና በዚያ ውስጥ አጋባው ። ከዚህ በኋላ በተለ መደው አባባል እየደገመ ሥርዓቱ ቅመማውን ፈጸመ ።

በዚህም ሥርዓተ ቅመማ ላይ ሳንቾና ሦቴለኛው የጐበዝ አለ ቃውም ጭምር ታዛቢዎች ሆነው ይገኙ ነበር ። ነጋዴው ግን ማለዳ ተነስቶ በቅሎዎቹን ለመጐብኘት መጥቶ ስለነበር በመ ከከላቸው አልተገኘም ።

ዶን ኪሾትም ለዚህ ለተአምራዊ አብነት የሰጠውን የፈ ዋሽነት ችሎታ ለማረጋገጥ ሲል እራሱን ለመፈተን ሲል በጣም ቸኩሎ ስለነበረ ከጣሳው ተርፎ ባፈላበት ድስት ውስጥ ዘቅጦ የቀረውን ጨልጦ ጠጣው ። ይህም ሁለት መጸዚያ ያህል ቢመ ጣው ነው ። መጠጡ ከኮርሮው ወርዶ ገና ወደጨጓራው ከመ ድረሱ ወዲያውኑ ሽቅብ ገንፍሎ በጋይል ማስታወክ ስለጀመ ረው ትውከቱ ሳያቋርጥ ቀጥሎ ከጨጓራው ውስጥ ያለ የሱ ለው ሁሉ ተሟጥጦ እስኪያልቅ ድረስ እየለበቀ አስወጣው የትው ከቱ ኃይል እስጨንቆት ሰውነቱ በመናወጡ ምክንያት የላቡ መጎ ቅርቅር ስለተሰማው በብርድልብሱ ሸፍፍነው ብቻውን እንዲተ ውት ሰምቾን ለመናቸው ። እነዚያም ይህንኑ ፈቃዱን በመፈጸም ልብሱን ደራርበው በደንብ ከሸፋፈኑት በኋላ ከባድ እንቅልፍ

ወሰዶት ተኛ ። ከሶስት ሰዓት ይበልጥ ተኝቶ ከነቃ በኋላ እውነትም እሱ እንዳለው ሆዱን በጣም ቀለል ብሎት ቁስሉም በጣም ተሽሎት በጐነቱ ስለተሰማው ጨርሶ የዳነ መሆኑንና « የፌድሮብራዚዩ » እውነተኛውን ዕፀ ፈውስ አቀማመም ምስጢር አግኝቶ አብነቱ ያለ ስህተት የተዋጣለት መሆኑን ለማመን በቃ ። በዚህ መድኃኒት በመተማመን ከእንግዲህ ወዲያ ያላንዳች ፍርሃትና ሥጋት የቱን ያህል አደገኛም ቢሆን በማናቸውም ዓይነት አምባጓሮና ጥል ፣ ውጊያና ፣ ጦርነት ውስጥ ገብቶ ለመራኮት የሚችል መሆኑን አረጋገጠ ።

ጌታው ሳንቾ ፖንቻ ይህን ሁኔታ በጥንቃቄ ሲመለከት ነበርና ገዢው በጥቂት ሰዓት ውስጥ መፈወሱን በማየቱ የመድኃኒቱን ተአምራዊነት እጅግ አድርጐ እያደነቀ እሱም በድስቱ ውስጥ የተረፈውን ጭላጭ ለመጠጣት እንዲፈቅድለት ጌታውን ለመ ነው። ዶን ኪሾትም ወስዶ እንዲጋበዝ ስለፈቀደለት ሳንቾ ድስ ቱን በሁለት እጁ አንስቶ በፍጹም እምነትና በሙሉ ፈቃደኛነት እያንገራገጨ በመጠጣት ከጌታው ጥቂት አነስ የሚል መጠን ወደከርሱ ሰደደ ። ዳሩ ግን ያልታደለው ሳንቾ ጨንጓራው እንደ ዶን ኪሾት በጣም የተለሳለሰ አልነበረምና ከማስታወኩ በፊት ቋቋና ጉግጫ እየተፈታተነው ፣ ቀዝቃዛ ላብ እያላበው ነፍሱ በጭንቅና በጣር መካከል ተጣበበች ። በዚያን ሰዓት ያደረገው ትግልና መንቀራጠጥ ሰውነቱን ክፉኛ ስላናወጠው ወደመጨ ረሻው የፍጻሜ ሰዓት ላይ የደረሰ መሆኑን አመነ ። እስከዚህም ጭረስ መስቃየቱ ተስፋ በሚያስቆርጥ ማክተሚያ ላይ ያደ ርሰው ስለመሰለው የጠጣውን መድኃኒትና እንዲጠጣም የፈቀ ደለትን ነፍስ ገዳይ ይራገም ጀመር ። ዶን ኪሾትም ጋሻ ጃግሬው የሚገኝበትን የጭንቅ ሁኔታ በተመለከተ ጊዜ እንዲህ ሲል አስ ረዳው ።

« ሳንቾ ሆይ ! እኔ እንደማምነው ይህን ሁሉ ጭንቀት ያመ ጣብህ አንተ የተካንህ ፈረሰኛ ባለመሆንህ ይመስለኛል ። ምክ ንያቱም ይህ መድኃኒት ፈረሰኛ ያልሆኑትን ሰዎች የሚፀናወ ታቸው በመሆኑ ሳይሆን አይቀርም አለው ።

«በኔና በዘር ማንዘሮቼ ላይ መዓትና መቅሰፍት ይውረድ ብን » አለ ሳንቾ እንደባባ ''እርስዎ ይህንን እያወቁ ለምን ስጠ ጣው እያዩ ዝም አሉኝ ? ሆነ ብለው ያደረጉት ተንኮል ቢሆን አይደለምን ? እያለ ያቃስት ጀመር ።

መጠጡ ሥራውን ሲሰራ ቆይቶ በሆዱ ውስጥ ተተኩሰና ቡሽ እንደተከፈተ ሻምፓኝ ስለገነፈለ አሣረኛው ጋሻ ጃግሬ በላ ይኛውና በታችኛው በር እያስፈተለከ መኝታው ላይ ዘፈዘፈው ለብሶት የነበረው የኬሻ ብርድ ልብስ በአጉል አኳኋን ተበ ክሎ ስለበሸቀጠ ለምንም የማይረባ ሆኖ ተጣለ ። በኃይል የመ ጨነቁ የመጠበቡ ብዛት መላው ሰውነቱ በሳብ ተዘፍቆ መተ ንፈስ ስለአቃተው እሱ የጭንቁ ባለቤት ብቻ ሳይሆን ዙሪያ ውን ከብበው የሚያዩት ሰዎች ሁሉ የማከተሚያው ሰዓት የተቃረበ መስሏቸው ተደናገጡ ። ይህም ብርቱ ጣር ሁለት ሰዓት ያህል ቆይቶ ጥቂት ፋታ ከሰጠው በኋላ ፊቱ አመድ መስሎ ተዳክሞ መቆም አቅቶት ተዝለፈለፈ እንጂ እንደጌታው ሕመም ተቃልሎለት ወዲያውኑ በጐ አልሆነም ነበር ።

ዶን ኪሾት ግን ከላይ እንደተባለው በጣም ተሸሎት ሰው ነቱ ስለነቃ አጋጣሚውን ለመፈለግ ወደዙረቱ ለመነሳት ተቻ ኮለ ። ምክንያቱም ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ አሁን ይህን ተአ ምራዊ መጠጥ ቀምሞ በመያዙ በልቡ ሙሉ እምነት ስለአ ሳደረ ከእንግዲህ ወዲያ እዚህ ስፍራ ተቀምጠ በችላ ባይነት የሚ ያሳልፈው ጊዜ ሁሉ የሱን እርዳታ ከሚጠባበቁት የተበደሉ ሰዎችና ከዓለሙም ላይ ሠርቆ እንደሚወስድ ያህል ስለቆጠ ረው ነው ። ይህ የችኩልነት መንፈሱ ትዕግሥት አሳጥቶ ስለ ጐተጐተው ተነስቶ ቸጥቁን ታጠቀና እሱው እራሱ ሮንዚናን ቴንና አህያይቱን ቁና ፤ የሳንቾንም ልብስ አልብሶ ፤ አህያው ላይ እንዲወጣ አግዞት እሱም እራሱ አፈረሱ ላይ ከወጣ በኋላ በሆቴሉ ባንዱ ማዕዘን ጥግ የተደገፈ አንድ አንካሴ መሣይ አይቶ ስለጦር ሊጠቀምበት ወስዶ ለጉዞው ተዘጋጀ ። በሆቴሉ ውስጥ የነበሩትም ከሃያ የሚበልጡ ሰዎች ተሰብስበው በአኳኋኑ እየ ተገረሙ አተኩረው ይመለከቱት ነበር ። የሆቴሉኛውም ልጅ ሁኔታው በጣም አስገርሟት ትመለከተው ነበር ።

እሱም በበኩሉ ዓይኑን ከሰ ላይ ሳይነቅል ትክ ብሎ እያየ አልፎ አልፎ ከታች ከሆዱ አዘቅት ፈንድቶ የወጣ የሚመስል ትን ፋሽ ይተነፍስ ነበር ። ሌሎች ሰዎች ይህን አተነፋፈሱን ሰም ተው የታፋው ሕመም የሚያስምጠው መስሏቸው ነበር ። በተ ለይም ይህን አተነፋፈሱን የሕመም ምክንያት መሆኑን የሚ ያረጋግጡ ሌሊቱ ቁስሉን ሲታከም ጉዳቱን በቅርብ ሆነው ያዩ ለት ሰዎች ናቸው ።

ሁለቱም ከብቶቻቸው ላይ ከወጡ በኋላ ዶን ኪሾት እበሩ ላይ ሲደርስ በረጋና በአክብሮት ድምጽ ሆቴለኛውን ጠርቶ እን ዲህ አለው ።

« ክቡር የግንቡ መስፍን ሆይ ! በዚህ በታላቁ ግንብዎ ውስጥ የተቀበልኩት መስተንግዶ እጅግ ከፍ ያለና የበዛ ስለሆነ እስከ እድሜ ልኬ ድረስ ውለታዎን የማውቅና አጋጣሚ ሲፈቅድ ልኝ እጥፍ አድርጌ ለመመለስ በጣም የሚያስገድደኝ ሆኖ አግ ኝቸዋለሁ ። ምናልባት ከዚህ ቀደም ያስቀየመዎት ወይም የበ ደለዎት ትእቢተኛ ሰው ኖሮ እሱን በመበቀል ይህን ውለታ ዎን ለመመለስ የምችል ብሆን ዋናው ተግባሬ ለዚሁ ጉዳይ የተመ ደበና ማናቸውንም ትእቢተኛ በመቅጣት ፥ የተበደሉትን ሰዎ ችና ጥቃት በመበቀል ፥ ደካማዎችን በመርዳት ላይ የተመሠ ረተ መሆኑን እንዲያውቁልኝ እወዳለሁ ። ስለዚህ ትዝ የሚል ዎት ጠላት ወይም ባላጋራ እንዳለ ትውስታዎን በርብረው ጨም ቀው ፈልጉና በኔ ላይ የሚጥሉትን ይህን የመሰለ ቂም ያሳደ ሩበት ሰው እንዳለ ባንድ ጥቅሻ አሳይተውኝ ዘወር ከማለት በስተቀር ሌላ ሃሳብ የለብዎትም ። እኔም የልብዎን አድርሼ ውለታዎን ከፍዬ ሙሉ በሙሉ ሳላስደስትዎት እንደማልቀር በተቀበልኩት የፈረሰኛነት ክህነት ቃል ገብቼልዎታለሁ» አለው።

ሆቴለኛው ንግግሩን በርጋታ ካዳመጠው በኋላ መልሱን ደግሞ እንዲህ ሲል በበለጠ እርጋታ ፈዝ መለሰለት ።

« ጌታው ፈረሰኛ ሆይ ! ክቡርነትዎ ማናቸውንም ዓይነት ጥቃት እንዲበቀሉልኝ አልፈለግም ። ምክንያቱም ያጠቃኝን ወይም ሊያጠቃኝ የፈለገውን ሁሉ እኔው እራሴ እንዳሰኘኝና እን

ዳስፈለገኝ አድርጌ መበቀሉን አውቅበታለሁ ። ስለዚህ ለተደ ረገልዎት መስተንግዶ ዋጋ ፥ ለመኝታና ለምግብ ፥ ለሁለቱ ከብ ቶች የገፈራና የገብስ ሂሳብ ፥ ከዚህም ሌላ ዛሬ ሌሊት በዚህ ሆቴል ውስጥ ላደረጉት ጉዳት የተገመተውን ካሣ ከከፈሉኝ ይበቃኛል ፤ በሌላው ነገር አላደክምዎትም» አለው ።

« እንዴት አባክዎ ይህ የሆቴል ቤት ኖሯል እንዴ?» ሲል ጠየቀ ዶን ኪሾት ።

«እንዴታ ፤ ያውም ከምርጦቹና ከጽዱዎቹ ሆቴሎች አንዱ ነዋ » ሲል ሆቴለኛው አረጋገጠለት ።

«ግሩም ነው!» አለ ዶን ኪሾት ለካስ እስካሁን ድረስ በተ ሳሳተ እምነት ላይ ኖሬአለሁ ። እኔ ምን ጊዜም የመስፍን ግንብ ያውም የማይከፋው ዓይነት መሆኑን አምኜ ነበር ። ሆኖም ግን ብነቱ ቀርቶ ሆቴል መሆኑ ከተረጋገጠ ዘንድ የሂሳቡን ደብ ተር በቀይ እርሳስ ከመሠረዝ በስተቀር ሌላ የሚያስቸግር ነገር የለም ምክንያቱም እስካሁን ድረስ የሆቴል ሂሣብ የከፈለ ፈረሰኛ መኖሩን በፈረሰኝነት ታሪክ ውስጥ ስላላነበብሁ በበኩሌ ሂሣብ በመክፈል ዘዋሪ ፈረሰኞች የደነገጉትን ደንብ ለማፍረስ ስለ ማልችል ነው ። ከጥንት ጀምሮ ሲተላለፍ የመጣው ልማድ እን ደሚያስረዳው እነሱ በዋሉበትና ባደሩበት ሆቴል ወይም የመስፍን ግንብ ከሚደረግላቸው ነጻ የክብር አቀባበል በስተቀር ገንዘብ ተጠ ይቀው አያውቁም ። እርስዎ እንደሚሉት ለሆቴልዎ ኪራይ እን ዲከፈልዎ የጠየቁት ሂሣብ ምናልባት ሊከፈልዎ የሚገባ ይሆን ይሆ ናል? ። ዳሩ ግን ዘዋሪ ፈረሰኞች በዚህ ቀንበር በሆነ ሥራ ተጠ ምደው አጋጣሚያቸውን ለመፈለግ በቀንና በሌሊት ፥ በበጋ እና በክረምት ፥ በእግርና በፈረስ ፥ በብርድና በሙቀት ፥ ለረ ሃብና ለውሃ ጥም ተጋልጠው ለሰማዩ ቴግብና ለምድሩ ሐሩር መከተው ላደረጉት ብርቱ ተጋድሎና ድካም ዋጋቸውና ውለ ታቸው ይሆን ዘንድ ማናቸውም ዓይነት አስደሳች አቀባበል እንዲደረግላቸው ነፃ መብትና ልዩ ድርጉ ስለተሰጣቸው ይህን በመላው ዓለም የታወቀውን ማኅበራዊ ግዴታ ለማጓደል መፈ ለግ በውነቱ አዙሮ አለማየት ነው ።

« ይህ ጉዳይ ሲል መለሰ ሆቴለኛው «በፍጹም እኔን የሚ መለከትና በኔ ላይ የሚፀና አይደለም ስለዚህ እኔ ጥቅሜን ከመ ጠበቅ በስተቀር ሌላ ታሪክና ልማድ አላውቅምና የፈረሰኞችን ጉረትና ወግ መዘብዘቡን ትተው ለብዙ ሳንዳረስ ማግኘት የሚ ገባኝን ገንዘቤን ይክፈሉኝ » አለው ።

«እርስዎ በውነቱ ገትጋታ ባላገርና ገብጋባ ቸርቻሪ ነዎት» ሲል በቁጣ ከመለሰለት በኋላ አንካሴውን አጓመደና ሮንዚናን ቴን ኩርኩሮ አሰነስቶ ማንም ሊያግደው ሳይችል ፤ ጋሻጃግሬ ውም ተከትሎት እንደሆነ ዞሮ ሳይመለከት ፤ እየጋለበ ከሆቴሉ ግቢ ወጥቶ ራቅ ብሎ ሄደ ።

ሆቴለኛው ሲጨታጨቅ ውሎ ሂሣቡን ሳይቀበል ፈረሰኛው ማምለጡን በተመለከተ ጊዜ ሳንቾ ፓንቻን ይዞ ለማስከፈል ተን ደርድሮ ሄደ ። ሳንቾ ግን ጌታው ለመክፈል ያልፈቀደውን እሱም ለመክፈል የማይፈቅድ መሆኑን አስታወቀ ። ምክንያቱም እሱም የዙዋሪ ፈረሰኛ ጋሻጃግሬ እንደመሆኑ መጠን ለጌታው የታወቀ ለት መብትና ማመካኛ ደንብ ለሱም የሚረጋለት መሆኑን መሠ ረት በማድረግ ነው ። በዚህ አነጋገር ሆቴለኛው በንዴት ስለ ሠፈ የሳንቾን ጢም ጨምድዶ ያዘና ገንዘቡን ያልከፈለው እን ደሆነ በአጉል አካሄን አንገላቶት የሚያስተፋው መሆኑን በዛቻ አስጠነቀቀው ።

«አዬ እንደሆንኩ» አለ ሳንቾ ብታንገላታኝም ብትገድለኝም ያፈቀደህን አድርገኝ እንጂ አንዲት ቤሳ እንኳ አልከፍልህም ። ምክንያቱም ጌታዬ የተቀበሉት የፈረሰኞች ደንብ የሚያዝዘው በልቶ መሸሽን ስለሆነ ይህ ጥንታዊና በጣም ጥሩ የሆነው የዙ ዋሪ ፈረሰኞች ልማድ እኔ ዘንድ ሲደርስ ተሽሮ ተረስቶና ወድቆ መቅረት አይገባውም ። እንዲያውም ይህን የመሰለውን ትክክለኛ መብትና ድርጉ እፍርሽ በመገኘቴ ወደፊት የሚተኩት የዙዋሪ ፈረሰኞች ጋሻጃግሬዎች ሁሉ በኔ እንዲያማርሩብኝና አጥንቴን ሲወቅሱት እንዲኖሩ አልፈቅድም» አለው ።

ያልታደለው ሳንቾ የኩስቡ መዋርነት በሆቴሉ ውስጥ ከሠፈሩት ሰዎች መካከል ከሴንቪያ የመጡ አራት የቡትቶ

ጨርቅ ደላላዎችና ሶስት የጐርደባ ተዘዋዋሪ ሸቃጮች ሁለት የሲቪሊያ ነጋዴዎች እንዲገኙ አዘዘበት ። እነዚህም ሰዎች ሁሉ ፈዘኞችና ሰካራሞች ደብረ በጥብጦች ስለሆኑ ባንድ ዓይነት የተንኮል መንፈስ ተገፋፍተው ሳንቾን ከበቡትና ከአህያው ላይ ዘርጥጠው አወረዱት ።

ከዚያም በኋላ ከመካከላቸው አንደኛው ወደ ሆቴሉ ሮጠና ከሆቴለኛው አልጋ ላይ አንዱን ብርድ ልብስ ገፎ አምጥቶ ሰጣቸው ፣ ሁሉም ሳንቾን ታግለው በብርድ ልብሱ ላይ ወረወሩት ። ቀጥለውም ቀና ብለው ወደላይ ቢመለከቱ የጣሪያው ቅርብነት ለተንኮል ሥራቸው ማከናወኛ የሚያመች ሆኖ ስላገኙት ሸክማቸውን ይዘው ከሰማይ በስተቀር ሌላ ጣሪያ በሌለበት መስክ ላይ አወጡት ። እንደገና ብርድልብሱን አንጥፈው ሳንቾን እመካከሉ ላይ ከአጋደሙት በኋላ አራቱም ሰዎች የብርድልብሱን አራት ማዕዘን ጫፍ ጨብጠው ይዘው የፈረደበትን ሳንቾ በመንሽ እንደሚወረወር ምርት ሽቅብ ወዳየር እያጓኑ በነፍሱ ይጫወቱበት ጀመር ።

ያልታደለው ጓኚ የሚያሰማው እሪታ በኃይል የሚያስተጋባ ስለነበረ ወዲያውኑ ወደ ዶን ኪሾት ጆሮ ለመድረስ ቻለ ። ያም ቆም ብሎ የእሪታውን አቅጣጫ ሲያዳምጥ በመጀመሪያው ጊዜ ስሜቱ አንዳች አዲስ አጋጣሚ የተገኘለት መስሎት ነበር ። እየቆየ ሲያጣራ ግን እሪታው የጋሻ ጃግሬው ድምጽ መሆኑን ለይቶ ስላወቀ ፈረሱን አዞረና እየጋለበ ወደ ሆቴሉ ተመለሰ ። ዳሩ ግን እዚያ ሲደርስ በሩ ዝግ ሆኖ ስለአገኘው መግቢያ ለመ ፈለግ የውድሞውን ዙሪያ እንደአለሌ ይዞር ጀመር ። በመስኩ አጥር አጠገብ እንደደረሰ የአጥሩ ቁመት በጣም ረጂም አልነበረምና ተንጠራርቶ ሲመለከት በሳንቾ ላይ የሚፈጸመውን አጉል ቀልድ ለማየት ቻለ ።

ዶን ኪሾት እዚያው ቆሞ በሚመለከትበትም ጊዜ ሳንቾ በአየር ላይ ሽቅብና ቁልቁል እየተመላለሰ በታላቅ ቅልጥፍና እና ፍጥነት ሲንር አይቶ ንዴት ባያቃጥለው ኖሮ በውነቱ የሚሠራው ተንኮል እሱንም ሳያስቀው የሚቀር አልነበረም ። ስለ

ዚህ በቀልዳቸው ተናድዶ ከኮርቻው ላይ ተነስቶ እርካቡ ላይ ቆመና በአጥሩ ላይ ተንጠልጥሎ ለማለፍ ሞክሮ ነበር ። ዳሩ ግን ሰውነቱ ቆሳስሎ ታፋውም ተደቁሶ ገና ገመምተኛ በመሆኑ በሙከራው ለመዝለቅ ስላልቻለ እዚያው ኮርቻው ላይ እንደተቀመጠ እነዚያን ሳንቾን የሚያራግቡትን ሰዎች ተደጋግሞ ሊነገር በማይቻል አኳኋን በዛቻና በስድብ ይጨፈጭፋቸው ጀመር ። እነሱም ይህን ፈርተው በሳንቾ ላይ መጫወታቸውንና ማስቃየታቸውን የሚተው ሰዎች አልነበሩም ። ከፊተኛው ይበልጥ እያጣደፉ ማጓናቸውን ቀጠሉ ። ሳንቾም ካሁን አሁን ይተውኛል ሲል እየጨከኑበት ስለሄዱ ያለ ክንፍ በሚበርበት ጊዜ ትንፋሹ እየተቆራረጠ አንዴ በዛቻ አንዴም በልመና እየወተወተ ይለፈልፍ ነበር ። ሆኖም እነሱ ደክሟቸው እስኪተውት ድረስ ይህ ውትወታውና ልመናው ምንም ሊረዳው አልቻለም ነበር ። በዚህ አኳኋን ሲጫወቱበት ቆይተው ስለሰለቻቸው ከብርድ ልብሱ ላይ አውርደው አህያውን አቅርበው ከጫኑት በኋላ በማቁ ሸፍነው እንዲሄድ ነፃ ለቀቁት ።

ማርቶርኔስ ያልናትም አስቱሪያዊት በጣም ልበ ርህሩህ ስለሆነች ሳንቾ በዚህ ሁኔታ መናበዙን ዓይታ አዘነችለትና አንድ ኩባያ ውሃ ልትሰጠው ፈልጋ ቀዝቃዛ እንዲሆንለት በማለት ከጉድጓዱ ውስጥ ቀድታ አመጣችለት ። ሳንቾም አመስግኖ ተቀበለና ለመጠጣት ወደ አፉ ሲያስጠጋ ዶን ኪሾት በሩቅ ይመለከተው ኖሮ እንዲህ ሲል ጮኾ ሲናገር ሰማውና ገና ሳይቀምስ ወዲያውኑ አቋረጠ ።

« የኔ ልጅ ሳንቾ ፣ ልብ አድርግ እንዳትጠጣ ፣ የጠጣህ ፣ እንደሆነ መሞትህን እወቀው » አለና የመድኃኒቱን ጣሳ እያሳየ « ይኸውልህ ተአምራዊውን መጠጥ ይገፎአለሁና ከዚህ ሁለት ጠብታ እንደጠጣህ በቅጽበት እንደምትድን እርግጠኛ ሁን » አለው ።

ሳንቾም ይህን ጥሪና ምክር ሲሰማ ፊቱን አዞረና ከዚያ ያኛው ይበልጥ እየጮኸ እንዲህ አለው ። « ለመሆኑ እኔ የተካንሁ ፈረሰኛ አለመሆኔን ክቡርነትዎ ዘንግተውት ነውን ይህን መርዝ ጠጣ የሚሉኝ ወይም ደግሞ ዛሬ ሌሊት በሆዴ

ውስጥ ተርፎ የቀረው ያንኑ ጥቂቱን አንጀቴን አስታውኬ እን ድጨርሰው ነው የሚፈልጉት ይበሉ ጌታዬ ይህን የሰይጣን መጠ ጥን እዚያው ለአራስዎና ለዲያብሎሶች ይጋብዙዋቸውና እኔን በሰላም እንድጠጣ ይተውኝ » አለው ።

ይሁን ተናግሮ መጨረሱና ውሀውን መጠጣት መጀመሩ ባንድ አፍታ የተፈጸመ ሥራ ነበር ። ዳሩ ግን በመጀመሪያው ቅምሻ ላይ ውሀ መሆኑን ስላወቀ መጠጣቱን ለመቀጠል አል ፈለገም ነበርና የወይን ጠጅ እንድትአመጣለት ማሪቶርኔዝን ለመናት ። እሷም ምንም እንኳ ባፈጣጠሯ እንደዚህ ባይተዋር ብትሆን ምን ጊዜም የዓላማዋን ቀጥተኛነት እርሮዋን የያዘች» ናት ስለሚሏት በቅን ልቦና ተልካ የገዛ ገንዘቧን ከፍላ የወይን ጠጅን ገዝታ አመጣችለት ።

እሱም ስለቸርነቷ አመስግኖ ተቀበለና ጠጥቶ ከጨረሰ በኋላ ምንም እንኳ በዚያው በተለመደው ሂሣቡ ይህም ማለት እራሱን በማስኮዳት ዋጋውን የከፈለው ቢሆንም በገንዘብ ረገድ ላንድም ነገር አንዲት ቤሳ ከኪሱ አውጥቶ ሳይከፍል አሸንፎ በመሄዱ በጣም እንደተደሰተ አህያውን በተረከዙ ሁለት ጊዜ ኮርኩሮ መንገድ ሲጀምር የሆቴሉን በር በረገዱለትና ወጣ ። ይሁን እንጂ ሆቴለኛው በዕዳው አስቦ ቦርሳውን በመያዝ አስ ቀርቶበት ነበር ። ሳንቾ ግን ሆቴሉን በለቀቀበት ጊዜ አንኮሰ ተበ ጥብጦ ነበርና ሆቴለኛው ቦርሳውን አስቀርቶት ሂሚቡን በገዛ እጁ መክፈልን እንዳወቀበት በጭራሽ ረስቶት ነበር ። ሳንቾ ወጥቶ መሄዱን ሆቴለኛው ከተመለከተ በኋላ ዶን ኪሾትን በመስ ጋት ለጥንቃቄ ሲል በሩን ደህና አድርጉ ለመቀርቀር ፈልጉ ነበር ። እነዚያ አራጋቢዎች ግን ክፍቱን እንዲቀመጥ ፈልገው እንዳይዘጋ ከለከሉት ። ምክንያቱም ሰዎች ጥጋበኞች ስለሆኑ ዶን ኪሾት ሌላው ቀርቶ ከውነተኞቹ « የክብ ጠረጴዛ » ዙዋሪ ፈረሰኞች አንዱ ቢሆንም እንኳ ከጤና ቅንጣት የማይቆጥሩ በመሆናቸው ነበር ።

ምዕራፍ 18

በጌትየው በዶን ኪሾትና በጋሻጃግሬው በሳንቾ ፓንዛ መካከል የተደረገውን አስደሳች ንግግር የሚጠቅስና እንዲሁም መተረክ የሚገባቸው የሌሎች ጥሩም የሆኑ አጋጣሚዎች ሁኔታ ይተረካል ።

ሳንቾ ከሆቴሉ ወጥቶ ከጌታው ጋር በተገናኘበት ሰዓት በጣም ተዳክሞ ነብዙ ስለነበረ ሌላው ቀርቶ አህያውንእንኳ ውሸ ለማ ለት ተሰኖት ነበር ። ዶን ኪሾትም በዚህ ሁኔታ ተዝለፍልፎ ሲመጣ አየውና እንዲህ አለው ።

« የኔ ደጉ ሳንቾ መጣህልኝ ? ይህ ግንብ ወይም ሆቴል በር ግጥ በምትሐት የተወረረ መሆኑን ከቅድሙ ይልቅ ገና አሁን አመንኩ ። ለመሆኑ እነዚያ ባንተ ላይ በጭካኔ ሲያላግጡብህ የነበሩት ሰዎች የሌላ ዓለም ፍጥረታት ወይም ጭራቆች ካል ሆኑ በስተቀር ሌላ ምን ዓይነት ሰዎች ለመሆን የሚችሉ ይመ ስልሃል ? ይህንንም አስተያየት ለማረጋገጥ የበቃሁት ከመስኩ አጥር ውጭ ሆኜ ያንን የሚያሳዝነውን የስቃይህን ልዩ ልዩ አደራረግ በምመለከትበት ጊዜ በደረሰብኝ መታገድ እንደ ተገነዘብኩት አጥሩን ለመዝለል ቀርቶ ከነአካቴውም ከሮንዜ ናንቴ ላይ እንኳ ለመነሳት ያልቻልኩበት ምክንያት በአስማት አፍዝዘውኝ መሆኑ ስለገባኝ ነው ። በዚህ አኳኋን ባልታገድና አጥሩን ዘልዬ ለማለፍ ወይም ለመንቀሳቀስ ችዬ ቢሆን ኖሮ እነዚያ ወስላቶች ለሠሩት ተንኰል ቅጣታቸውን በመስጠት ለዘለ ዓለም ሲያስታውሱት እንደሚኖሩ አድርጌ ጥቃትህን እበቀልህ እንደነበረ በፈረሰኛነት ክህነቴ ክብር እምልልሃለሁ ። ይህንንም ለማድረግ ቆርጬ የነበረው ከዚህ ቀደም ብዙ ጊዜ ደጋግሜ እንደነገርሁህ አንድ የተካነ ፈረሰኛ የሚያጣድፍና ከባድ የሆነ

ችግር አጋጥሞት ሕይወቱንና ክብሩን ለመከላከል ካልሆነ በስተ ቀር ፈረሰኞች ካልሆኑት ሰዎች ጋር ውጊያ እንዲገጥም የፈ ረሰኛነት ደንብ የማይፈቅድለት በመሆኑ ደንቡን የማፈርስ መሆ ኔን እያወቅሁት ነው ።

« ጠላቶቼ ፈረሰኞች ቢሆኑም ባይሆኑም አለ ሳንቾ የም ችል ብሆን ኖሮ እኔው እራሴ እበቀላቸው ነበር ። ዳሩ ግን ሳል ችል በመቅረቴ እንደተጠቃሁ ቀረሁ ። የሆነው ሆኖ በኔ አስ ተያየት እነዚያ የተጫወቱብኝ ሰዎች እንደኛው በአጥንትና በሥጋ የተፈጠሩ ሰዎች ናቸው እንጂ እርስዎ እንደሚሉት ጭራቆች ወይም በምትሐት የተሠወሩ ሰዎች አይደሉም ። ሁሉም ደንበኛ የክርስትና ስም ነበራቸው ። እኔንም በሚያራ ግቡበት ጊዜ እርስ በእርሳቸው በየስማቸው ሲጠራሩ ደህና አድርጌ ሰምቻቸዋለሁ ።

ለምሳሌ እንደኛው ጴጥሮስ ማርቲኔዝ ፣ ሁለተኛው ደግሞ ቴኖ ሪዬ ሔርናንዲዝ ይባላል ። ሆቴለኛውንም ዮሐንስ (ፖሎሜንቤ) ፖሎሜክ « አባ ግራኝ» ብለው ሲጠሩት ሰምቻለሁ ። ስለዚህ የተከበሩት ጌታዬ የመስኩን አጥር ለመዝለልም ሆነ ከፈረስዎ ላይ ለመንቀሳቀስ ያልቻሉት በሌላ አዳካሚ ምክንያት እንደሆነ ነው እንጂ በምትሐት ተይዘው እንዳልሆነ እርግጠኛ ነኝ ።

በዚህን ሰሞን ከደረሱብን መከራዎች የተገኘውን ውጤት ሳመዛዝነው ይህ እየዞርን የምንፈልገው አጋጣሚ ካነሰ ወደ ባሰ ጉዳት ላይ እየጣለን ቆይቶ በመጨረሻ ላይ መሞታችን ወይም በሕይወት መቆማችንን ለይተን ለማወቅ በማንችልበት አኳኋን እጅግ የበዛ አደጋ አከታትሎ አውርዶብናል ። ሁለተኛው ደግሞ በኔ በደንቆሮው አስተያየት እንደምገምተው ልናደርገው የሚገባንና የተሻለ በመሆኑም ሊመረጥ የሚገባው ፣ ጥንትም ሲባል እንደሰማሁት ከሄሮድስ ወደ ጲላጦስ ፣ ከምጣድ ወደረመጥ ፤ ከመጥበሻ ወደ ፍም መጋባታችንን ትተን ልክ ባሁኑ የመከር ወቅት ላይ ወደ አገራችን ተመልሰን በሠላምና በፀጥታ የዱሮ ሥራችንን ብንቀጥልና ጉዳያችንን ብናጠናቅቅ ነው ።

«አወይ የኔ ሳንቾ»! «አለ ዶን ኪሾት» ባሁኑ አነጋገርህ ስገም ትህ ስለፈረሰኛነት ጉዳይ ሊገባህ የሚችለው ምስጢር በጣም ያነስ መሆኑን እረዳዋለሁ ። ስለዚህ አይዞህ ! ዝም በል ! እስከዚህ ድረስ ሆደባሻ አትሁን ትእግሥትም ይኑርህ ፣ ይህን የፈረሰኛነት ተግባር ማከናወን በዓለም ላይ የቱን ያህል የሚያስከብር ሞያ መሆኑን በገዛ ዓይኖችህ የምታይበት ቀን በቶሎ እንደሚመጣ እመን ። ኧረ በል እስቲ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ ! በዚህ ዓለም ላይ ስት ኖር የሰውን ልጅ ታላቅነት የሚያጐላና የክብሩን ደረጃ ከፍ የሚያደርግ በጦርነት ላይ ድል ከማድረግ ወይም በገዛ ጠላት ላይ ከመግነን የበለጠ ምን ዓይነት ደስታ ሊኖር የሚችል ይመ ስልሃል ? ምንስ ዓይነት ተወዳጅ ነገር ሊተካከለው ይችል ይመ ስልሃል ? ያለጥርጥር አንዳች ነገር አታገኝም ።

«እርግጥ ላይገኝ ይችል ይሆናል» ሲል መለሰ ሳንቾ «መቼም ለኔ ይህን የመሰለው ነገር እንደማይገባኝ እርስዎም አውቀውታ ልና በበኩሌ ለጌታዬ የምገልጠው አስተያየት እኛ ዙዋሪ ፈረ ሰኞች ከሆንበት ጊዜ አንስቶ ወይም በተሻለ አነጋገር ክቡር ነትዎ ዙዋሪ ፈረሰኛ ከሆኑበት ጊዜ አንስቶ እኔ እንደሆንኩ በናንተ የክብር መዝገብ ውስጥ ገብቼ ለመቆጠር አልችል ምና ከዚያ ከቢስካሊያው በስተቀር ሌላ አንድም ጦርነት ድል አልተደረገም ። ይህም የቢስካሊያውም ቢሆን ክቡርነትዎ ድል ለማድረግ የቻሉት ግማሽ ጆሮዎንና ግማሽ የራስ ቁርዎን አስ ቆርጠው ነው ። ከዚያን ጊዜ ወዲህ የተገኘው ድል በማኩራት ፋንታ የሚያዋርድ በሽመል ላይ ፣ ሽመል በቡጢ ላይ ቡጢ ፤ እየተደራረበ መሆኑን አይዘነጉትም ። በተለይም ደግሞ እኔ በተ ጨማሪ የብርድልብስ ጉኖሽ አግኝቼአለሁ ። ክቡርነትዎ እንደ ሚሉት ከድል አድራጊነት የሚገኘው ክብርና ደስታ ምን ያህል የኩራትና የደስታ ስሜት እንደሚያሳድርና የደስታውና የክብ ሩም ወሰን እምን እንደሚደርስ ለማወቅ ስል እንኳ ጠላቴን ለመበቀል እንዳልሞክር የደረሰብን አደጋ ሁሉ የተፈጸመው በማይታዩትና በማይዳሰሱት በጥበብ በተራቀቁ ሰዎች አማካይ ነት ነው ።

«ይህ አሁን የተናገርከው ይልቅ» አለ ዶን ኪሾት» በውነቱ እኔንም በጣም የሚቆረቁረኝ ነገር ነው ። አንተንም እንደኔው እንደ

ቆረቆረሀ ይገባኛል ። ለወደፊቱ ግን የጥበቡን ማጥፊያ ዘዴ ለማ ግኘት እደክምበታለሁ ። ይኸውም ታጣቂውን ፈረሰኛ ከማና ቸውም ዓይነት የአስማት ኃይል ነፃ ሊያደርገው የሚችል በልዩ ጥበብና በረቀቀ ምስጢር ተከውኖ የተሰራ ሠይፍ ፈልጌ ለማ ግኘት እችል ይሆናል ። ይህም ሰይፍ አማዲሰን በዘመኑ « ባለ ሰይፈ ነበልባሉ ፈረሰኛ» እያሰኘኢያስጠራው የኖረና ጥንት በመላው ዓለም የነበሩ ዙዋሪ ፈረሰኞች ታጥቀውት የማያው ቁት ምርጥ ሰይፍ ነበር ። ምክንያቱም ከዚህ በላይ ከተነገረው አብነቱ ሌላ ስለቱ ከምላጭ ይበልጥ የሚቆርጥና እንደዚሁም የቴን ያህል የተባና የምትሐት ድግምት የተደገመበት መሳሪያ ቢሆን በፍጹም ሊመክተው ስለማይችል ነው ።

« እንግዲያውስ እኔ ምንም አልታደልኩም ማለት ነዋ»! አለ ሳንቾ ምክንያቱም ምናልባት ይህን የተመኙትን ዓይነት ሰይፍ ለማግኘት የቀናዎት እንደሆነ እንደዚያው እንደመፍትሔው አገልጋይነቱ ለተካኑት ፈረሰኞች ብቻ ስለሚሆንና ለጋሻ ጃግ ሬዎች ግን ያገኙት ሁሉ ገንዘባቸው ስለሆነ ይህን ሰይፍ ቢታጠቁትም ለመከራ አሳልፎ እንደሚሰጣቸው ስለማልጠራ ጠር ነው ።

« አይዘህ ሳንቾ አትፍራ ! ከእንግዲህ ወዲህ ሁኔታው እን ደሚጠበቅህ አመንና ልብህን አጽናናው ።

እንግዲህ በዚያው በሚጓዙበት መንገድ ላይ ከፊት ለፊታ ቸው በኩል ወደነሱ የሚመጣ የአቧራ ጉም ዶን ኪሾት አይቶ ንግ ግሩን እስከ አቋረጠበት ሰዓት ድረስ ሁለቱ ዙዋሪዎች እየሄዱ ሲነጋገሩ የነበሩት ይህን ከላይ የተጠቀሰውን ጉዳይ አንስተው ነበር ። ስለዚህ ዶን ኪሾት አቧራውን አየና ወደ ሳንቾ መለስ ብሎ እንዲህ አለው ።

« ሳንቾ ይህን የዛሬውን ቀን እስካሁን ድረስ ዕድሌ ደብቆ ያስቀመጠልኝ በጐ ነገር ምን ዓይነት እንደሆነ ተገልጠ የሚ ታይበት ቀን ነው ። ይህ የዛሬው ቀን ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ የክንዴ ኃይለኛነት የሚገመትበት ቀን ነው ። እንደዚሁም በጀግ ኖች የጎድል መጽሐፍ ላይ ተጽፎ ለመጪው ዘመናትና

ትውልድ የሚተላለፍ ተግባር የምፈጽምበት ይህ የዛሬው ቀን እንደሚሆን አምናለሁ ። በስተፊታችን የሚቦነውን አቧራ ታየ ዋለህ? ፤ በል እንግዲህ አደምጠኝ ፤ ይህ አቧራ ቁጥራቸውና ዓይ ነታቸው ብዙ በሆኑ ሰዎች የተሠራ ታላቅ የጦር ሠራዊት በሰ ልፍ ሲጓዝ ያነሳው ነው ።

«እንግዲያውማ ሠራዊቱ በሁለት የተከፈለ መሆን አለበታ!?» «አለ ሳንቾ» በስተኋላችንም ይህንኑ የመሰለ ሌላ አቧራ ይታያል ።

ዶን ኪሾት ወደኋላው ዞሮ ቢመለከት እውነትም አቧራ ስለሚታይ ይበልጥ ተደስቶ በዚህ በሰፊው ሜዳ ላይ ተጋጥመው ለመራኮት የሚመጡ የሁለት ወገን ሠራዊታት መሆናቸውን አሰበ። ምክንያቱም በየጊዜውና በየሰዓቱ በራሱ ውስጥ ሞልተው የሚ ታዩት ትርኢቶች ሁሉ በፈረሰኛነት መጽሐፍ ላይ ተጽፈው የሚተረኩት የጦርነትና የአስማት ድርጊቶች ፤ የተዘበራረቁ አጋ ጣሚዎች ፤ የፍቅር ሁኔታዎችና ዛቻዎች ስለሆኑ ፤ የሚናገረውና የሚያስበው የሚያደርገው ማናቸውም ነገር ሁሉ ይህን ከመ ሰለው አርእስት የሚቀዳ ነበር ። ዳሩ ግን ይህ ከፊቱም ከኋላ ውም ሲነሳ ያነው አቧራ በሁለት የተከፈሉ የበግ መንጋዎች በዚያው መንገድ ለመተላለፍ እየተነዱ ሲመጡ ያነሱት ነበር ። ይሁን እንጂ የአቧራው አነሳስ በሩቁ ሆኖ ለሚመለከት ሰው በው ስጡ ያለው ምን እንደሆነ ለመለየት የሚያስቸግር ስለሆነ ዶን ኪሾት መጪዎቹ የጦር ሠራዊታት መሆናቸውን አጥብቆ ካረ ጋገጠ በኋላ ሳንቾም ይህንኑ እምኖ መቀበል ግዴታ ስለሆነ በት እንዲህ ሲል ጥያቄውን አቀረበ ።

« ጌታዬ ሆይ ! ነገሩስ ይሁን በጅቷል ! እኛ ደግሞ በዚህ ውጊያ ውስጥ ምን ማድረግ ይገባናል »

« ምን ማድረግ ይገባናል ትላለህ ሳንቾ» ? ሲል ጠየቀ ዶን ኪሾት እንደተለመደው ደካማዎችንና እርዳታ ፈላጊዎችን ማገዝ በነሱ ጉን መሰለፍ ነዋ ። ለካንስ እስከዚህ ድረስ ቂል ኖረሃል። ይልቅስ የምንግርህን አድምጠኝ አሁን በስተፊታችን ያለው ሠራዊት የዘመተውና የሚመራው የታላቁ የትራፖባና ደሴት ጌታ ኃያሉ ንጉሠ ነገሥት አሊፋን ፋሮኔ ነው ። ሁለተኛው በስ

ተጀርባችን የሚመጣው ደግሞ የዚህ ንጉሠ ነገሥት ጠላት የሆነ የጋራማቴዎች ንጉሥ ፔንታፖሌና ነው ። የፈረስ ስሙም «ባለ ጉርድ እጅጌ» ይባላል ። ምክንያቱም ዘወትር ወደ ጦርነት መሐል ሲገባ ቀኝ ክንዱን አራቁቶ ነው ።

እነዚህ ሁለቱ ንጉሦች እስከዚህ ድረስ የተጣሉበት ምክንያት በምን የተነሳ ነው ሲል ሳንቾ ጠየቀ ።

«የተጣሉበት ምክንያት ሲል ዶን ኪሾት ማስረዳት ጀመረ።» ይህ አሊፋንፋሮኔ የሚባለው ንጉሥ አከራካሪ ሁኔታ ያለው ሆኖ ሳለ የፒንታፖሊናን ልጅ አፈቀረ ። ይህችም ብላቴና እጅግ የተዋበች ትሁት ነበረች ። ዳሩ ግን ብላቴናይቱ የክርስቲያን ልጅ በመ ሆኗ ምክንያት ይህ አረመኔው ንጉሥ የሐሳዊ መሲሁን የመሐ መድን ሕግ ትቶ በሰ ሃይማኖት ካልተጠመቀ በስተቀር አባቷ ሊድርለት ስላልፈቀደ በዚሁ ተቀያይመው ዘወትር ደም እንደ ተፋሰሱ ይኖራሉ አለው ።

« የሸንጐቤቴ ያለህ» ሲል ተደነቀ ሳንቾ የጥላቻው መነሻ ይህ የሃይማኖት ጉዳይ ከሆነማ ፔንታፖሊና በሃይማኖቱ ፀንቶ እስከ መጨረሻው መጋደል አለበት ። የሚዋጋበትም ምክንያት ትክክለኛና እውነተኛ ስለሆነ እኔም ባለኝ ኣቅሜ ልረዳው ፈቃ ደኛ ነኝ አለ ።

ሳንቾ ሆይ! ይህን ካደረግህማ የሚገባህን ተግባር ፈጸ ምህ ማለት ነው ። ምክንያቱም ይህን በመሰለው የክተት ጦር ነት ውስጥ ገብተህ ለመዋጋት የፈረሰኛነት ክህነት እንዲኖርህ አትጠየቅም ።

« ይህ የአሁኑ ሃሳብ በጣም ይስማማኛል አለ ሳንቾ። ሆኖም በውጊያው ላይ የሚገኘው ሠራዊት ለመግደልና ለመማረክ መሽ ቀዳደሙን ትቶ ክህነት ያለውንና የሌለውን የሚመረምር ዳኛ ስለ ሌለ እርስዎም ባይነግሩኝ የሚከለክለኝ ሰው አለመኖሩን አውቄዋ ለሁ ። ይልቁንስ አሁን የማማክርዎት ጉዳይ እስከዛሬ ድረስ እንደሚደረገው በጦርነት ውስጥ ለመግባት ፈረሰኛ ወይም በቅ ሎኛ ሆኖ ነው እንጂ ምንም ቢችግር አህየኛ ሆኖ መግጠም

የሚፈቀድ ስላልመሰለኝ አህያዬን ወዴት አስሬ ላቆያት? ፤ ጦር ነቱ ካለቀሳ በኋላ እንደገና ለማግኘት እርግጠኛ ነኝን ?

« ይህ ጥያቄ እውነት ነው አለ «ዶን ኪሾት» በበኩሉ ግን የተሻለ ነው ብዬ የምስጥህ ምክር አህያዬቱ ብትጠፋም ብት ገኝም እድሏ እንዳወጣ ያውጣት ብሎ ነፃ መልቀቅ ነው ። ምክ ንያቱም ጦርነቱን ድል በምናደርግበት ጊዜ ለማግረጥ እስኪ ስለችን ድረስ ብዙ የምርኮ ፈረሶች ስለሚኖሩን ያሰኘህን ያህል እየነዳህ ለመውሰድ ትችላለህ ። ሮንዚናንቴም ወደ ማርጀቱ ስለተቃረበ እሱንም በሌላ ፈረስ መለወጤ አይቀርም ። ሳሁን ግን በነዚሁ እየተጠጉ በሚመጡት በሁለቱ የጦር ሰራዊታት ውስጥ የሚገኙትን ዋና ጦር ቀማሽ ፈረሰኞች ለይቼ ላስጠናህ ስለምፈልግ የማሳይህን ልብ አድርገህ ተመልከት ። እንዲያውም ይበልጥ አጣርተህ ለማየትና ለመለየት እንዲመችህ በደንብ ለመ መልከት ወደሚቻልበት አዘያ ጉብታ ላይ እንውጣ አለውና ተያይዘው ወዳንድ ጉብታ ላይ ወጥተው ቆሙ ። እዚህም ላይ ሆነው የአቧራው ጉም ዓይናቸውን ጋርዶ ማየት ባይከ ለክላቸው ኖሮ ዶን ኪሾት የጦር ሠራዊት የሚላቸውን ሁለት የበግ መንጋዎች በግልጥ ለማየት ይችሉ ነበር ።

ዶን ኪሾትም የሌለውንና ያላየውን ነገር በቅዠት መንፈሱ እየፈጠረ የተዋጊዎችን ስምና መልክ ፣ የመሣሪያቸውን ዓይነትና ዋራት ፣ እየለየ በአንካሴው እየጠቀሰ በማሳየቱ ድምጹን ከፍ አድርጐ እንዲህ ይል ጀመር ።

«ያ በወርቅ የተኰላ መሣሪያ የለበሰውና እንዲሁም ባንዲት ብላቴና እግር ሥር ተኝቶ ዘውድ የጫነ አንበሳ የተሳለበት ጋሻ የያዘው ፈረሰኛ «የብሩ ድልድይ ጌታ» የተባለው ጀግናው ላውርካ ልክ ነው ። ሁለተኛው ደግሞ የወርቅ አበባ ቅርጽ ያለበት ጥሩራ የለበሰውና እንዲሁም መደቡ ሰማያዊ ሆኖ በላዩ ላይ ሶስት የብር ዘውዶች የተጌጠበት ጋሻ የያዘው የኪሮሲያ ታላቁ መስፍን ተፈ ሪው ሚኮሌምቦ ነው። ከርሱ በስተቀኝ በኩል ያለው ሰውነቱ ግዙፍ የሆነው የሶስቱ ዓረብ አገሮች ጌታ የተባለው ነፍሰቢሱ የቦሎቼው ብራንዳባርባራን ነው ። የለበሰውም ጥሩራ እባብ ሰንኮፍ ቅርጽ

Pdf by Meysor Bro

ሆኖ ስለጋሻም የያዘው አንድ የበር መዝጊያ ሳንቃ ነው። ስለዚህም ሳንቃ ሰዎች እንደሚተርኩት ሶምሶን ጠላቶቹን ለመበቀል አብሮ በሞተበት ጊዜ ካፈረሰው ምኩራብ የአንደኛው በር መዝጊያ የነበረው ነው ይባላል ። አሁን ደግሞ ዓይኖችህን ወደ ሁለተኛው ክፍለ ሠራዊት አዙርና የጦር አዝማቹን ፊትአውራሪ ሠራዊት ተመልከት ። ያ በሠራዊቱ ታጅቦ ሲተም የሚታየው ያዲሲቷ ቢስካሊያ መስፍን የካርሶናው ቴሞኔሉ ነው ። የለበሰውም ጥሩራ የመደቡ ሩብ ሰሚያዊ ፣ ሩብ ነጭ ፣ ሩብ አረንጓዴ ፣ ሩብ ቢጫ ሆኖ በአራት ማዕዘን የተሠራ ነው ። የጋሻውም መደብ መልኩ ዳለቻ ሆኖ በስጉዱ ላይ አንድ የወርቅ ድመት የተሳለችበትና እንዲሁም ትርጉም ባለው አነጋገር ሚያው የሚል ፊደል የተጻፈበት ነው ። የዚህም ምሳሌ የእመቤቱ የሰሚ የመጀመሪያው ፊደል ነው ። ይሽውም የአልጋርቬው መስፍን የልዑል አልፌ ፓኳን ልጅ የወደር የለሽ ልዕልት ሚያውሊና ሙሉ ስሚ ነው ይባላል ። ሌላኛው በዚያች በስቅስቋ ባዝራ ላይ ጉብ ያለውና እንደበረዶ የነጣ መሣሪያ የያዘው ፣ አንዳች የጀብዱ ሥራ ምልክት የሌለበት ልሙጥ ጋሻ ያነገበው ፣ የፈረንሳይ ተወላጅ የሆነ አዲስገብ ፈረሰኛ ነው። ስሙም ኢጥሮስ ፖፒን የሚባለው የአትሪክ ጉልቶች ጌታ ነው ። ወዲህኛው ባለ መኰርኰሪያው ተረከዙ የዚያቺን የዝጉርጉራን እና የፈጣኒን ሜዳ አሀያ ወገብ የሚጉሸመውና እንዲሁም በመሣሪያው ላይ ሰማያዊ ጽዋዎች የተቀረጹበት ኃያሉ የኦርቢያ መስፍን የዱኔ ኤስፖርታፊላርዶ ነው። በጋሻው ላይ የሚገኘው የጀብዱ ምልክት የሴሪቲ ተክል ያለበት ሆኖ በካስቲሊያ ቋንቋ ከሥሩ « ራስትሪያ ሚ ሱዊርቴ » (ዕጣዬን ተከተል) የሚል ጽሑፍ ይነበባል ።

በዚህ አኳኋን በፊተኛውም ሆነ በኋለኛው የጦር ሠራዊት ውስጥ በቅዠት መንፈሱ የሚያያቸውን ብዙ ፈረሰኞች በዝርዝር እየጠራ የሁሉንም ማዕረጋቸውን ፣ የጦር መሣሪያቸውን ፣ ቀለማቸውን ፣ የጀብዱ ምልክታቸውን ፣ ቃለ ምሳሌያቸውን እያመለከተ ከመጠን ያለፈ እብደቱ ያቃዠውን ሁሉ ከለፈለፈ በኋላ እንደገና ደግሞ በመቀጠል የሚከተለውን መናገር ጀመረ ።

« ይህ በስተግንባራችን ያለው ፈረንሳዊ ጦር ከልዩ ልዩ አገር ሰዎች የተገነባ ነው ። በዚህም ጦር ሠራዊት ውስጥ

የስመ ጥሩውን ከሳንቶ ጣፋጭ ውሀ የሚጠጡት ሰዎች ይገኙበታል ። እነዚያ በማርሲሊያ ገጠር የሚኳትኑት ባላሮች ፣ እነዚያ የሃብታሙን ዓረብ ረቂቅና ደቃቅ ወርቅ የሚያንጓልሉት ሰዎች እነዚያ የስመ ጥሩዎቹን የቴርሞ ዶንቴን ወንዞች የጠሩትንና ንጹህ የሆኑትን ቀዝቃዛ ውሀዎች እንደልባቸው የሚያገኙትን ሰዎች እነዚያ በብዙና በልዩ ልዩ መንገድ የፖቶሎን ወርቅ የሚለቅሙት ሰዎች እነዚያ በቃላቸው የማይረጉትና የማይታመኑት ወላዋዮች ኑሚዲዎች ፣ እነዚያ በቀስታቸውና በወሰፈ ንጥራቸው የታወቁት ፋርሶች ፣ እነዚያ እየሸሹ የሚዋጉት ፖርቲዎችና ሚዴዎች ፣ እነዚያ ዘላን የበረሀ አረቦች ፣ እነዚያ ልባቸው ጥቁር ቆዳቸው ነጭ የሆኑቪታዎች ፤ እነዚያ በቃጭልና በዶቃ ያጌጡትና ከንፈራቸውን የተበሱት ኢትዮጵያዎች ፣ ሌሎችም መልካቸውን የማያቸውና የማውቃቸው ስማቸውን ግን ለጊዜው የማላስታውሳቸው ሁልቆ መሣፍርት የሌላቸው አገሮች ሁሉ ሕዝባቸው ተቀያይጦ ይገኝበታል ።

በዚህኛው በሌለኛው በስተፊታችን በሚመጣው ፊት/ወራሪ ጦር ውስጥ ደግሞ እነዚያ ከቤቱ የወይራ ደን ሥር የሚፈል ቁትን ብርጭቆ የሚመስሉ ፏፏቴዎች የሚጠጡት ፣ እነዚያ ዘወትር የሞላውንና ወርቅማ የሆነውን የታጉን ጅረት መልኩን የሚያደፈርሱት ፣ እነዚያ የመለኮታዊውን ጄኔል ጤና ሰጪ የጠበል ውሀ እንደልብ የሚያገኙት ፣ እነዚያ ለከብት ማሰማሪያ ምቹ በሆኑትና በበለፀጉት ሜዳዎች ላይ ሲራወጡ የሚውሉት አረኞች ፣ እነዚያ በጃሪስ የርቀ ሠላም ሜዳ ላይ ሲጫወቱና ሲቧርቁ የሚውሉት ሥራ ፈቶች ፣ እነዚያ የወርቅ ጉን ጉን አክሊል የሚያደርጉት ሃብታሞች ማንቼናዎች እነዚያ የብረት ልብስ የሚለብሱ ከጥንታውያን ጌታዎች ደም የፈለሱ ዝርያዎች ፣ እነዚያ በውሃው ጥራት ስመጥሩ በሆነው በፔስዌርኃ መልካ ገላቸውን የሚታጠቡት ሰዎች ፣ እነዚያ በአውራረዱ በጥልቅነት በታወቀው በጥምዝምዙ ጓዲያና ወንዝ ዳር ሰዳር ሠፈና ጨፈጨያማ በሆነው መስክ ላይ መንጋዎቻቸውን አሠማር ተው የሚያግዱት እረኞች ፣ እነዚያ ከፔሬኔይ ደንና ከኩሬው እፔኔና በረዶዋም ተረተሮች ላይ እየነፈሱ በሚመጡት ብርዳም አየሮች የሚንቀጠቀጡት ሰዎች ፣ በሰብሳቢ ቃል ፤ እነዚያ አውሮፓ

በወሰኗ ከብባና አቅፋ በያዘቻቸው አገሮች የሚወለዱት ሁሉ ይገ ኙበታል ።

« ኢየሱስ ማረኝ ስንቶቹን አውራጃዎች ጠራቸው ፤ ስንቶ ቹን አገሮች አነሳቸው ፤ ለያንዳንዳቸው የሚገባቸውን ስያሜ በሚ ያስደንቅ ፍጡንነት እየሰጠ ዘረዘራቸው ፤ በውነቱ በጣም የሚገርም እብደት ነው ። መቸም አፍታ ዕድሜ ባላቸው በልበ ወለድ ድር ሰቶቹ ስም ውስጥ እንደ ጢፍ ተነከሮአልና የሚናገረው ሁሉ ያንኑ የድርሰቱን ንባብ እየከላለሰ ነበር ። ሳንቾም አንዳች ቃል ለመናገር ፋታ ሳያገኝ ጌታው የሚቃዣውን ሁሉ አፉን ከፍቶ ያዳምጥ ነበር ።

«አንዳንዴም እውነት እየመሰለው ጌታው የሰየማቸውን ፈረሰኞችና ጀዊሣዎች ለማየት ግራና ቀኝ ይገላመጥ ነበር» ።

ዳሩ ግን አንዳች ነገር ለማየት ስለአልቻለ መጨረሻው እንዲህ ሲል ጌታውን ጠየቀው ።

«ጌታዬ ሆይ ! አሁን ክቡርነትዎ ከጠሯቸው ውስጥ አንድም፤ ሰው አንድም ጀዊሣ አንድም ፈረሰኛ በመሀል መታየቱ ቀርቶ ጥላቸው እንኳ የታየ እንደሆነ ዲያብሎስ ነፍሴን ነጥቆ ይውሰ ዳት ። እንደዛሬው ሴሊት ጭራቆች የአስማት ጉዳይ ይሆንን ?

«እኔ እንደሆንኩ እንኳን ይህንን ያህል ሠራዊትና አንድ ሰው እናኳን አልታየኝም» ።

« ምን ማለትህ ነው አለው ዶን ኪሾት » አይንህ ቢታ ወር ጆሮህ አልተዶፈነም ፥ የቀረው ቢቀር የፈረሶቹ ማሽካካት ፥ የእምቢልታው መነፋት ፥ የከበሮዎች መጐሰም ሲያስተጋባ አይ ሰማህምን ?

« እኔ ግን አለ ሳንቾ የብዙ ጠቦቶችና የብዙ ሙክቶች ጩኸት በስተቀር ሌላ ድምጽ አይሰማኝም ።

ይህ ንግግር በሚደረግበት ጊዜ ከፊትም ከኋላም የሚመ ጡት የበግ መንጋዎች ተቃርበው ነበርና እውነትም ሳንቾ እን ደሚለው ጩኸታቸው ጐልቶ ይሰማ ነበር ።

ዶን ኪሾትም እንዲህ ሲል መለሰለት «ሳንቾ ሆይ ! ፊት ለፊት ታላቅ ፍርሃት ዓይንህን እያንበገበገ ጆሮህንም እየኮ ረኮረ እንዳታይና እንዳትሰማ ሊያደርግህ እንደሚችል አውቃ ለሁ ። የፍርሃትም ዋናው ጠባዩ መንፈስን ማወክና ማናቸውም ነገር በእውነተኛው መልኩ እንዳይታይ አድርጐ ማደናገር ነው ። መሪነት ሲባል (በውርስ ጊዜ ልባሙ ፈሪውን ልባም ያደር ገዋል ። በፈሪ ላይ ፍርሃትን ፥ በጐበገ ላይ ድፍረትን ያበዛል ። ፈርተህ እንደሆነ ወዳንዱ ጥግ ተሸሸጥና እኔን ለብቻዬ ተወኝ። እኔ እንደሆንኩ ወገኑ ሆኜ የምዋጋለት ክፍል ድል አድራጊ ነት እንዲያገኝ ለመርዳት ብቻዬን እበቃለሁ አለው ።

ይህን ከተናገረ በኋላ ሮንዚናንቴን ኮርኩሮ ይውጣ አን ካሴውን ዘቅዝቆ ከጉበታው ላይ እንደመብረቅ ተፈንቅሎ ወርዶ ሽምጡን ለቀቀ ። ሳንቾም እዚያው ላይ እንደቆመ እንዲህ እያለ ይጮህ ጀመር ።

« ጌታዬ ዶን ኪሾት ወደኋላዎ ይመለሱ ፥ ስለእውነት ብለው ይመለሱ ፥ እንዳይታለሉ ፥ የበግ መክቶች ናቸው ብዬዎታለሁ ፤ ወይኔ መከረኛው ምነው የተወለድኩ ዕለት ሞቼ በቀረሁት፤ ለመ ሆኑ ምን ዓይነት እብድ ኖረዋል የምከተለው ኋላ አይሆንም መሳቂያ እንዳይሆኑ ይመለሱ ፥ ጀዊሣም ፈረሰኛም ድመትም ጥሩራም የለም ። እርስዎ እንዳሉት ሩብም ሙሉም ጋሻ የለም ፤ ሰማያዊ ፅዋም ሰይጣንም የለም ፥ እባክዎ ይቅርብዎት ይመለሱ። ምን ሊያደርጉ ይሆን? ወይኔ አሳረኛው ፥ ወይኔ እድለቢሱ ፥ ወይኔ እርጉሙ ፥ እርስዎን የምከተለው ፥ እያለ ጢሙን እየነጨና እየ ተማፀነ ይማረር ነበር ።

ዶን ኪሾት ግን አንድ ጊዜም እንኳ ፊቱን አልመለሰም ። እንዲያውም በጉላ ድምጽ እየፎከረ እንዲህ እያለ ይሄድ ነበር ።

« ተው አርጋ በለው ፥ በርታ በለው ፥ እናንተ በጐበዙ ንጉሠ ነገሥት በባለ ጉርድ እጅጌው ፔንቴፖሊኖ ሰንደቅ ዓላማ ሥር የምትመሩትና የምትዋጉት ፈረሰኞች ሆይ ! ሁላችሁም ተከተሉኝ ፥ በንጣፋችሁ ጠላት በትራፖባኖው ደሴት መስፍን በአሊፋንፋሮኔ ላይ የምፈጽመውን በቀል ታያላችሁ ።

ይህን ከተናገረ በኋላ በበጐቹ ሠራዊት መካከል ገባና በእውነተኛ ደመኛ ጠላቶቹን የሚዋጋ ይመስል በብዙ ድፍረትና በብዙ ማምረር እነዚያን የዋሃን እንስሳት በጦር ይሸጥባቸው ጀመር ። መንጋዎችንም የሚነዱት እረኞችና ባለቤቶች ይህን ያልታሰበ አደጋ በማየታቸው ተደናግጠው እየጮኹ እንዲተው ያወግዙት ነበር ። ዳሩ ግን ጩኸታቸው ለምንም እንዳልረባና መልስም እንዳልሰጣቸው ከተረዱ በኋላ ወንጭፋቸውን ከየወገባቸው ላይ ፈቱና ቡጢ በሚያካክል ኰረትና ጓል እያነሱ በመወርወር በጆሮ ግንዱ ሥር ያስፋጩበት ጀመር ። ዶን ኪሾትም ለመጀመሪያ ጊዜ የተወነጨፈውን ድንጋይ ከጉዳይ አልቆጠረውም ነበር ። እንዲያውም መንጋዎችን እያተራመሰ በመካከላቸው ወዲያና ወዲህ እየጋለበ እንዲህ ማለቱን ቀጠለ ።

ወዴት ነህ ትእቢተኛው አዳ ፋንፋሮኔ ብቅ በል እንግዲህ ፤ ጀግናውን ንጉሥ የጋራማንቴውን ፔንታፖሊኖ ያላቅምህ እየተነኰስህ በማስቸገር የሚገባህን ቅጣት ለመስጠት ካንተ ጋር አንድ ላንድ ገጥሜ ነፍስህን ከሥጋህ ለመለየት ቆርጬ የመጣሁት አንድ ጠልጣላ ፈረሰኛ ስለሆንኩ ወንድነትህ እንዲታይ ፈንጠር ብለህ ከመካከል ውጣ ።

እዚህ ነጥብ ላይ ሲደርስ እነሆ አንድ የድንጋይ አለሎ ተወርውሮ ጐኑን ቢመታው ሁለቱን የጐድን አጥንት ጠረመሰበት ። በዚህም ምት ስሜት መሞቱን ፣ ወይም በብርቱ የቆሰለ መሆኑን ስለአመነ ያንን ቀምሞ የያዘውን ተዓምራዊ አብነት አስታወሰና ጣሳውን ከብብቱ ወደአፉ ወስዶ ይጠጣ ጀመር ። ዳሩ ግን ለመድኃኒት ይበቃል ብሎ የገመተውን ያህል ከጉሮሮው ከማውረዱ በፊት እነሆ ደግሞ ሌላ ሙልሙል ተወርውሮ ጣሳውን ሙሉ ለሙሉ መትቶ አነካከተበት ። እግረ መንገዱን ደግሞ ሶስት ወይም አራት ጥርሶቹን አርግፎለት ከእጁም ጣት ሁለቱን ሰብሮለት አለፈ ። የመጀመሪያውም ሆነ ሁለተኛው አመታት ኃይለኛ ስለነበር ያልታደለው ፈረሰኛ በብርቱ እንደተጐዳ ከኮርቻው ላይ ተዘንጥፎ መውደቅ ግዴታ ሆነበት ። እረኞቹም ተጠግተው ሲያዩት የሞተ መስሏቸው ስለፈሩ በፍጥነትና በጥድፊያ መንጋዎቻቸውን ሰበሰቡና የሞቱትንም ከስ

ድስት የሚበልጡ በጐች በጫንቃቸው ላይ ተሸክመው ሌላ ነገር ለማወቅ ሳይሹ ከዚያ ስፍራ በሩጫ እየሸሹ ራቁ ።

ሳንቾም ይህ ሁሉ ረብሻ በሚሆንበት ጊዜ እዚያው እጉብታው ላይ እንደቆመ ከጌታው ጋር የተዋወቀበትን ቀንና ሰዓት እየረገመ ፣ በንዴት ጢሙን እየነጨ ፣ ዕድለቢስነቱን በማማረር ጌታው የሚሠራውን የዕብደት ሥራ ይመለከት ነበርና ጌታው ተመትቶ መውደቁን እረኞቹም ሸሽተው መራቃቸውን ከአየ በኋላ እየተበሳጨ ከጉብታው ላይ ወርዶ ወደሱ ሄደ ። ዶን ኪሾትም በሚያሳዝን ሁኔታ ላይ ቢገኝም ሕሊናውን አልሳተም ነበርና ሳንቾም አጠገቡ እንደደረሰ እንዲህ አለው ።

« ጌታው ዶን ኪሾት እነዚያ ሊገጥሟቸው የሄዱባቸው የበግ መንጋዎች እንጂ የጦር ሠራዊት አለመሆናቸውን ደጋግሜ እያስረዳሁ ወደ ኋላዎ ይመለሱ ብዬ አላስጠነቀቅሆት ምን?

« ማስጠንቀቁንስ አስጠንቅቀኸኝ ነበር አለ ዶን ኪሾት » ዳሩ ግን ምን ይደረግ ያ ጠላቴ አመፀኛው ፉቅራ የሠራዊታትን መልክ ለውጦ እንዲሠወሩ አደረጋቸው ። ሳንቾ ሆይ ! እነዚህ አስማተኞች የፈለጉትን ነገር በፈለጉት መልክ ለውጠው ላንተ መስሎ እንዲታይ ማድረግ የማይሳናቸው መሆናቸውን ማወቅ ይገባሃል ።

ይህ የሚከታተለኝ እርኩስ አስማተኛ በዚህ ጦርነት ላይ ላገኘው እችል በነበረው የአሸናፊነት ክብር የሚመቀኝ በመሆኑ የጠላትን ጦር ሠራዊታት ወደ በግ መንጋነት ለወጣቸው ። ቃሌን ለማመን ቅር የሚልህ እንደሆነ እኔ የነገርኩህ እውነት መሆን አለመሆኑን በዓይንህ ዓይተህ ለመረዳት እንድትችል እንዲህ አድርግ ፣ አህያህ ላይ ውጣና ቀስ እያልክ በዱካቸው ተከተላቸው ። ከዚህ ጥቂት ራቅ እንዳሉ ወዲያውኑ የበግ መንጋነታቸው ቀርቶ ቅድም ዘርዝሬ እንደነገርኩህ ደንበኛ ሰዎች ሆነው ታገኛቸዋለህ ። ዳሩ ግን ባሁኑ ሰዓት ያንተን እርዳታ በጣም እፈልገዋለሁና በቶሎ አትሂድብኝ ። መቸም አንድ ጥርስ እንኳ ተርፎ የቀረኝ አልመሰለኝምና በልስቲ ተጠጋና ምን ያህል ጥርሶች እንደጐደሉብኝ አይተህ ንገረኝ » አለው ።

ሳንቾም ትእዛዙን ተቀበለና በውል ለማየት እንዲመቸው ዓይኑን ወደ አፉ ውስጥ ከተተ፤ ለማለት በሚያስችል አኳኋን እንደእንጥል ቆራጭ ተጠግቶ ከንፈሩን እየፈለቀቀ ይመረምር ጀመር። ዳሩ ግን በዶን ኪሾት ሆድ ውስጥ ሲገለባበጥ የቆየው ያ ቅድም የጠጣው ተአምራዊ መድኃኒት ሲሰራ ውሎ ልክ በዚህን ሰዓት ስለባረቀ በውስጡ ያለው ቡልቅታ በኃይል ወጥቶ የታጋሹን ጋሻ ጃግሬ ፊት በሙሉ አጥለቅልቆ ቢያለብሰው የኋ ሊት ፈንግሎ ጣለው።

ሳንቾም በዚህ የዱብ እዳ አደጋ ደንግጦ ከተነሳ በኋላ እን ዲህ አለ፤ «የሰላም» ያለህ አውን ባሁን የምንፍርጀ ነው የደረሰብኝ? ይህ ሰው ድም ካስታወከው ያሰጥርጥር ለሞት በሚያስጋው አኳኋን ቆስሏል ማለት ነው።

ዳሩ ግን የተተፋውን ነገር ለማወቅ ፊቱን ጠራርጐ ቢያ የው በቀለሙም ፣ በሽታውም በጣሙም ፣ ቅድም ከጣሳው ውስጥ ሲጠጣው የነበረው መፍትሔ እንጂ ደም አለመሆኑን ተረዳው። በዚህም ጊዜ የመድኃኒቱ ሽታና ጣዕም ስለአቅለሸለሸው እሱም በበኩሉ ምንም ያህል ሳይቆይ በጌታው ላይ ቾለበስበት። በዚህ አኳኋን ሁለቱም እንዳልሆነ ሆነው ተሠራሩ። ሳንቾ ፈጥኖ ተነሳና ዶን ኪሾትን ለማከሚያና ለማጽጃ የሚሆን ጨርቅና ቅባት ለማምጣት ወደ አህያው ሮጠ። ዳሩ ግን መመከኪያቸው ሁሉ የነበረበትን ሻንጣ ሆቴሰኛው አስቀርቶት ኖሮ አለመገኘቱን ሲያስበው ጊዜ ባንድ አፍታ እብድ ሊሆን ምንም አል ቀረውም ነበር። እንደገና የተለመደውን የእርግማን መዓት አከታትሎ ካወረደ በኋላ ያቺን ተስፋ የተደረገችለትን የደሴት ግዝነትና እስካሁንም ድረስ ያገለገለበትን ደመወዝ ጭምር የሚያሰጣውም ቢሆን ጌታውን እዚያው እወደቀበት ቦታ ጐል ቶት ወደአገሩ ለመመለስ በልቡ አቀደ። ሳንቾ በዚህ ሁኔታ ፊቱን አኬማትሮ በሚበሳጭበት ጊዜ ዶን ኪሾት ከወደቀበት ተጣጥሮ ተነሳና ጥርሶቹ ጨርሰው እንዳይረግፉበት አፉን በግራ እጁ አፍኖ ይዞ ፣ በቀኝ እጁ ደግሞ የሮዜናንቴን ልጓም እየሳበ «መቸም ፊረሱ ታማኝና በደንብ ስልጥኖ ያደገ ስለሆነ ከአጠ ገቡ አልተንቀሳቀሰም ነበርና» ወደ ጋሻ ጃግሬው ሄደ።

ያኖውም በደረቱ አህያይቱን ተደግፎ ፣ ሁለቱንም መዳፎቹን እጉንጮቹ ላይ አድርጐ በሚያስጨንቅ ሃሳብ እንደተወጠረ ሰው ሆኖ አገኘው። እንደአካሄዱ ፈጥኖ በመመለስ ፈንታ በዚህ አኳ ኋን በጥልቅ ትካዜ ፊቱ ተጨማደዶ በማየቱ ግራጣባውና እን ዲህ ሲል ያጽናናው ጀመር።

«ስማኝ ሳንቾ አንድ ሰው ከሌላው ይብልጥ ካልሰራ የሌላውን ያህል ዋጋ ሊኖረው አይችልም። ይህ በኛ ላይ የዘ ነበው የስምኑ ማእበልና ውሽንፍር ወደፊት በቅርቡ የሚያበ ራና የጉዳያችንን መቃናት የሚያስተማምን ምልክት ነው። ምክ ንያቱም ከፉና በጐ ነገር ለዘለዓለም እንዲኖሩ ሆነው ስለተፈ ጠሩ እና እንዲሁም ክፉው ነገር ብዙ ጊዜ በኛ ላይ ስለቆየብን ከአንግዲህ ወዲያ የሚተካው በጐ ነገር ቅርባችን መሆኑን ለማ ረጋገጥ እንችላለን። ስለዚህ አንተን በማይነካውና በፍጹም ባል ደረሰብህ በተለይ በኔ ላይ ብቻ በደረሰው አደጋ እስከዚህ ድረስ መመረርና መበሳጨት አይገባህም» አለው።

«እንዴት ነው የሚሉት ፥ እንደምን እኔን አይነካኝም?» ሲል ጠየቀ ሳንቾ አረ ለመሆኑ ትናንትና በዚያ ሆቴል ውስጥ በብርድ ልብስ ተገንዘ ሽቅብ ሲጓንጉኝ ሳይሰማ ኖሯል ያባቴ የባህር ልጅ ሳንቾ አልነበረምን? ዛሬስ ደግሞ ሙሉ ጠቃሚ እቃ እንደ ያዘ የጠፋው የውዴላ ቦርሳ ምናልባት የሌላ ሰው ኖሮአልን? እንተን አይነካህም የሚባለው ከመንካትም አልፎ ልቡን ጭምር ቦጭቆ ወስዶታል» አለው።

«እንዴት በል ቦርሳውም ጠፍቶብሃል እንዴ» ሲል ዶን ኪሾት ጠየቀው።

«አምን እልም ብሎ ጠፍቶብኛል» ሲል አረጋገጠ ሳንቾ እንደተናደደ።

«እንግዲያውማ ለዛሬ ማታ እራታችንን የምንበላው ምንም የለን ማለት ነዋ» ሲል ጠየቀው ዶን ኪሾት።

በእርግጥ የለንም «ሲል መለሰ ሳንቾ ንግግሩን በመቀጠል» ባለፈው ጊዜ ክቡርነትዎ የነገሩኝን እንደማስታውሰው እነዚያ

እንደርስዎ ዕድል የከዳቸው ዙዋሪ ፈረሰኞች አሁን እኛ በም ንገኝበት ሁኔታና እንዲሁም በክፉ ቀን ዘመን ከጫካና ከሜዳ እየለቀሙ እርሃባቸውን ይከላከሉበታል ያሉኝን ዓይነት ፍሬዎችና ቅጠላ ቅጠሎች በዚህ መስክ ላይ አግኝተን ለቅመን ለመብላት ካልቻልን በስተቀር ሆዳችን እንደተጣበቀ ጦማችንን ተያፍተን ማደራችን ነው» አለው ።

« የሆነው ሆኖ » ሲል መለሰ ዶን ኪሾት ባሁኑ ሰዓት ያደ ረብኝ የምግብ ፍላጐት የሐመልማሎች ሊቅ ዲዩስኮሪዴ ተበ ይነታቸውን በዝርዝር ከጻፋቸው እና ዶክተር ላጐናም በስዕል አንስቶ ካሳያቸው የዓለም ቅጠላቅጠሎች ሁሉ ይልቅ ቁራሽ ዳቦና ጥቂት ገንፎ ከሁለት የአሳ ጥብስ ጋር ባገኝ በደስታ እበላ ነበር ። ዳሩ ግን ለማይገኘው ነገር መጓጓት ከንቱ ስለሆነ መል ካሙ ሳንቾ አህያህ ላይ ውጣና ወደምሄድበት ተከተለኝ ። አይ ዞህ አታስብ ፣ የማናቸውንም ፍጥረት ውሎና አዳር የቀደነገ ውና ያደራጀው አምላክ የከፈተልንን ጉሮሮ ሳይዘጋው አያድ ርምና እሱው ይጨነቅበት ።

ተፈጥሮ በኪነ ጥበቡ እኛ እራሳችንን መርዳት ለምንችለው ለሰ ዎች ከሚያደርገው ቸርነት ይበልጥ ያየሩን በራሪዎችና ትንኞች ፣ የምድርን ትላትሎች ፣ የባሕርን ተርመስማሾች ሁሉ መግቦና አጥግቦ ስለሚያሳድራቸው ለነሱ ያሰበ አምላክ እኛን የሚረ ሳን አይምሰልህ ። እንኳንስ እኛን ለሰው አገልግሎት ስንል ዓለምን የምንዞረውን ከመርዳት ችላ ሊል ይቅርና በቸርነቱ ሠፊነትና በርህራሄው ታላቅነት ፀሐይን ለደጐች ለክፉዎችም ያወ ጣላቸዋል ፣ ዝናምን ለምሕረትም ለጥፋትም ያዘንብላቸዋል ። በዓለም ላይ ከረድኤቱ የማይሳተፍ ፍጡር ከቶ አይገኝም» አለው ።

« ክቡርነትዎ ጠቃሚ የሚሆኑበትን ስጦታዎን ቢያውቁት ኖሮ » አለሳንቾ ከዙዋሪ ፈረሰኛነት ይልቅ ለሰባኪነት በጣም የተገቡ ነበሩ ። በዚህ ዓይነት ልብን ጠልቆ በሚነካ አሰባበክዎ ብዙ አሕዛብ ለማሳመን እንደሚችሉ እርግጠኛ ነኝ ።

« ውድ ሳንቾ ሆይ ! ሲል መለሰ ዶን ኪሾት ዙዋሪ ፈረ ሰኞች ሲባሉ በጠቅላላው ሁሉን ነገር አዋቂዎች ናቸው ። ሁሉ

ንም ማወቅ ይገባቸዋል ። ምክንያቱም ባለፉት ክፍለ ዘመናት ከነበሩ ዙዋሪ ፈረሶች አብዛኛዎቹ በፈረንሳይ ዩኒቨርስቲ የተ መረቁ ሊቆች ይመስል በማናቸውም የጦር ሜዳ ሠፈር ላይ በሚ ነሳው ብርቱ ክርክርና በሚደረገው የጉባኤ ንግግር ሃሳባቸውን ለመስጠትና ነቀፌታ ለማድረግ ፣ ትችት ለማቅረብ የተሟላ ችሎ ታና ስሚነት የበለፀገ ጥልቅ አስተያየት ስላላቸው እና ይህን የመሳሰለውንም አፍአዊ ጦርነት ለማሸነፍ ዝግጁዎች ስለነ በሩ በዚህ የተነሳ «ጦር ብዕርን አይቀርጸውም ብዕርም ጦርን አይስለውም » ተብሎ ተወስኗል ።

እርስዎ እንዳሉት ይሆን ይሆናል «ሲል መለሰ ሳንቾ » የሆነው ሆኖ ላሁን ከዚህ ስፍራ እንነሳና ዛሬ ሌሊት ለማደር የምንችልበትን ቦታ በጊዜ እንፈልግ ። በእውነት ጸንተን ከተዘጋጀን በብርድልብስ የሚያራግቡ ሸረኞች ፣ በቡጢ የሚማቱ ጭራቆችና በምትሐት የሚያፈዝዙ ዓረቦች የማይገኙበት ሰላማዊ ቦታ ያጋጥመን ። ምናልባት ከእንግዲህ ወዲህ ይህን የመሰለ ሰይጣናዊ ሥራ ያገኘን እንደሆነ ማናቸውንም ነገር ከንብዬ ጥዬ ወደ አገሬ መሄድ እቅጭ ያለው ቁርጥ ሃሳቤ ነው » አለው ።

«ልጄ ሆይ በትክክለኛ ሥራህ ላይ ተማመን አለ ዶን ኪሾት ። ላሁን ተነሳና አንተ ወደፈለግሽው አቅጣጫ ምራኝ ። ለዛሬ የማደሪያ ቦታ የመምረጡን ኃላፊነት ላንተ ለመልቀቅ ፈቅጄ አለሁ ። «አለውና» እስቲ ከመነሳትህ በፊት እጅህን ወደአፌ ስደ ድና ባንድ ጣትህ እየነካህ ከላይኛው መንጋጋዬ በስተግራ በኩል ስንት ጥርሶች እንደጐደሉ እይልኝ ። ምክንያቱም ሕመሙ በጣም የሚሰማኝ ልክ እዚሁ ቦታ ላይ ነው ።

ሳንቾም ጣቱን ወደ አፉ ከተተና መንጋጋውን ከዳሰሰው በኋላ እንዲህ ሲል ጠየቀው ።

« ቀድሞ ከዚህ ወገን ስንት ጥርሶች ነበሩዎት »?

« አራት ነበሩኝ ሲል መለሰ ዶን ኪሾት « ያውም የአእ ምሮ ጥርሴን ሳልቆጥር ነው ። የቀሩት ግን በሙሉ ከነጤናቸው እንዳሉ ናቸው » ።

« ደህና አድርገው ያስታውሱና ይቁጠሩት » ሲል መከረ ሳንቾ ።

« አምስት መሆናቸው ቢቀር አራት ናቸው እያልኩህ «ሲል መለሰ ዶን ኪሾት »

« ከተወለድኩ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ አንድም ጥርስ ተነ ቃንቆብኝ አላስወለቅሁም ፣ አንድም ጥርስ አውቆ አልተነቀ ለብኝም ፣ ሌላው ቀርቶ ብልዛትም ሽርፍታም ነክቶኝ አያው ቅም ጥርሶቼ ሁሉ ክክ እንደመሰሉ ተደርድረው ነበር ።

« በደንብ ቆጥረው ይንገሩኝ ያልኩበት ምክንያት ሲል ማስረዳት ጀመረ ሳንቾ በዚህ በታችኛው በኩል እኔ እንደማ የው ከሁለት ጥርስ ተግማሽ በስተቀር ሌላ የለምትም ። በላይ ኛው በኩል ደግሞ ግማሽም ሙሉም ስለሌለበት የሚታየው እንደመዳፍዎ የዳለጠ ድድ ብቻ ነው አለው ።

« ወይኔ ያልታደልኩት » አለ ዶን ኪሾት ይህን የሚያ ሳዝን መርዶ ከጋሻጃግሬው እንደበት በሰማ ጊዜ « ጥርሴን ከሚ ያወልቁብኝ ጐራዴ የምጨብጥበትን የቀኝ ክንዴን አይሁን እንጂ የግራውን ክንዴን ቆርጠው በወሰዱት ኖሮ ይሻ ለኝ ነበር ። ማኘኪያ ጥርስ የሌለው አፍ መጅ እንደሌ ለው ወፍጮ የሚቆጠር ነው ። ካንድ አልማዝ ይልቅ አንድ ጥርስ የበለጠ ዋጋ እንዳለው ሊገመት ይገባዋል ። መቸስ ምን ይደረጋል ፣ የዙዋሪ ፈረሰኝነትን ጠንካራ ሕግ የምንፈጽመው ሰዎች ሁሉ ይህን የመሰለውንም ጉዳት ለመቀበል ምንጊዜም ቢሆን የተገደድንና የተጋለጥን ነን ። ወዳጄ ሳንቾ ሆይ በል እን ግዲህ አህያህ ላይ ውጣና መንገዱን ምራኝ ። እኔም እንተ በፈ ለግኸው እርምጃ እከተልሃለሁ አለው ።

ሳንቾም ይህንኑ ትዕዛዝ በመፈጸም አህያው ላይ ተቀመ ጠና ከአውራው መንገድ ሳይወጣ ማደሪያ ቦታ ለማግኘት የሚ ቻል መስሎ በታየው አካሄዱ ጉዞውን ቀጠለ ፤ ይህም መንገድ በዚያን ሰዓት ብዙ መንገደኞች የተመላለሱበት መሆኑን የሚያ ስረዳ ትኩስ ዱካ የታየበት ነበር ። ሆኖም ለዶን ኪሾት የመን

ጋገዎቹ ሕመም ሩታም ሆነ የመቸኮል ፍላጐት ስላልሰጡት በዚህ ምክንያት ጌታ ከኋላ ጋሻ ጃግሬ ከፊት ሆነው በጣም ዝግ ባሰ እርምጃ እያዘገሙ በሚሄዱበት ጊዜ ሳንቾ ይህን የሚያበ ሳጭ እዶጋ ለማስረሻ ለጊዜ ማሳለፊያ ፤ ጌታውን ለማበረታቻ የሚሆን ልዩ ልዩ ወሬዎች እያመጣ ሲያጫውተው ፈለገ ። ከወ ሬዎቹም ውስጥ የመጀመሪያው ከዚህ በሚቀጥለው ምዕራፍ ላይ የሚተረከው ነው ።

ምዕራፍ 19

ዶን ኪሾት ከጋሻ ጃግሬው ጋር በጨለማ ሲጓዝ ካንድ ሬሳ ጋር ተጣናኝቶ ያከናወነው ግጥሚያና እንደዚሁም ስለ ሴሎች ልዩ ልዩ አስደናቂ ሁኔታዎች ሳንቾ ፓንቻ ለጌታው ያደረገው ቁምነገር የሞላበት ንግግር ይተረካል ።

ሳንቾ ፓንቻ እርምጃውን በመቀጠል እንዲህ ሲል ወግ አመጣ ። « የተከበሩት ጌታዬ ሆይ ! እኔ እንደሚመስለኝ በነ ዚህ ቀኖች ውስጥ የደረሱብን አደጋዎች ሁሉ ከክቡርነትዎ የፊ ረሰኛነትን ሕግ አፍርሰው ለሠሩት ኃጢአት የተጣሉ መቀጫ ዎች መሆን አለባቸው እላለሁ ። ምክንያቱም ያስታውሱት እን ደሆነ ባለፈው ጊዜ ሲናገሩ እንደሰማሆት ያንን ማሳንደሪና ወይም ማንትስ እንዳሉት እንጂ በውል አላስታውሰውም የዚ ያን የሳረቡን የራስ ቁር ማርከው እጅዎ ከማግባትዎ በፊት በተ ሠናዳ ገበታ ላይ ቀርበው ዳቦ ላይበሉ ፥ በተነጠፈ አልጋ ላይ ላይተኙ ፤ ከንግሥት ጋር ላይጨዋወቱ ፥ ከዚህም በስተቀር በዚ ያኑ ጊዜ ምንም ቢሆን ከቶ አላደርገውም ያሉትን ሌላውንም ድርጊት ሁሉ ላያደርጉ የማሉትን መሐላ አክብረው ባለመጠ በቅዎ ነው ።

ዶን ኪሾትም መለሰ እዚህ ላይ እውነት አልህ ፥ ሳንቾ ፥ ጸሩ ግን እውነተኛውን ስነግርህ የማልኩት መሐላ ሁሉ ከሃ ላቤ ውስጥ በመውጣቱ በሞራሽ ዘንግቼው ነበር ። ባንተም ላይ የብርድልብሱ ጉኖሽ ሊደርስብህ የቻለው ስለአንድ ጉዳይ መሣ ሌን እያወቅህ እንዳልረሳው በየጊዜው እየጐተጐትህ ሳታስጠ ነቅቀኝ በመቅረትህ መሆኑን ለማረጋገጥ ትችላለህ ። ይሁን እንጂ በፈረሰኛነት ትእዛዛትና ደንቦች ውስጥ በያንዳንዱ አንቀጽ ላይ

የሚያርሰውን የተጣመመ ጉድለት እያቃኑ ለማረም የሚረዳ ዘዴ ስለማይታጣ ይህ ከመዘንጋት የመጣ ጉድለታችን የሚሻሻል በትን መንገድ ለማግኘት እንደምችል ተስፋ አደርጋለሁ ። አለው

ሳንቾም በመገረም እንዲህ ሲል ጠየቀ ፥ «ጌታዬ ሆይ ! ይቅርታዎን ያድርጉልኝና እረ ለመሆኑ እኔን በዚህ መሐላ ውስጥ የሚያገባኝ ነገር ኖሯልን? ምናልባት ደግሞ ስላንዳች ጉዳይ ስምል ሰምተውኝ ይሆንን አለው ።

« ያንተ አለመማል በውነቱ ቁምነገር የለውም » አለ ዶን ኪሾት ምክንያቱም ከጓላዬ እንደጅራት ተጣብቀህ ከኔ ጋር የምትዞር ስለሆንክ በዚህ የተነሳ የመሐላው ተካፋይ መሆን አለብህ ። ስለዚህ ለኔ የመጣው ዳፋ ሁሉ ላንተም የተረፈ ከደ ጉም ሆነ ከክፉው ድርሻህን ከማግኘት በአባሪ ተባባሪነት ተከ ስሰህ ከመቀጣት ለመዳን አትችልም ። የሆነው ሆኖ ለአሁኑ የሚበጀን ክርክሩን መተውና የስህተታችን ማረሚያውን ዘዴ ፈልገን ማግኘት ነው ።

ነገሩ እንዲህ ከሆነማ « አለ ሳንቾ አደራውን ጌታዬ ከዛሬ ጀምረው የማሉትን መሐላ ሁሉ እንደገና መላልሰው ያስታው ሱት ፥ ለወደፊቱም እንዳይረሱት ይጠንቀቁ ፤ ምናልባት መሐ ላው ያልተዘነጋ እንደሆነ እነዚያ የተረገሙት ቄራቆች ዳግመኛ በኔ ላይ ለማላገጥና በትከሻዬ ላይ ለመጨፈር የሚኖራቸው ፍላጐት ይወገድላቸው ይሆናል ፤ በርስዎም ላይ ቢሆን የመተናኮያ ሰበብ ሲያጠብዎ ይተውዎታል አለው ።

እንግዲህ ከብዙው በጥቂቱ ይሆን እየተባባሉ ሲጓዙ በመ ንገዳቸው ላይ ቀኑ ስለጨለመባቸው የሚያድሩበትን ሥፍራ ለማግኘትም ሆነ ለማወቅ የነበራቸው ተስፋ ያመነታ ጀመር ። የባሰውን ደግሞ ሁኔታቸውን ይበልጥ ያከፋው ረሃቡ እየሞረ ሞረ ሊገድላቸው መድረሱ ስለሆነ ምን ለማድረግ እንደሚችሉ ግራ ገብቷቸው ተጨንቀው ነበር ። ምክንያቱም የውዲሳው ቦርሳ ከጠፋ ወዲህ ከስንቅ ጋር ተሰነባብተዋልና ነው ። በዚህም በሚ ገኙበት ችግር ላይ የሚጐድለውን ችግር ለመሙላት ሲል አሳ ረኛው ዕድላቸው ሌላ አደገኛ አጋጣሚ ፈልጐ አቀረበላቸው ።

ይህም የተገኘው አጋጣሚ በዚያን ጊዜ በከበባቸው ጨለማ ውስጥ ሆነው በሩቁ ሲያዩት የአደገኛነቱን ብርቱነት ለማረጋገጥ አን ዳች ማሰብና መጨነቅ ሳያሻ እውነተኛ አስፈሪ አጋጣሚ መስሎ ይታይ ነበር ።

ጊዜው ወደ መንፈቀ ሌሊቱ በተቃረበ ቁጥር ጨለማው እያደር እየደነጐረ ይሄድ ጀመር ። ይህም ሆኖ ይህ የሚጓዙበት መንገድ አውራ ጐዳና በመሆኑ ምክንያት በሳንቾ አስተያየት ከዚህ ከአለበት ነጥብ አንስቶ ግፋ ቢል ካንድ ወይም ከሁለት ምዕራፍ ጉዞ በኋላ ወደ አንድ የመንገድ ዳር ሆቴል ቤት ለመ ድረስ እንደሚቻል ገምቶ ነበርና በመጨረሻ ተስፋቸው እየተጥ ናኑ ጉዞአቸውን ቀጥለው ነበር ። ይሁን እንጂ በዚህ አካኋን በደነጐረው ጨለማ ውስጥ እየተደናበሩ ጋሻ ጃግሬው በረሀብ እን ደጠወለገ ፥ ጌትዬውም መብላት እንዳስከጀለው ሆነው በሚንጠራ ወዙበት ጊዜ በዚያው መንገድ በስተፊታቸው በኩል የብዙ ተወር ዋሪ ከዋክቶች ብርሃን የሚመስሉ እያሌ የችቦ መብራቶች በሚያስደ ነግጥ ሁናቴ እየተንቦገቦገ ወደነሱ ሲመጣ አዩ ። ሳንቾ ይሀን ትር ዒት አሻግሮ በተመለከተ ጊዜ ከመደንገ ጡ የተነሳ እንደሕፃን ልጅ ባብቶ እንደፈዘዘ ቀረ ። ዶን ኪሾትም በወትሮው የፀ ጥታ ስሜቱ ላይ ነበር ለማለት አያስደፍርም ነበር ። ይህም ሆኖ እንደኛው የአህያውን ሉኮ ስቦ ሁለተኛውም የፈረሱን ልጓም ጐትቶ ከቆሙ በኋላ ይህ ወደነሱ የሚመጣው መብራት ምን ለመሆን እንደሚችል ለማወቅ በጥንቃቄ ይመለከቱ ጀመር ። መብራቶቹ ወደእነሱ እየተቃረቡ በመጡ ቁጥር የብርሃናቸው ውጋጋን እያደር እየነገሠ ይታያቸው ነበር ። ሳንቾ ይሀን ቃጠሎ እንዳየ ወዲያውኑ የእንቅጥቅጥ በሽታ እንደለከፈው ሰው ሰው ነቱ ይርድ ጀመር ። ዶን ኪሾትም እንደተቆጣ አንበሳ የአራሱ ጠጕሮች ሲቆሙ ተሰማው ። ቢሆንም ልቡን አደፋፈረና ሳን ቾን እንዲህ አለው ።

ሳንቾ ሆይ ! ይህ የቀረበልን አጋጣሚ ያላንዳች ጥርጥር በጣም ታላቅና በጣምም አደገኛ አጋጣሚ መሆን ስላለበት ድፍረቱ ንና ኃይለኝነቴን ሁሉ አጠቃልዬ እዚህ ላይ አጋፍጬ ማሳየት ይገባኛል ።

«ወይኔ ያልታደልኩት» ሲል አቅማማ ሳንቾ ይህ አጋጣሚ ምናልባት እንደዚያን ሰሞኑ ያሰ የሚከናወን እንደሆነ መቸም በአመጣጡ እንደሚታየው ይሽው የጭራቆች መስሎ ታይቶኛል እና ፤ እርግጫውንና ጡጫውን የምንችልበት ትርፍ ታፋና ጀርባ ማን ያበድረኝ ይሆን ? የኛው እንደሆነ ሰሞኑን ተወቅጦ ስለደቀቀ ለዛሬው እንደማይበቃ እርግጠኛ ነኝ ። ወዮልኝ ይብላኝ አለ ።

«ጭራቆችም ሆኑ ወይም ብራቆች» ሲል መለሰ ዶን ኪሾት እኔ በመጀመሪያው ግጥሚያ ላይ ተመትቼ ካልወደቅሁ በስተ ቀር በሕይወቴ ቆሜ እያለሁ የፀጉርህን አንዲቷን ዘለላ እንኳ እንደማላስነካብህ እመነኝ ። ይህንንም የምልህ ባለፈው ጊዜ አንተ ስትልፈሰፈስ ከኔ ተለይተህ ወደኋላ በመቅረትህ ጭራቆቹ ብቻ ህን አግኝተው ሊጫወቱብህ የቻሉት እኔ የመስኩን አጥር ጥሼ ወይም ዘልዬ ለማለፍና ለእርዳታ ልደርስልህ ባለመቻሌ ነው ። አሁን ግን ሁላችንም የምንገናኝበት ሥፍራ አንዳች የሚያግድ አጥር የሌለበትና ጐራዴዬንም እንደልቤ ወዲያና ወዲህ ለመ ሰንዘር በምችልበት በጠራ ሜዳ ስለሆነ ፤ በፍጹም ቅንጣት ሥጋት ሊኖርህ አይችልም አለው ።

ሳንቾም እንዲህ ሲል ጠየቀ «ባለፈው ጊዜ እንደደረሰብዎ ሁሉ ያበሰኝ በምትሐታቸው ኃይል አፍዝዘው ያደነዝዙዎት እንደሆነ እጅና እግርዎ ሽባ ሆኖ ተጣትረው ሲቀሩ በገላጣ ሜዳ ላይ መገኘትዎና አለመገኘትዎ ለምን ጉዳይ የሚረዳዎ ይመ ስልዎታል ? አለው» ።

ሰማኝ ሳንቾ «አለ ዶን ኪሾት» በማናቸውም ረገድ እንግ ዲህ ተመልሰህ እናትህ ሆድ አትገባምና አይዞህ አትፍራ ልብ ህን ጥቂት ደፈር አድርገው ፥ አሞትህም ቆጣ ይበል ከዚያም በኋላ በግጥሚያው ሰዓት እኔ ምን ያህል ጀግንነት እንዳለኝ ፈተና ውን ታየዋለህ ። ለአደጋም አጣጣል ውድቀት ሌሊት ምቹ መሆኑን ግንንም ጠይቅ አለው ።

«ደግ ነው አለ» ሳንቾ» መቸስ ወዴት እደርሳለሁ በትክክል ለኛነቴ ተግምኜ ግጥሚያውን ለማየት ያህል እንኳ ዓይኔን እን ድገልጥ ከረዳኝ ማየቴ ወዴት ይቀራል ።

ከዚህም በኋላ ሁለቱም ከመንገዱ ጐራ ብለው የእነዚያ የሚንቀሳቀሱት መብራቶች ምስጢር ምን ለመሆን እንደሚችል ለማጣራት እንደገና በጥንቃቄ መመልከት ጀመሩ ። ከጥቂት ቆይታም በኋላ ነጫጭ ካባ የለበሱ ብዙ ሰዎች ታዩዋቸው። ይህም አስደንጋጭ ትርዒት የሳንቾን ነፍስ በሙሉ ስለ አሻከረው አርባ ቁጥር ትኩሳት እንደያዘው ሰው ጥርሶቹ ይንቀጫቀጩ ጀመር ፤ መንቀጫቀጩም እየበረታበት የሄደው የመጪዎቹ ሁኔታ ተገልጦ በውል ከታየ በኋላ ነው ። ይኸውም ሃያ የሚሆኑ ካባ ለባሾች ሁሉም በበቅሎ ተቀምጠው የተቀጣጠለ ችቦ ይዘው የሚመጡ ነበሩ ። ከነሱም በስተጀርባ በጥቁር የከል ጨርቅ የተሸፈነ አንድ ቃሬዛ ነበር ። ይህንንም ቃሬዛ በበቅሎ የተቀመጡ ስድስት ሰዎች እስከ በቅሎዎቻቸው ኩቴ ድረስ የተንዘረፈፈ ጥቁር የሐዘን ጨርቅ የለበሱ ስድስት ሰዎች ግራና ቀኝ አጅበውት ነበር ። የተቀመጡባቸውም ከብቶች በቅሎዎች መሆናቸው የታወቀው በአካሄዳቸው ዝግታና ዳተኛነት ነው ። ካባ ለባሾችም እርስ በእርሳቸው እየተቀባበሉ ዝቅ ባለ አጉረምራሚ ድምጽ ሥርዓተ ፍትሐት እያደረሱ ይንዙ ነበር ።

በዚያ በውድቅቱ ሌሊትና በዚያ ጭው ባለው በበረሃ ቀበሌ የሚታየው ይህ ልዩ የሆነው ትርዒት በጌታውና በተለይም በጋሻጃግሬው ልብ ውስጥ ተቅማጥ የሚያስመጣ ፍርሐት ለማሳደር ያህል በቂነቱ ከመጠኑ በላይ ነበር ።

ምንም እንኳ ዶን ኪሾት በእኳኋኑ ፍርሐት ያደረበት መሆኑን ለመግለጥ ባለመፍቀዱ ጨክኖ ቢግደረደር የሳንቾ ፖንቻ ድፍረት ሁሉ ገና ድሮ እንደ በረዶ ማሙቶ ውሀ ሆኖ ማለቁ ተረጋግጧል ። ዶን ኪሾት ግን ስሜቱ አፍራሻውን ሆኖ በመገኘቱ በዚያን ሰዓት በቅዠት አስተያየቱ እንደሚመለከተው የተጨበጠ እውነት አድርጐ የገመተው ይህ የሚመጣው አጋጣሚ በዚያ ባነበበው የፈረሰኞች ታሪክ መጽሐፍ ላይ ተደረገ ተብለው በሚ ተረክው ዓይነት እና መልክ ሆኖ የሚታይ መሆኑን ነበር ። ይህን ግምት መሠረት በማድረግ በዚያ በቃሬዛው ውስጥ ተኝቶ የሚገኘው ክፉኛ የቆሰለ ወይንም የሞተ ፈረሰኛ መሆኑን አሰበ ። እንዲሁም ደግሞ የዚህን ፈረሰኛ ደም ለመበቀል የቀረበው ግጥ

ሚያ በተለይ ለሱ ብቻ የተወሰነ መሆኑን አመነ ። ስለዚህ ብዙ ሐተታ ሳያበዛ ጦሩን ዘቀዘቀና በኩርቻው ላይ ተመቻችቶ ተቀመጠና በቁርጠኝነትና በቀልጣፋነት መንፈስ ፈረሱን እያራመደ ሄደ ። እነዚያ ካባ ለባሾች በግዴታ ለማለፍ በሚመጡበት መንገድ መካከል ቆሞ ጠበቃቸው ።

ሰዎቹ እየቀረቡ መጥተው አጠገቡ መድረሳቸውን ካየ በኋላ ድምጹን ከፍ አድርጐ እንዲህ ሲል አስጠነቀቃቸው ። የሴሊት ዙዋሪ ፈረሰኞች ሆይ! ሁላችሁም ባላችሁበት ሥፍራ ቁሙ ፥ ማንኛችሁም ብትሆኑ ሳትነቃነቁ እዚያው እንዳላችሁ ማን እንደሆናችሁ ፥ ከወዴትስ እንደምትመጡ ወዴትስ እንደምትሄዱ ፥ በዚያ በቃሬዛው ውስጥ የተሸከማችሁት ማንን እንደሆነ በዝርዝር አስታውቁኝ ። ለኔ እንደሚመስለኝ ግን ሁኔታችሁ የሠላም ወይም የጠብ መሆኑ ስለማይለይ ፥ ምናልባት እናንተ በሌሎች ላይ የግፍ ሥራ ሠርታችሁ በጨለማ ውስጥ ተደብቃችሁ ለማምለጥ የምትሞክሩ ሰዎች እንደሆናችሁ ወይም ደግሞ ሌላ ሰው በእናንተ ላይ የግፍ ሥራ ሠርቶባችሁ በብርሃን መንገድ እንዳትሄዱ ከልክሏችሁ እንደሆነ ከሁለት አንዱ ሳይሆን አይቀርምና ምስጢሩን አብራርታችሁ ልትነግሩኝ ይገባችኋል ። ምክንያቱም የፈረሰኝነት ተግባሬ እንደሚፈቅድልኝ አጥፊዎቹ እናንተ እንደሆናችሁ የሚገባችሁን ቅጣት ለመስጠት ፥ ወይም ደግሞ ሌላ ሰው በድሏችሁ እንደሆነ እሱን ተከታትዬ ልበቀልላችሁ እንድችል በቂ የሆነ ማስረጃ ከናንተ ዘንድ ለማግኘት እፈልጋለሁና በፍቅርና በሰላም ንገሩኝ አላቸው ።

ከካባ ለባሾች መካከል ወደፊት ቀደም ብሎ የቆመው አንደኛው ሰው እንዲህ ሲል መለሰለት ። እኛ በአካሄዳችን መቻኮል እንደሚያዩት ወደሰፈር ለማድረስ በጣም ተጣድፈናል የምናድርበት ሆቴል ሩቅ ስለሆነ ይህን የተጠየቅነውን አስረጂ መልስ ለመስጠት ስንል እዚህ ተግተረን የምናባክነው ትርፍ ጊዜ አናገኝልዎትምና እርስዎም በፍቅርና በሠላም መንገዱን ይልቀቁልን ካለው በኋላ በቅሎይቱን ኮረኮረና ወደፊት ጥሎ ለማለፍ መጣ ።

ዶን ኪሾትም በዚህ ጕምዛዛ በሆነ መልስ በመደፈሩ የንቀት ሁኔታ ስለተሰማው የበቅሎይቱን ልጓም አፈፍ አድርጕ የተናጋሪውን እርምጃ ከዳኘ በኋላ እንዲህ አላቸው ።

« ኋላ አይሆንም ቁሙ ብያለሁ ፣ ትሁታንም ሁኑ ፣ ለጠ የቅኋችሁ ጥያቄ ተገቢውን መልስ ስጡኝ አለበለዚያ ግን ሁላ ችሁንም ለግጥሚያ ጋብዣችኋለሁ ።

ለተንኮሉ ደግሞ በቅሎይቱ ደንባራ ቢጤ ኖራ የልጓሟ መያዝ በጣም ስለአስበረገጋት የፊት እግሯን ሽቅብ አነሳችና ጌታዋን ከኮርቻው ላይ አሽቀንጥራ ወደመሬት ጣለችው ። በዚ ህን ጊዜ በእግሩ ይሄድ የነበረው እንደኛው አሽከር ካባ ለባሹ ባጉል ሁኔታ መውደቁን በተመለከተ ጊዜ በዶን ኪሾት ላይ የስድብ መዓት ያወርድበት ጀመር ።

ዶን ኪሾትም ከቅድሙ አንስቶ በቁጣ ላይ ነበርና ይህ ስድብ ተጨምሮ ቁጣውን ይብስ ስለአጋለው ጦሩን ዘቀዘቀና ሴላ ድጋሚ ማሰጠንቀቂያ ሳይሰጥ እንደኛውን ባለጥቁር ካባ ወግቶ ክፉኛ አቁስሎ እመሬት ላይ ዘረረው ። ቀጥሎም ወደ ሴሎቹ ዞረና መካከላቸው ገብቶ እየጓጮጠ ያተራምሳቸው ጀመር ። በምን ያህል ፍጥነትና በምን ያህል ቅልጥፍና እየዋከበ እንደሚያ ስፈረጥጣቸው ለማየት በእውነቱ እዚያው አቦታ ላይ መገኘት የሚያስፈልግ ነበር ። በተለይም ደግሞ በዚያን ሰዓት ሮንዜና ንቴ እንደነፋስ ሲሮጥ ለተመለከተው ሰው የፍጥነቱ ብዛት በኮ ቴዎቹ ላይ ክንፍ ያበቀለ ይመስል ነበር ።

ካባ ለባሾቹ ሁሉም ጀሌዎችና ወዲህም ግርግር የማይወዱ የገዳም ሰዎች ስለነበሩ እንዳች መለመን ሳያስፈልጋቸው በቶሎ የጦር ሜዳውን ለቀቁለትና እነዚያን በቡሔ ሌሊት የሚጨፍ ሩትን ጕረምሳዎች ይመስል የችቦአቸውን መብራት ከነፋስ ጋር እያውለበለቡ ቀሚሳቸውን ከፍ ከፍ አድርገው በማይገታ ፍጥነት በእርሻው መካከል ተፈተለኩ ። እነዚያ ጥቁር ሰናፍል የለበሱት ደግሞ ተከታትለው በሚሸሹበት ጊዜ እስከተረከዛ ቸው በተንዘረፈፈው መቀነታቸው በመጠቅለላቸውና በመጠ ምጠማቸው የተነሳ እየተወላከፉ እንኳንስ እሮጠው ለማምለጥ

ቀርቶ መላወስ ስለአቃታቸው ሞገደኛው ዶን ኪሾት አንዳች ተከላካይ እጅ ሳያግደው ቅድም እንደተናገረው እጁን በነፃነት ወዲያና ወዲህ እየሰነዘረ ቀሳውሶቶቹን በሶሩ ዛቢያ እየጀለጠ እነሱንም ያለውዱታቸው የጦሩን ሜዳ ለቅቀው እንዲሄዱ አስ ገደዳቸው ። ካባ ለባሾችም ሁሉ ይህን በድንገት የወደቀባቸ ውን አደጋ በተመለከቱ ጊዜ ያንን በቃሬዛው ላይ የሚገኘውን ሬሳ ነጥቆ ለመውሰድ በክፋቱ የለየለት ተንኮለኛ የመጣባቸው መሰላቸው እንጂ በውነቱ ከሰው የጭካኔ መንፈስ የመነጨ ያደጋ አጠጣል ዘዴ መስሎ ስለአልታያቸው በእንቆቅልና በእን ብርክክ እየዳሁ የተወቁበትን አውድማ ለቀውለት ሸሹ ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ሳንቾ የአህያውን ጆሮ ግንድ ተገን አድ ርጕ ቆሞ የጌታውን ዲና ጣይነትና ጀግንነት እያደነቀ በመመ ልከት ብቻውን እንዲህ ይል ነበር ።

« ለካንስ ይህ የኔ ጌታ የማንቻው ዶን ኪሾት እርሱ እራሱ እንደሚለው በጉራ ብቻ ሳይሆን እውነትም ደፋርና ጀግና ኖሯል።

ዶን ኪሾት ነጋዴዎቹን አባርሮ ሲመለስ መጀመሪያ ከበ ቅሎይቱ ላይ ተገልብጦ የወደቀው አንደኛው ካባ ለባሽ አንድ እግሩን እርካብ ጠልፎት ሁለተኛው እግሩ በኮርቻው መሃል ተሰንቅሮ ከበቅሎይቱ ጋር እንደወደቀ የያዘውም ችቦ እስከዚያን ሰዓት ድረስ እንደበራ ይታይ ስለነበር ዶን ኪሾት በዚህ መብራት ብርሃን እየተመራ መጥቶ አጠገቡ ደርሶ ሰውዬውን ከአየው በኋላ ባንድ አፍታ ከፊረሱ ላይ ዱብ ብሎ ጀርባው ላይ ተከ መረበትና የአንካሴውን ጫፍ እፊቱ ላይ ደግኖ እንዲህ ሲል ጮኸበት ። ነፍስህን ትመርጥ እንደሆነ ተማረክ ፣ አለበለዚያ ግን ገደልኩህ አለው ።

ወዳቂውም እንዲህ ሲል መለሰለት ፣ ከዚህ ይበልጥ ምር ኮኛ ለመሆን አልችልም ፣ ምን ዓይነት መማረክ ነው የሚጠ ይቁኝ አንዱ ቅልጥሚ ስለተሰበረ ለመነቃነቅ እንኳ አልሆነል ኝም ። ይልቁንስ በእውነት ፈረሰኛ እንደሆኑ ነፍሴን እንዲያተ ርፉልኝ ክቡርነትዎን ተማጥኜዎታለሁ ። በተረፈ ግን እኔ እንድ

ካህን ስለሆንኩ የገደሉኝ እንደሆነ ይቅርታ የማይደረግለት ሠረይ ከባድ ጥፋት መሥራትዎን ይወቁ አለው ።

ዶን ኪሾትም እንዲህ ሲል ጠየቀው ፥ የቤተ ክህነት አገልጋይ ከሆኑ እዚያው ቤተ ክርስቲያን መጸለይዎን ትተው የምን ዲያብሎስ ነው እየነዳ በዚህ ሰዓት እዚህ ስፍራ ያመጣዎት? ያም መለሰ ። የነዳኝማ መጥፎው ዕድሌ ነው አለው ።

«ይጠንቀቁ አለ ዶን ኪሾት ፥ የተዛተብዎ አደጋ ከቅድመ የባሰ ብርቱ ስለሆነ በመጀመሪያው ጊዜ ላቀረብኳቸው ጥያቄዎች ሁሉ የሚያጠግብ መልስ ካልሰጡኝ በስተቀር ፥ ያልኩትን ማድረጌን» ነው አለው ።

« ማናቸውንም ሁኔታ ባጭር ቃል ስነግርዎ ከቡርነትዎ ለጠየቁት ሁሉ የሚያጠግብ መልስ በቀላሉ ሊያገኙበት ይችላሉ» አለው ። ካህኑ ንግግሩን በመቀጠል «ምንም እንኳ ቅድም በድንጋጤ መንፈሴ ተሸብሮ ካህን ነኝ ብልዎት ካህንነቴን አፍርሼ ደብተራ ከሆንኩ ሰንብቻለሁ ፥ ስሜም ያብተራ አሎንሶ ሎፔዝ ይባላል ፥ ተወላጅነቴም በአልኮቬንዳንስ አውራጃ ነው ። የመጣሁትም ከነዚያ ከነችበአቸው ከሸሹት አስራ አንድ ቀሳውስቶች ጋር ከቦይዛ ከተማ ነው ። የምንሄደውም እዚያ ቃሬዛ ላይ የተጋደመውን አፅም ይዘን ወደ ሲጐቪያ ነው ። ይህ ሟቹ በአገራችን የታወቀ ጀግና ፈረሰኛ ነበር ። በድንገት ቦዬዛ ላይ ሞቶ ለጊዜው እዚያው ተቀብሮ ሲኖር አሁን ደግሞ እንደነገር ኩዎት ሴጐቪያ የተወለደበት አገር ስለሆነ እዚያ አድርሰን ከቤተሰቦቹ መቃብር ጐን ለመቅበር እንደሚያዩን ሆነን ስን ነገ ይህ አደጋ ወደቀብን አለው ።

«ለመሆኑ ማን ናፖል የገደለው» ሲል ዶን ኪሾት ጠየቀ ።

«ደብተራውም መለሰ» የሞተበት ምክንያት በብጫ ወባ ተቀሰፎ ነው ገዳዩ ግን እግዚአብሔር መሆኑ ነው» አለው ።

«አሚሚቱ እንዲህ ከሆነማ» ሲል ዶን ኪሾት ተግባባ ። « መቸም ሌላ ሰው ገድሎት ቢሆን ኖሮ ደሙን ሳልበቀልለት አልቀርም ነበርና ጌታችን የዚህ ሰው ሞት ለመበቀል ስል ማድ

ረግ ከነበረብኝ ድካም አዳነኝ ማለት ነው ። ዳሩ ግን የገደለው እጅሬ ስለሆነ አፈን ዘግቼ ዝም ከማለትና እንቴን ከማቀርቀው ሌላ ምንም ለማድረግ አልችልም ። ምክንያቱም እንኳንስ ሌላ ሰው በመገደሉ ልቆጣው ይቅርና እኔንም ቢገድለኝ ኖሮ ከዚህ ይበልጥ መኩራመት ስላለብኝ ነው ። የሆነው ሆኖ ያካሄዳችሁ ምክንያት ከተገለጠልኝ ወዲህ እጄን በቤተ ክህነት ሰዎች ላይ በማሳረፌ በውነቱ ልቤ በሃዘን ሳይነካ አልቀረም ። ይሁን እንጂ ያለፈው አልፏልና ላሁን ብፁዕነትዎ እንዲያውቁልኝ የምሻው እኔ ዶን ኪሾት የምባለው የማንቻው ፈረሰኛ መሆኔንና ተግባሬና ግዳጂም በዓለም ዙሪያ እየተዘዋወርኩ አጋጣሚዎን መፈለግና ጠማማዎችን ማቅናት ጉዳትን መጠገን መሆኑን ነው ። ደብተራው እንዲህ ሲል መለሰ ፥ ጠማማዎችን ለማቅናት የሚችሉት በእንዴት ያለ አኳኋን እንደሆነ በውነቱ ምስጢሩ ሊገባኝ አልቻለም ። እኔ ቅድም ቀጥ ብዬ የነበርኩትን አሁን ጠማማ እንድሆን አድርገውኛል ። ይህንንም ማለቴ እንዱ እግሬ እንዲሰበር ምክንያት ስለሆኑብኝ ምን ጊዜም ቢሆን ተመልሶ ሊቃና እንደማይችል እርግጠኛ በመሆኔ ነው ። ጉዳትን በመጠገን ረገድ ደግሞ እኔን እስከ ሕይወቴ ፍጻሜ ድረስ እንደተጐዳሁ በምቀርበት አኳኋን ጐድተውኛል ። ስለዚህ አጋጣሚ ፍለጋ ከሚዞሩት ከክቡርነትዎ ጋር መገናኘቴ በኔ ላይ የቴን ያህል የከበደ አደጋ እንደ ጣለብኝ በሁኔታዬ ሊረዱት ይችላሉ አለው ።

ዶን ኪሾትም መለሰ « ወዳጄ ደብተራ አሎንዝ ሎፔዝ ሆይ» አንዴ ይስሙኝና ልንገርዎት ፥ ጉዳዮች የተባሉት ሁሉ ባንድ ዓይነት አቅድ ተመርተው አይፈጸሙም ። የዛሬውን ሁኔታ ወደ እደ ገኛ መልክ የለወጠው ይህ የሴሲት አመጣጣችሁ መሆኑን ይመኑኝ ። በዚህ አኳኋን በጥቁር ካባ ተጠቅልላችሁ የተቀጣጠሉች ችቦ ፥ እያውለበለባችሁ ፤ እንደዚያ እያጉረመረማችሁ ፤ የሀዘን ከል ለብሳችሁ ፥ በሴሲት ስትሄዱ ላያችሁ ሁሉ መጥፎ መንፈስ የሚያሳድርበት ስለሆነ ፤ አምሳያችሁ የልቡን ክፋት ወይም ደግሞ የሌላ ዓለም ልዩ ፍጥረቶች እንጂ የዚህ ዓለም ሰዎች መሆና ናችሁን የሚያምን ከቶ አይገኝም ነበር ። ስለዚህ እኔም ባየኋችሁ ጊዜ ይኸው መንፈስ ያደረብኝ በመሆኔ ምክንያት ተግባሬን ለማንደል ስላልቻልኩ በቀጥታ ላጠቃችሁ ተገደድኩ ። እስካ

Pdf by Meysor Bro(Ppp)

ሁንም ድረስ እንደገመትካችሁ ሁሉ እውነተኞቹ የክፋት ምን ጮች መሆናችሁን አረጋግጩ ባውቀውም ኖሮ ያለ ጥርጥር ሳላንኩታችሁ አልቀርም ነበር ።

« መቼም » አለ ደብተራ « ገደቢሱ እጣዬ እዚህ አደጋ ላይ እንድወድቅ እንዴ ፈርዶብኛልና የዛሬውን ቀን በማናቸ ቸውም አካሏን ላመልጠው አልችልም ነበር ። አሁንም ጌታው ዙዋሪ ፈረሰኛ መልካም ፈቃደዎ ይሁንና ከዚህች በቅሎዬ ስር እንድወጣ ይርዱኝ ። አንዱን እግሬን በእርካቡና በኩርቻው መካ ከል አጣብቃ ስለያዘችኝ ብቻዬን ለመላቀቅ አቅቶኛል አለው ።

«እኔ እርስዎን ብሆን ኖሮ» ሲል ዶን ኪሾት በማፌዝ መለሰለት «ይህን እርዳታ ለመጠየቅ እስከ ነገ ጡዋት ድረስ እጠብቅ ነበር ፣ ለመሆኑ ነገሩ ከታወቀ ወዲህ እርዱኝ ለማለት እስከዚህ ሰዓት ድረስ መቆየት ያሻ ኖሩዋልን? ይህን ከተናገረ በኋላ ለእርዳታ ፈጥኖ እንዲደርስ ሳንቾን ጠራው ። ሳንቾ ግን ለጊዜው ጥሪውን ሰምቶ መልስ ለመስጠት ፋታ አላገኘም ነበር ። ምክንያቱም ፣ እነዚያ የተባረኩ ሰዎች የመንገድ ስንቃቸውን በደንብ አሰናድተው ጭነው በስተኋላቸው ያስከተሉትን አጋሰስ አግኝቶ እሱን ከመንገድ አግ ልሎ ቀርቃባውን ፈትቶ አገልግል በመበዝበዝ ሥራ ተወስኖ ስለነበረ ነው ። ስለዚህ ባናውን መሬት ላይ አንጥፎ ከሞኑቱ ውስጥ ጠቃሚ ሆኖ ያገኘውን ሁሉ አራግፎ ባናው ለመያዝ የቻለውን ያህል አንሰቶ በአህያው ላይ ከጫነ በኋላ ጌታው የተጣራበትን ምክንያት ለማወቅ ሄደና ደብተራውን ከበቅሎይቱ ሥር ጐትቶ ለማውጣት እገዘው። ቀጥሎም ደጋግፈው እበቆሎይቱ ላይ ካስቀ መጡት በኋላ ሳንቾ ችቦውን ሲያቀብል ዶን ኪሾት ደግሞ እነ ዚያ ጓደኞቹ የሸሹበትን አቅጣጫ ይዞ እንዲከተላቸው በመም ከር ይህን የወደቀባቸውን አደጋ ከመጣል ለመታገድ ሳይችል ከቀረ ጥፋቱ የሱ አለመሆኑን ገልጦ በማስረዳት በሱ ስም ሆኖ ይቅርታ እንዲጠይቅለት ለመነው ። ሳንቾም በተጨማሪ ለደብተ ራው እንደዚህ ሲል አስረዳ። ምናልባት እነዚያን መኳንንቶች በዚህ ሁኔታ አጉሳቁሎ ያስፈረጠጣቸው ጀግና ሣን መሆኑን ለማወቅ የፈለጉ እንደሆነ ስመ ጥሩው የሚንቻው ዶን ኪሾት መሆኑን እንዲሁም ተደራቢ ስሙ «የአረመመው ፈረሰኛ የሚባል መሆ ኑን እንዲያስታውቁአቸው አለው ።

ደብተራውም ንግግራቸውን ካሰጨረሱ በኋላ እንደተመ ከሩት ጓደኞቻቸው የሸሹበትን ዱካ ተከትለው ሄዱ ። ዶን ኪሾት ግን ይህ ጋሻ ጃግሬው ያወጣለት አዲስ ስም ምስጢሩ ምን እንደሆነ ለማወቅ ስለቸኮለ ከዚህ ቀደም ሳይሆን ልክ ባሁኑ ሰዓት የአረመመው ፈረሰኛ ብሎ የሰየመበት ምክንያት እንዲ ያብራራለት ጠየቀው ። ሳንቾም ምስጢሩን አሁኑ ገልጭ እነ ግርዎታለሁ ሲል መለሰለትና ማስረዳቱን በመቀጠል» እንዲህ ብዬ መሰየሜ በዚህ ባልታደለው የተንኮለኛ አጠገብ ሲበራ በነበረው የችቦ ብርሃን ትይዩ ሰጥቂት ጊዜ ስመለከትዎ ቆይቼ ነበርና ይህን ያህል ጊዜ አብሬዎ ስኖር ምን ጊዜም ያላየሁቦ ትን እጅግ የሚያስቀይም ጨፍጋጋ የትካዘ መልክ በፊትዎ ላይ በማየቴ ነው ።

መልክዎንም ለመለወጥ ምክንያት የሆነው ለኔ እንደሚመስ ለኝ በዚህ ውጊያ ላይ ደካም ስለተሰማዎት ወይም ደግሞ የጥርስዎ መርገፍ እያበሳጨዎት ይሆናል አለው ።

«ምክንያቱም ይህ ሊሆን አይችልም» አለ ዶን ኪሾት ዳሩ ግን የጀብዱ ሞያዬን ታሪክ ለመጻፍ ኃላፊነት የተጣለበት ሊቅ ለጥንቶቹ ዙዋሪ ፈረሰኞች እንደሚወጣላቸው ሁሉ እኔም አንድ ተደራቢ ስም እንዲወጣልኝ አስፈላጊ መሆኑን ስለአመነ ይሆናል ። ለጥንቶቹም ዙዋሪ ፈረሰኞች የወጣላቸውን ስም የግ ስታውሰውን ሰምሳሴ ያህል ልጠቅስልህ እፈቅዳለሁ ። ይኸውም ባለ አብረቅራቂ ሰይፍ ባለ አንድ ቀንድ ፣ ባለ ሴት ወይዘሮ ፣ ባለ አፈ ያፈድ ፣ ባለ ጆቢራ አሞራ ፣ ባለዓዕረ ሞት የሚባሉ ፈረሰ ኞች ሁሉ በየጊዜያቸው በዚህ ተደራቢ ስም እየተጠሩ በመላው ዓለም የታወቁ ሆነው ነበር ። ስለዚህ እኔ እንደማምነው ያ ያል ኩህ ሊቅ አንተ ባለ ትካዘ መልክ የሚል ስም እንድትለወጣ ልኝ ሃሳቡን በእራስህ ውስጥ አግብቶ በምላስህ ላይ አናግሮህ ይሆናል ። እኔም ከአሁኑ ጀምሬ ወደፊት በዚሁ በወጣልኝ ተደ ራቢ ስም ለመጠራት አስቤአለሁ ። እንዲያውም ስመ ጥሩ ሆኖ ከመልኬ ጋር እንዲመሳሰል ጊዜ ሳገኝ በጋሻዬ ስጉድ ላይ የት ካዘ መልክ ሰዕል አስልበታለሁ አለው ።

«የዚህን ዓይነት መልክ ለማሳል ሲሉ ጊዜ ማጥፋትና ገን ዘብ ማባከን በፍጹም የሚያስፈልግ አይደለም «ሲል መለሰ ሳንቾ ክቡርነትዎ ፊትዎን ወደሚመለከትዎ ሰው አዙረው ከታዩ ይህ ብቻ በቂ ነው ፣ በዚያን ጊዜ ማናቸውም ተመልካች ስዕል ማየ ትና ጋሻ መመከት ሳያስፈልገው መልክዎንና ስምዎን በማመሳ ከር ወዲያውኑ በቀጥታ ይህ «የአረመመው ፈረሰኛ » ነው ብሎ እንደሚጠራዎት እርግጠኛ ለመሆን ይችላሉ ። የተናገርኩትም እውነቴን መሆኑን ይመኑኝ ። ምክንያቱም (በመቀለዴ ይቅርታ ያድርጉልኝና) በረሃብ መጠውለግዎና ጥርስዎም መርገፉ መል ክዎም አጨማዶ አስቀያሚ ስለአደረገዎት ቅድም እንደነገር ክዎት ተጨማሪ መግለጫ የሚሆን አስቀያሚ መልክ ማሳል በፍጹም ሊቀር የሚችል ነገር መሆኑን አረጋግጥልዎታለሁ» አለው ።

ዶን ኪሾትም በሳንቾ የቀላጅነት መንፈስም ከልቡ ሳቀ ። ሆኖም ያንን የወጣለትን ተደራቢ ሰም ለመውሰድና እንዲሁም እንዳሰበው ሁሉ የትካዜውን መልክ ስዕል በጋሻው ላይ ለማ ሳል ቁርጥ ሃሣብ አድርጐ ሳንቾን እንዲህ አለው ።

« የምወድህ ሳንቾ ሆይ ! የተቀደሰውን ነገር ያረከሰ እር ኩስ ይሁን እንደተባለው እኔ በዛሬው ቀን የተወገዝሁ መሆ ኔን አሳምሬ አውቄዋለሁ ። ምክንያቱም ምንም እንኳ እነዚያን ሰዎች የነካኋቸው በእጄ ሳይሆን በዚህ በያዝኩት አንካሴ ቢሆን በአጥቂነት መንፈስ ተገፋፍቼ ብፁዓን የሆኑትን የቤተ ክህነት ሰዎች በመንካቴ ተፀጽቻለሁ ። እንደምታውቀኝ በምግባሬ ፍጹም በአልሁበት ነገር የጸናሁ እንደመሆኔ መጠን እጅግ አድርጌ የማ ከናውነውንና የማመለክተበትን የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይና በተ ለይም ካህናትን ለመበደል አላሰብኩም ነበር ። መቼም ልፋቴ ሁሉ እነዚያን አጋንንቶችና የሌላ ዓለም ጀግያኮሳትን ከምድር ላይ ለማጥፋት ስለነበረ አስማተኞቹ አዛውረው ወደምወገዝበት ጥፋት ላይ ጣሉኝ ። ይህም ውግዘት የሚያርስብኝ ቢሆንም ቅሉ በሴዲ ሩዋይዲያዝ ላይ የደረሰውን ሁኔታ ፣ አስታውሰዋለሁ ፣ ይኸውም በብፁዕነታቸው ፊት ቀርቦ የነበረው አምባሳደር የተቀ መጠበትን ወንበር ረግጦ በመሰባበሩ በዚህ ምክንያት መወ

ገዙን ነው ። ይህም ሆኖ በዚያኑ ዕለት ጉበዙ የቪቫሩ ርድ ሬጉ በፈጸመው የወንድነት ሙያ የተከበረና ዋጋ ያለው ፈረሰኛ የሚ ያደርገውን ስመ ጥሩነትን አግኝቷል ።

ይህን አነጋገር ደብተራው ከሰማ በኋላ እንደተባለው ሁሉ አንዳችም መልስ ሳይሰጥ ትቷቸው ሄደ ።

ዶን ኪሾትም በዚያ በቃሬዛው ውስጥ እውነት እንደተ ባለው የሰው አጽም መኖር አለመኖሩን አይቶ ለማረጋገጥ ፈቅዶ ነበር ፣ ሳንቾ ግን ይህን ሃሳቡን በመቃወም እንዲህ አለው ።

«ክቡርነትዎ ይህን የዛሬውን አደገኛ ግጥሚያ ከሌሎች እስካሁን ድረስ ከአየኋቸው ግጥሚያዎች ሁሉ እጅግ በተሻለ አኳኋን ተወጥተውታል ፣ እነዚህ ሰዎች ምንም እንኳ ቢሸ ነፉና ቢበታተኑ እንዲህ አድርጉ ያንኰዳቸው አንድ ሰው ብቻ ውን መሆኑን ሲያመዛዝኑ ጥቃትና እፍረት ተሰምቷቸው በመ በቀልና ድሉን ለማግኘት ሊፈልጉ መመለሳቸውና ቢያገኙም እንደማንተርፋቸው አድርገው ማጥመልመላቸው የማይቀር ነገር ስለሆነ በኔ ይሁንብዎትና ምክሬን ይቀበሉኝ ። አህያይቱ ዝማጁ ሆናለች፡ ዝማጁ የሆነችውም ደስ በሚያሰኝ መሰናዶ ነው ፣ አፋፍ ቅርባችን ነው ። እረሃቡ ወንቷል ፣ ስለዚህ ባሁኑ ሰዓት እንዲህ እንደ አማረብነ እርምጃችንን አስረዝመን ከመሥገስ በስተቀር ሌላ ነገር መመራመር አያስፈልገንም ተረቱም የሚለው «የሞቱት ወደመቃብራቸው ፣ የቆሙት ወደ እንጀራቸው ትዳራቸው» ነውና እዚህ ስንልከሰከስ ተገኝተን አደጋ እንዳይደርስብን መሥጋት ይገ ባናል ፤ ካለ በኋላ መልስ እስኪሰጠው ድረስ ሳይጠብቅ አህያይቱን ወደፊት እየነዳ ጌታው ተከትሎት እንዲመጣ ለመነው ። ጌታውም የሳንቾ አስተያየት ትክክለኛ ስለመሰለው እንደል ማዱ ሳይከራከር ተከተለውና ጉዞአቸውን ጀመሩ ። በሁለቱ ኮረ ብታዎች መካከል ተጠምዘዘው ጥቂት ምዕራፍ መንገድ ከተ ጓዙ በኋላ ሰፋ ያለመስክ የሚገኝበት ሆኖ ምኞት የሚያን ሰው እረባዳ ቦታ ላይ ደርሰው ሠፈር አደረጉ ። ሳንቾም ፈጥኖ አህያውን አራገፈና እነዚያ የሚቹ አጃቢ ቂሶች (በረሀብ መጐዳትን ያልለመዱ ሰዎች በመሆናቸው) በደንብ ሰንቀው

በበቅሎ ጭነው በሰተኋላቸው ካስከተሉት ላይ ዘርፎ የያዘውን ስንቅ ዘርግፎ በመስኩ ላይ ማዕዳቸውን ዘርግተው ተቀመጡና በረሃብ ወጥ እያጣፈጡ አንድ ሰሞን ለቁርስ ለምሳ ለመሸን ገሃ ለእራት የሚበቃውን ሁሉ በአንድነት አጠቃልለው ከሰ ከሱ ። ዳሩ ግን እዚህ ላይ ሌላ ጠንከር ያለ ችግር ደረሰባቸው ። ይኸውም በሳንቾ አስተያየት ከማናቸውም ችግር ይበልጥ የከፋ ሆኖ የታየው የሚጠጣ ወይን ጠጅ ባለማግኘቱና የባሰውን ደግሞ ከንፈራቸውን የሚያርሱበት አንድ ጠብታ ውሀ እንኳ መታ ጣቱ ነው ። በውነቱ ይህ የውሃ ጥም ታላቅ ሥቃይ ፈጥሮባቸው ነበርና ከተቀመጡበት መስክ ላይ የበቀለውን ሣር እርጥበትና ለምለምነት ሳንቾ ተመልክቶ በሚቀጥለው ምዕራፍ ላይ የሚ ተረከውን ተናገረ ።

ምዕራፍ 20

በስመ ጥሩነታቸው ፡ በመላው ዓለም ላይ የነገኑት ዙፋሪ ፈረሰኞች ምን ጊዜም ይህን የመሰለ ብርቱ አጋጣሚ ለማግኘት እድል ሳይኖራቸው ጀግናው የማንቻው ዶን ኪሾት አማኙቱ እጅግ ባነሰ አደጋ ያከናወነው ከቶ ያልተሰማና ያልታዩ የጥሚያ ሁኔታ ይተረካል ።

ሳንቾ ፖንቻ እንዲህ ሲል ሃሳቡን ለጌታው አካፈለ ። «የተከበሩ ጌታዬ ሆይ ! ይህ የምንነካው ሣር እንደዚህ እርጥብና ለምለም ሆኖ ለመብቀል የቻለው በአቅራቢያው የምንጭ ወይም የወንዝ ስሜት ቢያገኝ ስለሆነ ጥቂት ወደፊት እለፍ ብለን ብን ፈልግ አይከፋም ። ዕድላችን አግዞን ወሀ ብናገኝ ይህን የሚ ያስቃየንን ብርቱ የውሀ ጥም በቶሎ ልናስወግደው እንችላለን ። ከረሃቡ ይልቅ ይበልጥ የጉዳን ውሃ ጥሙ ነው አለው »

ይህ ምክር ለዶን ኪሾትም የተስማማ ሆኖ ስለተገኘ ከእራታቸው ያተረፉትን ስንቅ በአህያይቱ ላይ ከጫኑ በኋላ ሳንቾ የአህያውን ሎሀ ሲስብ ዶን ኪሾት ደግሞ የሮንዚናንቴን ልጓም ይዞ መቸም የሴሊቱ ጨለማ አንዳች ነገር እንዲያዩ አልፈቀ ደላቸውም ነበርና በዳበሳ እየተመሩ ተከታትለው በመስኩ ላይ መሄድ ጀመሩ ። ዳሩ ግን ሁለት መቶ እርምጃ የሚሆን እንደ ተንዙ ካንድ ትልቅና ረጅም ከሆነ ቋጥኝ ላይ ቁልቁል የሚወርድ ፏፏቴ የሚመስል ታላቅ የውሀ ጉርምርምታ በኃይል እያስተ ተጋባ ወደ ጆሮአቸው ደረሰ ። ይህንንም ኃይለኛ ጉርምርምታ በሰሙ ጊዜ በደስታ ተጽናንተው ድምጹ የሚመጣበትን አካያ ለማወቅ ሲያዳምጡ እነሆ ሌላ ኃይለኛ ነጐድጓድ ተቀላቅሎ

ስለተሰማቸው በዚህ ምክንያት ቅድም ውሃ ለማግኘት ያደረጉት ደስታና ተስፋ ወዲያውኑ ወደ ፍርሃት ተለወጠባቸው ።»
በተለይም ሳንቾ በተፈጥሮው ፈሪና አሞተ ትንሽ በመሆኑ ይህ እሽባሪ ድምጽ ልቡን አባብቶ በድንጋጤ ሊገድለው ደረሰ ። ይህም አስገምጋሚ ድምጽ ከተራራና ከቋጥኝ ጋር እየተላጋ እንደሚወድቅ ብዙ ናዳ በመንጋጋትና እንዲሁም የብረትና የሰንሰለት ቅጭልጭል የሚመስል ኳኳታ አብሮት እየወረደ ከፏፏቴው ጩኸት ጋር ተገኝቶ የሚያሰማው ድብልቅልቅ ጩኸት የዶን ኪሾትን ልብ ላልያዘ ለሌላ ለማናቸውም ሰው ፍርሃትና ሽብር የሚፈጥርበት መሆኑ የተረጋገጠ ነበር ። ከላይ እንደተባለው ሁሉ ሌሊቱ በጣም የጨለመ በመሆኑና እነሱም ወደ ፈት ተጉዘው ረጣኙም ዛፎች የሞሉበት ጫካ ውስጥ በመግባታቸው ፣ የዛፎችንም ቅጠል ነፋስ እያወዛወዛቸው የለዘበና የቀፈፈ ሹክሹክታ ፣ በማሰማታቸው በዚህ አካኋን የሰፍራው መከበድ የጨለማው መደንገር ፤ የውሃው ማጉረምረም ፣ የቅጠሎቹ መንከሻከሽ ፤ ይህ ሁሉ እንድነት ተደምረው ሲታሰብ በውነቱ የሚያስደነግጥና የሚያስፈራ ነበር ። ይህም ሆኖ ፍርሃታቸውን ለመቀነስ ያህል እንካ ጉርምርምታው አላቋረጠም ፣ነፋሱም ፀጥ አላለም ፤ ሌሊቱ የመንጋት ምልክት አላሳየም ነበር ። በዚህ ሁሉ ላይ ደግሞ በተጨማሪ ሁለቱ ከርታታዎች የሚገኙበትን ቦታ በፍጹም አያውቁም ነበር ። ዶን ኪሾት ግን በቆራጡ ልቡ ተደፋፍሮ ዘልሎ ሮንዝናንቴ ላይ ወጣና ጋሻውን አንግቦ ፣ እንካሲውን አጓምዶ ወደ ጉርምርምታው አቅጣጫ ለመሔድ ዝግጁ ከሆነ በኋላ ጋሻ ጃግሬው እንዲህ አለው ።

« ወዳጄ ሳንቾ ሆይ ! እኔ እውነትና ትክክለኛነት ከአንተ ጋር ይሁን ፤ በዚህ በብረት ዘመን መወለዴ ያንን የወርቅ ወይም የወርቀ ዘቦ የሚባለውን ዘመን ለማንሳት ነው ። እኔ ታላላቅ የጀብዱ ተግባሮችና መቅሰፍት የሆኑ አደጋዎች የተደገሱለት ሰው ነኝ ። እኔ አውንም መላልሼ እናግረዋለሁ ፤ እነዚያን የክብ ጠረጴዛ ጀግኖችን ፣ አስራ ሁለቱን የፈረንሳይ የኮበዝ አውራዎችን ፣ ዘጠኙን የዓለም ሰመ ጥሩዎችን ከተረሱበት ሥፍራ የማስነሳ ነኝ ። እኔ የነፕላቱርን ፣ የነታብላንቴን ፤ የነአባልቴን ፣ የነቴራንቴን ፣ የነፈቦን ፣ የነቤሊያንጂንና እንዲሁም ደግሞ ባለፉት ዘመናት

የነበሩት እነዚያ ስማቸውን ለማስጠራት ሲሉ ይህን የመሰለ ታላላቅ የጀብዱ ተግባርና የጦርነት ጉዳይ የፈጸሙትን ዘውሪ ፈረሰኞች ከንተከታዮቻቸው እጅግ ከባድና ጠንካራ የሆነ ሞያቸውን ዛሬ በጥላዬ የማጨልመው ነኝ ።

« ስለዚህ ታማኙና ቁምነገራሙ ጋሻ ጃግሬዬ ሆይ ! በል እንግዲህ ቅደምና የዚህን የሌሊት ጨለማ መንገድ ምራኝ ። የጨለማው አስደናቂ ዝምታና የነዚህ ዛፎች ልዝብና ድንቁር ያለው ሹክሹክታ ይህ ዱካውን ተከትለን የምንሄድበት እርዝመቱ ካለቀው ከጨረቃ ተራራ ላይ ፈልሶ የሚመጣ የሚመስለው አስደንጋጭ ድንፋት ፣ ይህ ጀሮአችንን እያቆሰለ የሚያደነቁርና ያለማቋረጥ የሚደወለው የብረት ቅጭልጭል ድምጽ እነዚህ ሁሉ አንድነት ተደምረው ፣ እንዲያውም እያንዳንዳቸው ራሳቸውን ችለው ሲታሰቡ የዚያኑ የጦርነትን አምላክ የማሪቴን ልቡ በድንጋጤ ፣ በፍርሐትና በሽብር ለመሙላት የሚበቁ ናቸው ።

« ወዮላቸው እነዚያ ያለፉት ጀግኖች ይህን የመሰለ ከባድ ሁኔታና አደገኛ አጋጣሚ ሲያገኛቸው አሸንፈው ለመውጣት የቱን ያህል መጨነቅ እና መጠበብ ፣ ፍርሐትና ድንጋጤ እንደሚደርስባቸው ሳስበው በእጅጉ ያሳዝኑኛል ። ዳሩ ግን እነዚህ የማስደንገጥን ኃይል አከማችተው የያዙትና ድምጻቸውን የሚያሰሙ መሳሪያች ሁሉ በኔ ልብ ውስጥ ድፍረቴን ከማጋጋልና ወኔዬን ከማነቃቃት በስተቀር ከቶ ፍንክች አያደርጉኝም ። እንዲያውም እነዚህን የነጐድጓድ መሳሪያች ከሰማሁበት ጊዜ ጀምሮ የቱን ያህል አደገኛና ቀሰፊ ቢሆኑም አጠገባቸው ደርሼ ለመግጠም ያለኝ ፍላጐት በመገንፈሉ የተነሳ ገና ቅድም ልቤ መግሸቶ ወጥቶ ደረቴ ላይ ደርሷል ። ስለዚህ የሮንዜናንቴን ቅናት በደንብ አጥብቅልኝና እስከ ሶስት ቀን ድረስ እዚሁ ሆነህ ስትጠብቀኝ ቆይ ። እውነትና ትክክለኛነት ካንተ ጋር ይሁን ። ምናልባት ሰውና እንጨት ተሰባሪ በመሆኑ በዚህ በሶስት ቀን ውስጥ ተመልሼ ሳልመጣ በዚያው ቀልጬ የቀረሁ እንደሆነ አንተ በመሞቴ ቁርጠኛ ሆነህ ወደ መንደራችን ለመመለስ ትችላለህ ። እዚያም እንደደረስህ ሳትውልና ሳታድር ወደ ቶቦዞ ተሸግረህ ለእመቤቴ ለወደር የለሽ ዱልቺኒያ ባሪያዎ ፈረሰኛ የማንቻው

ዶን ኪሾት የኔ ነው ተብሎ ለመጠራት የሚያበቃውን እጅግ ከፍ ያለ የጀግንነት ተግባር ሲፈጽም ሞተ ብለህ እንድትለ ረዳት አደራዬን ጥዬብሃለሁ አለው ።»

ሳንቾ ይህን የኑዛዜ ቃል ከጌታው እንደበት በሰማ ጊዜ እንደተቆረጠች በለስ እንባው እየረገፈ ተንሰቅስቆ ያለቅስ ጀመር ። ወዲያውም ቀጠለና እንዲህ ሲል ምክር አቀረበ ።

«ተወዳጁ ጌታዬ ሆይ ! መቼም ከዚህ እጅግ አደገኛ ከሆነው ጥሞሪያ ውስጥ በሕይወት ተርፎ መመለስ በፍጹም ተስፋ የሌለው ነገር ስለሆነ ክቡርነትዎ እስከዚህ ድረስ ጨክነው ለመጋጠም የፈለጉበት ምክንያት ከቶ ሊገባኝ አልቻለም ። እንደሚያዩት ወቅቱ መንፈቀ ሌሊት ነው ። ከሁለታችን በስተቀር ገበናችንን ዓይቶ የሚታዘበን ሰው ባጠገባችን የለም ። ምንም እንኳ ውሀ ሳንጠጣ ሶስት ቀን ያለፈን ብንሆን ያላንዳች መሣደርደር በቀጥታ በሌላ መንገድ አሳብረን ከዚህ አደጋ ለመራቅ እንችላለን ። እንደነገርክዎት ባሁኑ ሰዓት ማንም ሰው ስለማያየን ፈርጣጮች ብሎ ሊሰድበን አይችልም ። ይልቁንም ደግሞ እርስዎ በጣም የሚያውቋቸው የመንደራችን ቄስ አባ ጴጥሮስ ሲሰበኩ የሰማኋቸውን እንደማስታውሰው » አደጋን የሚፈልግ በዚያው ቀልጠ ይቀራል » ብለዋልና እርስዎም ይህን የቄሱን እውነተኛ ስብከት የሚያምኑ ከሆኑ ይህን ከመሰለው በተአምር ካልሆነ በስተቀር ሊዳንበት ከማይቻለው አቅላጭ አደጋ ውስጥ በገዛ እጅዎ ተሰንቅረው በእውነት ሌላ ሊያማርሩ አይገባዎትም ። ባለፈው ጊዜ እንደኔ በብርድ ልብስ ከመራገብ የጠበቅዎትንና እንዲሁም እነዚያን የሙት አጀቢዎችን የመሰሉ ብዙ ጠላቶች ብቻዎን ገጥመው አንዳች ጥቃት ሳያገኝዎት ድል እንዲያደርጉ የረዳዎትንና ቀኑንም የሰጠዎትን አምላክ የቸርነቱን ስፋት አመስግነው አርፈው ቢቀመጡ አይሻልዎትምን ? ዳሩ ግን ይህ ሁሉ ምክሬ ይህን የብረት ልብዎን ለማላሳትና ችኩላዎን ለማስታገሥ የማይቻል ሆኖ ከተገኘ ክቡርነትዎ ከዚህ እንደራቁ ወዲያውኑ ነፍሴን ሊወስዳት ለሚፈልገው ለማናቸውም ፍጥረት ያለክር ክር ለመስጠት የተዘጋጀሁ መሆኔን አውቀው በዚህም ምክን ያት የሚደርስብኝ ጭንቀት የቱን ያህል የከበደ መሆኑን አስ

በው ይዘኑልኝ ። እኔ ሚስቴንና ልጆቼን በትኜ ክቡርነትዎን በጋሻ ጃግሬነት ተከትዬ ለማገልገል ቆርጬ ከአገሬ የወጣሁት ቀድሞ ከነበርኩበት ሁኔታዬ ጥቂት ከፍ ለማለትና እንደሚያልፍልኝም ተስፋ በማድረግ ነው እንጂ የባሰ አደጋ ላይ ለመውደቅ አል ነበረም ። መቼም ብዙ የሚፈልግ ሰው ምንም አያገኝም ተብ ሏልና እኔም በዚሁ መጠን ተስፋዬንም ጭምር ለማጣት በቃሁ። ምክንያቱም ያቺን ተስፋ ያደረጉልኝን የተረገመች ደሴት ለመ ቀበል አጠገቧ የደረስኩ ሲመስለኝ እነሆ ይኸው አፍራሻውን ለአገልግሎቴ ዋጋ አድርገው ሊከፍሉኝ የተሰናዱት ሚናቸውም የሰብአዊ ማኅበር እርዳታ ሊገኝ በማይችልበትና እሪታዬንም ሁሉ ነፋስ በልቶት በሚቀርበት እጅግ ተናጠል በሆነ ዱር ውስጥ ብቻዬን ትተውኝ ክቡርነትዎ ወደ ሞት መሄድዎ ሆነ ። የተከ በሩት ጌታዬ ሆይ ! ስለ እውነኛው ብለው እንዲህ ያለ ክፉ በደል አይበድሉኝ ። ምንአልባት እንኳ ይህን ግጥሚያ ከማድ ረግ በፍጹም ለመታገድ የማይችሉ ሆነው ቢገኙ በዛሬው ሌሊት መሆኑ ቀርቶ ለነገ ጠዋት ያስተላልፉት ። በኔ በእረኛው ሂሳ ብና አገማመት እንኳ ወደ ጐሕ ለመድረስ ከሶስት ሰዓት ይበ ልጥ የሚርቅ አይመስለኝም ። ይህንንም የምለው አጥቢያው ኮከብ በእናታችን አቅጣጫ በግራ ክንድ መስመር ሲታይ መንፈቀ ሌሊት መሆኑን ስለማውቅ ነው » አለ ።

ዶን ኪሾትም እንዲህ ሲል ጠየቀው «ለመሆኑ እንዴት አድርገህ ነው ይህን አጥቢያና ይህን መስመር ፥ ይህን ክንድ ለማወቅ የቻልከው ? ሌሊቱ በጣም የጨለመ በመሆኑ በመላው ሰማይ ላይ እንዲት ኮከብ እንኳ አትታይም» አለው ።

«እርስዎ ያሉት እርግጥ ነው ።» ሲል መለሰ ሳንቾ ። ዳሩ ግን ፍርሃት የሚባለው መቶ ዓይኖች ያሉት ስለሆነ ማናቸውንም ነገር ከመሬት ውስጥ የተቀበረውንም ጭምር ጠልቆ ለማየት ሲችል በጠራው ሰማይ ላይ ደግሞ ይበልጥ እንደሚያይ ጥርጥር የለበትም ። ከዚህም በስተቀር ደግሞ በዓይን ጭፍን ቢገመትም እንኳ ካለሁን አንስቶ እስከ ንጋት ድረስ የሚቀረው ጥቂት ሰዓት መሆኑን በቀላሉ ለመረዳት ይቻላል» አለው ።

«ለመንጋት የሚቀረውን ያህል ቢቀርም «አለ ዶን ኪሾት» ዛሬም ሆነ ምንጊዜም እንባ እያፈሰሱ መለመንና መለማመጥ፣ መውትወት የዙዋሪ የፈረሰኛነት ግዳጁን ከማከናወን ያስተን ጉለኛል ብሎ በኔ ላይ ተስፋ ማድረግ ከንቱ ነገር ነው። ይል ቁንስ ሳንቾ ለማልበገርበት ጉዳይ ማልቀሱን ተወውና እረጋ በል፣ ሴት ይመስል አትነዝንዝኝ፣ በተለይ የምለምንህ ዝም እንድትለኝ ብቻ ነው። ይህን ምንግዜም ያልታየና አስፈሪ የሆነ ግዮሚያ እንድአከናውን ግዴታውን በልቤ ውስጥ ያሳደረው አውነት እኔን ከአደጋው ለማዳንና ያንተንም ጭንቀት ለማጽ ናናት ያስብበታል። ስለዚህ የሮንዝናንቴን ቅናት አጥብቅል ኝና እዚሁ ቆየኝ። እኔ ቆሚም ሆነ ሞቼ በፍጥነት እመለሳለሁ» አለው።

ሳንቾ ከጌታው የተሰጠው መልስ የመጨረሻ ቁርጥ ቃል መሆኑን በማመን፣ ልቅሶውም ምክሩም ልመናውም ለምንም እንዳልጠቀመው በመረዳት፣ በሌላ የተንኮል ዘዴ ሊያስገድ ደው አሰበ። ይህም ዘዴ የሚያዋጣው ቢሆን ዓለማው እስኪ ነጋ ድረስ ጌታውን ከአጠገቡ እንዳይርቅበት ለማድረግ ነበርና በዚህ ቁርጥ ሐሳብ ውሳኔ ካደረገ በኋላ ወደ ፈረሱ ተጠግቶ ዝቅ ብሎ ቅናቱን የሚያጠብቅ በመምሰል ምንም ሳያስማና ሳይታ ወቅበት በአህያይቱ ሰካ የሮንዝናንቴን ሁለት እግሮች አጥብቆ አሰረው። ዶን ኪሾትም ለመሄድ በሚነክርበት ጊዜ ፈረሱ እየተፈራገጠ ሽቅብ ከመዘለል በስተቀር ሊራመድለት አልቻ ለም ነበር። ሳንቾም ያጠመደው ተንኮል እንደያዘለት አወቀና እንዲህ አለ።

«አዩት የእኔ ጌታ የሰውን ልብ ርህሩህነትና የሰውን ልበ ደንዳናነት ለቅሶዬና ልመናዬ ሰርስዎ አልሰማ ቢል በእውነት ኃይል ተንበርክቆ እነሆ የሮንዝናንቴን እግር ሰነከለው። ከእንግዲህ ወዲያ ከቡርነትዎ ወርደው በእግርዎ ካልሄዱ በስተቀር ፈረሱ ይሄድልኛል ብለው እንስሳውን በኃይል ቢኰረኩሩት ዕድልዎን እንደማታከትና ግድግዳ እንደመኰርኮር የሚቆጠር ስለሆነ በክ ንቱ አይድከሙ» አለው።

ዶን ኪሾትም በዚህ ስውር በሆነ መታገድ ክፉኛ ተበሳ ጭቶ ፈረሱን ከቀድሞው ይበልጥ አከታትሎ ቢኮረኩረው የመ ነቃነቁ ኃይል ይበልጥ እየቀነሰ ይሄድ ጀመር። እግሩ የታሠረ መሆኑን ባለማወቁ የተነሳ ይህ ብርቱ መታገድ የመጣው በሳ ንቾ መሠሪነት ሳይሆን ከፍጡር በላይ በሆነ ሥልጣን ተዳኝቶ መሆኑን ስለአመነ ሴሊቱ እስቲነጋ ድረስ ወይም ደግሞ ሮንዜናንቴ ዛሩ ገለል ብሎለት ለመነቃነቅ እስቲሞክር ድረስ ታግሶ ለመጠ በቅ ከወሰነ በኋላ እንዲህ አለ።

«እንግዲህ ሳንቾ እንደምታየው ሁሉ ሮንዜናንቴ በፍጹም ለመነቃነቅ አልቻለም። ስለዚህ ምንም እንኳ ወደ አደጋው ቦታ ደርሼ ለመጋፈጥ ባለመቻሌ የተነሳ እስቲነጋ ድረስ መጠ በቅ ግዴታ ቢሆንብኝ እስከዚያው ድረስ እዚሁ ተገትሬ በክ ንቴ የማሳልፈው ጊዜ ሁሉ እያንገበገበ እንደሚቆጨኝ ይሰ ማኛል።

«አይዝዎት የኔ ጌታ አይበሳጩ» አለ ሳንቾ። «እኔ እንዳ ይቆጭዎት አድርጌ በዘዴ አጽናናዎታለሁ። መቸም እንደዶንቡ ሌሊቱ ነግቶልዎት ከዚህ ዓይኑን አፍጥጦ ከሚጠብቅዎት ታላቅ አደጋ ጋር ፊት ለፊት እየተያዩ የሚጋጠሙበት ጊዜ ሲደርስ ሕዋሳትዎ ቀደም ብሎ ጥቂት ዕረፍት አድርጐ በርትቶና ተብቶ መገኘት ይገባው ስለነበረ፣ ምንም እንኳ አስተዋዮች ዙዋሪ ፈረ ሰኞች የሚያደርጉትን በመከተል በአውኑ ሰዓት ከፈረስዎ ላይ ወርደው በዚህ በለመለመው ሣር ላይ ጋደም ለማለት ባለመ ፈለግዎ የተነሳ እንደተገተሩ የሚያነጉ ቢሆንም እኔ በበኩሌ ካውኑ ጀምሬ እስከ ነገ ጥዋት ድረስ ልዩ ልዩ ዓይነት ተረቶች እያከታተልሁ በማውራት አጫውትዎታለሁ» አለው።

«እንዴት በል? ከፈረስህ ላይ ወርደህ ተኛነው የምትለኝ?» ሲል ዶን ኪሾት በመገረም ጠየቀው፣ ንግግሩን በመቀጠል እረ ለመሆኑ ስትገምተኝ እነዚያን በተውጤ ውስጥ ተዝናንተው የሚገኙትን ዳተኛ ፈረሰኞች መስዬ ታየሀሀን? ይልቁንስ አንተ ጥንቱንም ለመተኛት የተፈጠርህ ስለሆንክ ተኛ።

ወይም ሌላ የሚያሰኝህ ነገር እንዳል አድርግ ፥ እኔ ግን ለተግባሬ የተገባውን ግዳጅ ከመፈጸም የሚያሰናክለኝ አንዳች ነገር ሊኖር እንደማይችል እወቀው » አለው

ሳንቾም መለሰ «ጌታዬ ሆይ ! አይቆጡ የተናገርኩት ለማ ለት ያህል ነው እንጂ እውነትስ የኔን ሃሳብ ይቀበላሉ ብዬ አይደለም » አለው ።

ከዚህ በኋላ ወደ ዶን ኪሾት ተጠጋና ባንድ እጁ ቀዳማ ውን ፥ በሌላኛው እጁ ደሐራውን ይዞ የጌታውን የግራ ታፋ ተደግፎ ያስደንጋጩን ጉርምርምታ ማስተጋባት እየሰማ አለ መጠን ፈርቶ ነበርና ያንዲት ቅንጣት ፈቀቅታ እንኳ ሳይርቅ ቆመ ። ዶን ኪሾትም ሳንቾ በሰጠው ተስፋ መሠረት አንዳንዴ ተረት እያወራ እንዲያጫውተው ጠየቀው ።

«መልካም ፈቃዴ ነው» አለ ሳንቾ ፥ የዚህ ጉርምርምታ ማደ ንቆር የልቤ ትርታ ምላሴን ካላሠረው በስተቀር አንዳችም ቃል ሳልሳሳት ሁሉንም በትክክል ለመናገር የቻልኩ እንደሆነ ከተረ ቶች መካከል በጣም ምርጥ የሆነውን ለማውራት ቻልኩ ማለት ነው ። እንግዲህ መጀመሪ ስለሆነ ተጠንቅቀው ይስሙኝ ።

«አንድ ጊዜ የነበረው አንድ ጊዜ ነበር ፤ ለሚገባው መል ካም ነገር ይግጠመው ፤ ክፉ ነገርም በሚፈልገው ላይ ይድረ ስበት ፤ ይህን ማለቴ የዱሮ ሰዎች ተረት ሲናገሩ የሚጀምሩበ ትን ፈሊጥ ክቡርነትዎ እንዲያውቁት ብዬ ነው ። ይህም ፈሊጥ ማናቸውም ዓይነት አይደለም፤ ዳሩ ግን ከአባት ነፍጠኞች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ምሳሌ ነው። የጥንቶቹ ሮማውያን እንደሚሉት «ክ ራን ነገር ለሚፈልገው ይሰጠው ፤ ያሉት በውነቱ ባሁኑ ሰዓት ተረትነቱ ከሁኔታችን ጋር እንደ እጅ ሹራብ ልክክ ያለ ስለሆነ ክቡርነትዎ በየትኛውም ቦታ ክፉ ነገር ለመፈለግ ባይሄዱ ደስ ይለኛል ። እንዲያውም ይህን መንገድ ትተን በሌላ መንገድ ብንሄድ እመርጣለሁ ። በዚህ ባሁኑ መንገዳችን ላይ በያንዳንዱ እርምጃ ከፍርሃትና ከድንጋጤ ጋር እየተገናኘን እንድንሄድ የሚያስገ ድደን ሰው የለም» አለው ።

ዶን ኪሾትም እንዲህ ሲል መለሰ «አንተ ያለብህ ተረ ትህን መቀጠል ነው እንጂ ያልተጠየቅኸውን ይህን ሁሉ ሐተታ

ማውራት አልተፈቀደልህም ። የምንሄድበትን መንገድ የመም ረጡ ጉዳይ እኔን የሚመለከት ስለሆነ እኔው አስብበታለሁ » አለው ።

«ይሁን ደግ ነው» በማለት ሳንቾ ምክሩን ተወና እንዲህ ሲል ተረቱን ቀጠለ። እንግዲህ ኢስትራማዱራ በሚባል አገር አንድ ጊዜ አንድ ፍየል አርቢ ይኖር ነበር ። ይህም ማለት ፍየሎችን የሚጠብቅ እረኛ መሆኑን ነው ። የሆነው ሆኖ የኔ ተረት እንደሚለው ሰውየው ፍየል አርቢ ወይም የፍየሎች እረኛ ቢሆንም ባይሆንም ስሙ ሎፔ ሩዌዝ ይባላል ። ይህም ሎፔ ሩዊዝ የሚባለው እረኛ ቶራልቫ የምትባለዋን እረኛ አፍቅሮ ነበር ፥ ይህችም ቶራልቫ የምትባለው እረኛ ያንድ ባለ አሩት ከብት አርቢ ልጅ ነበረች ። ይህ ባለአሩት ከብት አርቢ እዚህ ላይ ዶን ኪሾት አቋረጠው ። አንተ ተረትህን በዚህ ዓይነት ፈሊጥ አንዱን ነገር ሁለት ጊዜ እየደጋገምህ የምት አወራው ከሆንክ በሁለት ቀን እንኳ ልትጨርሰው አትችልም ማለት ነው ። ስለዚህ ሁሉንም አከታትለህ በመናገር እንደብ ልህ ሰው አድርገህ ተርተው ። አለበለዚያ ግን ብትተወው ይሻ ላል » አለው ።

«በኔ አገር» ሲል መለሰ ሳንቾ «ተረቶች ሁሉ በዚህ ዓይ ነት ፈሊጥ ነው የሚተረቱት ። እኔ በሌላ አኳኋን መተረቱን አላውቅበትም ። እንዲሁም ደግሞ ያልተለመደውን አዲስ ፈሊጥ እንድከተል መፈለግዎ የተገባ አይደለም» አለው ።

«አንተ እንደፈለግኸው አድርገህ ተርት ፤ አለ ዶን ኪሾት» «መቸም እድሌ አልሰማም እንድል አልፈቀደልኝምና በል» ቀጥል ።

«እንግዲህ የተወደዱት የነፍሴ ጌታ ሆይ! ይስሙኝና ልን ገርዎት» ሲል ቀጠለ ሳንቾ ቅድም እንዳልኩት ሁሉ ይህ እረኛ እረኛይቱን ቶራልቫን አፍቅሮ ነበር ። ይህችም እረኛ ወፍራም ረጅም ፤ ደንደሮ ፤ ኃይለኛ ፤ ስለሆነች በሁኔታዋ ከሴትነት ይልቅ ወደ ወንድነቱ ታደላ ነበር ። ይህም ሆኖ ጥቂት ሪዘች ነበራት ። ዋ ! ልክ አሁንም ባይኔ ላይ ትታየኛለች » ።

«እንግዲያውማ ታውቃታለህ ማለት ነዋ?» ሲል ጠየቀው ዶን ኪሾት ።

«የለም ማወቅስ አላውቃትም» ሲል መለሰ ሳንቾ «ዳሩ ግን ተረቱን ያወራልኝ ሰው ድርጊቱ ፍጹም እውነተኛ ነው ስላለኝ እኔም ለሌላ ሰው በማወራበት ጊዜ ሁሉንም በዓይኔ እንዳየሁት አድርጌ ለማረጋገጥ እችላለሁ ። ስለዚህ በጊዜ ብዛት መቸም ዲያብሎስ ለክፋት ሥራ የማይተኛና ጅራቱን በየቦታው የሚወትፍ በመሆኑ የእረኛውና የእረኛይቱ ፍቅር ወደ ጠብ እንዲለወጥ አደረገ ። የጠባቸውም ምክንያት አዋላቶች እንደሚሉት እሷ እጅግ የሚያንገፈግፍና ከመጠን ያለፈ ቅናት እንዲያድርበት አድርጋ ስለቀለደችበት ነው ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጠባቸው በጣም እየከረረ ስለሄደ እረኛው በተሰማው የጥላቻ ስሜት ተስፋ ቆረጠ የእሷን ዓይን ለማየት ወደማይችልበት አገር ለመጥፋት ወሰነ ። ቶራልቫ ግን ሎፒዝ አንቅሮ እንደተፋት አወቀችና ከዚህን ቀን በፊት ችላ ትለው የነበረችውን እንደገና የሱ ፍቅር ገነነባት ።

«ሴቶች ሲባሉ በሙሉ ጠባያቸው ይሽው ነው» አለ ዶን ኪሾት «የሚያፈቅራቸውን ይጠሉና የሚጠላቸውን ያፈቅራሉ ጠባያቸው ባካና ስለሆነ አይፈረድባቸውም» በል ቀጥል ሳንቾ ።

ሳንቾም ቀጠለ «በዚህም ምክንያት እረኛው ቁርጥ ሃሳቡን በገቢር ላይ ለማዋል ሲል ፍየሎቹን ሰበሰበና እየነዳ የኤስትራ ማዱራን ሜዳ አቋርጦ ወደ ፖርቱጋል ግዛት ለመግባት ተሰደደ ። ቶራልቫም ይህን ነገር በማወቋ ምርኩዝ ከዘራዋን ይዛ ጫማ ሳታደርግ ሻንጣዋን አዝላ በዚህም ሻንጣ ውስጥ አንድ ስባራ መስታወትና ግማሽ ሚዶ ፣ የጉንጭ ቀለም የያዘ መዳይ ነበረበት ። ዳሩ ግን በውስጡ ያፈቀደው ዕቃ ቢኖርበትም ይህን ሁሉ ዝርዝር ለመተንተን ጊዜ ስለማላገኝ ዋና ዋናውን ብቻ አወራለሁ ። በዚህ አኳኋን እረኛው መንገዱን ሲቀጥል እሷም ዱካውን ይዛ ስትከተለው ከነመንጋዎቹ ጓዲያና ጅረት ደረሰ ። ይህም ጅረት በዚያን ወቅት አለመጠን ሞልቶ ከመውረጁው መልካ ተርፎ ፈረሰኛው ሲያናጥር ይታይ ነበርና በዚያን ጊዜ

በደረሰበት ዳርቻ እሱንና ፍየሎቹን ወዲያ ማዶ ለማሻገር የሚችል ታንኳ ሆነ ጀልባ ጀልበኛም ስላልነበረ በጣም ተበሳጨ ። ምክንያቱም ቶራልቫ ተከታትላው መምጣቷንና ልትደርስበትም ምን ያህል እንዳልቀራት በማወቁና እንዲሁም የደረሰችበት እንደሆነ በልመና በለቅሶ እንደምታስቸግረው በማመኑ ነው ። በዚህ ሥጋት ላይ ሆኖ የጅረቱን ዳር ለዳር ሲቃኝ እነሆ አንድ አሳ አጥማጅ አንዲት ታንኳ ላይ ተቀምጦ ሲቀዝፍ አየው ። ይህችም ታንኳ በጣም ትንሽ በመሆኗ ለአንድ ሰውና ለአንድ ፍየል የሚሆን ቦታ በስተቀር ትርፍ ለመያዝ አትችልም ነበር ። የሆነው ሆኖ የማይቀር ነገር ስለሆነበት ሦስት መቶ ፍየሎችና እሱን ጭምር በተራ እንዲያሻግርለት ከባለታንኳው ጋር ተዋውሎ ተከራየ ። ከዚህ በኋላ ባለታንኳው በታንኳው ውስጥ ገብቶ አንድ ፍየል አሳፍሮ አሻገረ ፤ ከዚያም ተመልሶ ሁለተኛዋን ፍየል አሻገረ ፤ እንደገና ደግሞ ተመለሰና ሶስተኛዋን አሻገረ ፤ እንግዲህ እዚህ ላይ ጌታዬ ከአሁኑ ጀምረው ይጠንቀቁና አሳ አጥማጁ ተራ በተራ የሚያሻግራቸውን ፍየሎች ሁሉ አንድ ባንድ እየቆጠሩ ሂሣቡን አስታውሰው እንዳይዙ ። ይህንንም ማለቴ ከአቆጣጠር ላይ ተሳስተው አንዲት ፍየል ቢያበልጡ ወይም ቢያሳንሱ ተረቱ ተፈጸመ ማለት ነው ። ምክንያቱም በኔ በኩል ቁጥራቸው በትክክል ካልተነገረኝ በስተቀር አንዲት ቃል እንኳ ጨምሬ ለመቀጠል የማልችል በመሆኔ ነው ።

«እነሆ እንግዲህ ምን ብዬ ነበር ፤ ከጅረቱ ወዲያ ማዶ ያለው የፍየሎች መራገፊያ ዳርቻ በጣም አረንቋና ጥቅ የሞላበት ስለሆነ አሳ አጥማጁ ፍየል ባሻገረ ቁጥር ከታንኳው ላይ አውርዶ በጫንቃው ተሸክሞ ከደረቅ ሥፍራ ለማድረስ በጣጡ ውስጥ ሲዳክር ውሎ አድሮ እስኪመሰስ ድረስ ጊዜ እየፈጀበት ይዘገይ ነበር ። ይህም ሆኖ አንድ ፍየል አድርሶ ተመለሰና እንደገና አንድ ፍየል አሻገረ ፤ ቀጥሎም አንድ ደገመ አሁንም አንድ ጨመረ.....»

ዶን ኪሾት በሽቀና እንዲህ ሲል አቋረጠው ፤ «ስማኝ ሳንቾ በዚህ አኳኋን መሄድህንና መመላለስህን ተወውና ፍየሎቹን ሁሉ ጠራርጎ አሻገራቸው ብለህ ንገረኝ ። አለበለዚያ ግን በመሄድና

በመመለስ የምትቀጥል የሆንክ እንደሆነ ተረትህን ለመጨረስ አንድ ዓመት ሙሉ ብትመላለስም ላይበቃህ ነው» አለው ።

«እረ ለመሆኑ እስካሁን ድረስ ምን ያህል ፍየሎች ወዲያ ማዶ እንደተሻገሩ እስተ: ይበሉ የቆጠሩትን ይንገሩኝ?» ሲል ጠየቀ ሳንቾ ።

«እንጃልህ ምን አውቅልሃለሁ» ሲል መለሰለት ዶን ኪሾት ።

«ይህም ሆኖ » አለ ሳንቾ «የተሻገሩትን ፍየሎች ተጠን ቅቀው ይቁጠሩ ብዬ ነግሬዎት ነበር ፤ እንግዲህ አሁን ተረቴ ስለአከተመ በማናቸውም አኳኋን ቢሆን ወደፊት ለመቀጠል አልቻልኩም» ።

«ምን ማለትህ ነው» አለ ዶን ኪሾት «ተራ በተራ የተሻገሩትን ፍየሎች ቁጥር በትክክል ማወቅ ይህን ያህል ለተረትህ መቀጠል እስፈላጊ ነውን? አንድ ፍየል እንኳ ቢሳሳት ተረቴ ላይቀጥል ነውን ?»

«አዎን በርግጥ እንዲሁ ነው» አለ ሳንቾ ምክንያቱም እኔ ምን ያህል ፍየሎች እንደተሻገሩ ይንገሩኝ ብዬ በጠየቅሁዎት ጊዜ እርስዎ ደግሞ እንጃልህ አላውቅም ብለው ሲመልሱልኝ ልክ በዚያኑ ሰዓት ወደፊት የቀረው ተረት ሁሉ ባንድ አፍታ ከት ውስታዬ ውስጥ እልም ብሎ ሲጠፋ ተሰማኝ ። ይህም ተቋርጦ የቀረው ተረት በእውነቱ በጣም አስቂኝና በጣምም ተፈላጊው ክፍል እንደነበረ አረጋግጥልዎታለሁ ።

«ያም ሆነ ይህ» ተረትህ ተፈጸመ ማለት ነዋ ፤ ሲል ዶን ኪሾት ጠየቀው ።

«አዎን እንዳልታደለችው እናቴ ሞት ተፈጽሟል ። አለው ሳንቾ ።

ዶን ኪሾትም እንዲህ ሲል መለሰለት «ይህ እስካሁን ድረስ የዘባረቅኸው ተረት ወይም ታሪክ ምን እንደምትለው እንጃ ልህ በዚህ ዓለም ላይ ምንጊዜም ታስቦ የማይታወቅ በጣም አሪ

ታዊ በመሆኑ በዚህ ዓይነት ፈሊጥ ማውራትን ጀምሮ ወዲያው ደግሞ ከወገቡ ላይ እድርሶ ተቋረጠ ማለት ከቶ ተሰምቶና ታይቶ የማይታወቅ ወደፊትም ሊሰማና ሊታይ የማይችል መሆኑን አረጋግጥልሃለሁ ።

ምንም እንኳ ባንጐልህ ውስጥ ካለው ዕውቀት ከዚህ የተሻለ ፍሬ ነገር ይገኝበታል ብዬ መጠባበቅ ባይገባኝም ቅሉ ይህ መላቢስ የሆነው አተራረትህ ሊያስደንቀኝ አይችልም ። ምክን ያቱም ምናልባት እነዚህ ያለማቋረጥ የሚደውሉት አደንንቋሪ ድምጾች አንጐልህን አቃውሰውት ይሆናልና ነው ።

«ይህም ያሉት ሊሆን ይችላል» ሲል መለሰ ሳንቾ «ዳሩ ግን በተረቴ ጉዳይ ላይ ከእንግዲህ ወዲህ ልናገረው የምችለው አን ዳች ነገር እንደሌለ አውቄዋለሁ ። ምክንያቱም የተሻገሩት ፍየ ሎች ቁጥር በተሳሳተ ጊዜ ልክ እዚያው ነጥብ ላይ ተጐርዶ የሚያልቅ ስለሆነ ነው» አለው ።

«ሳንተ እንደመሰለህና እፈለግኸው ቦታ ላይ ብትጨርሰውም የተረትህ መቋረጥ እኔን አላስቸገረኝም ። ይልቁንስ ያንተን ትቼ እስ ቲሮንዚናንቴ ለመንቀሳቀስ ይችል እንደሆነ ልሞክር» ካለ በኋላ እንደገና ሮንዚናንቴን ኩርኩሮ ለማንቀሳቀስ ሞከረ ፤ ዳሩ ግን ፈረሱ የታሠረው በደንብ ተጠፍሮ ነበርና ኩርኩራው ሲሰ ማው አንድ ጊዜ ሽቅብ ዘለለና ተመልሶ እንደቀድሞው ቆመ ።

ይህም በሚሆንበት ጊዜ ወቅቱ ወደ ንጋቱ ስለተቃረበ የማ ልዳው ቅዝቃዜ ስሜት ይሁን ወይም እራት ላይ ሆድ የሚያ ለስልስ ምግብ በልቶ ይሆን ወይም ደግሞ የተፈጥሮ ፍላጐት አጣድፎት ይሆን (ይበልጥ የሚታመነው ይኸኛው ነውና) ያም ሆነ ይህ ሆዳባሻው ሳንቾ ሴላ ዘመድ ወይም ወዳጅ ስለ ርሱ ተወክሎ ሊፈጽምለት የማይችለው ጉዳይ መጣበት ። መቼም ወደሥራ አካላቱ የገባው ፍርሃት እጅግ የበረታ በመሆኑ ከጌታው ጐን ያንዲት ጣት ማሳረፊያ እርቀት ያህል እንኳ አልተነጠ ለም ነበርና በዚህ ምክንያት ጉዳዩን ለመፈጸም ሲል እስከዚ ያን ሰዓት ድረስ የያዘበትን የቀኝ እጁን ከቀዳማው ላይ አው ርዶ አንዳች ኩሽታ ሳያሰማ በቀስታ እጁን ሰድዶ ሱሪውን የታ ጠቀበትን የጥብጣብ ሽምቀቆ ከሚላላት በስተቀር ከዚህ የተ

ሻለ ሌላ ብልሃት ሊያገኝ አልቻለም ። ሱሪውም ሌላ የሚተዘ ተብ ማሰሪያ የሌለው በመሆኑ ወዲያውኑ ላልቶ ቁልቁል ወረ ደለትና እንደ እግረ ሙቅ እግሩ ላይ አረፈ ። ቀጥሎም የተቻ ለውን ያህል ሸሚዙን ከፍ ከፍ አደረገና ቁጢጥ ለማለት ዝቅ ሲል ሁለት ጥንድ የጦላ ላጥታ ወደ አየር ተኮሰ ። በዚህም ጊዜ ከሥጋት ለመገላገል ያህል የመጀመሪያው ዋናው አዋጅ ነጋሪ በመውጣቱ የተገላገለ ሊመስለው እነሆ ደግሞ ሌላ የባሰ ጣጣ ተከታትሎ ደረሰ ። ይኸውም ዕቃው የሚራገፍበትን መን ገድ ያለ ጓጓታ ለማለፍ አለመቻሉን ስለአወቀው ጥርሱን ነከሰ። ትክሻውንም ገጠመ ፤ የተቻለውን ያህል ትንፋሹን ዋጠ ። ዳሩ ግን ይህን ሁሉ ጥንቃቄና ጭንቀት ቢያደርግም ቅሉ ዕድል አሳገዘውም ነበር ። ምክንያቱም በመጨረሻው ውጤት ከበድ ያለ ድዝታ አምልጠ ወጣ ፤ ይኸው በሰውነቱ ውስጥ ታላቅ ፍርሃት ካሳደረበት የጉርምርምታ ድምጽ ጋር በምኑም የማ ይመሳሰል ነበር ።

ዶን ኪሾት ይህንኑ ድምጽ በሰማ ጊዜ እንዲህ ሲል ጠየ ቀው ፣ «ሳንቾ ይህ የሚተኩሰው የምን ድዝታ ነው?» አለው ።

ያም መለሰ «ጌታዬ ሆይ ! በውነቱ ምን እንደሆነ አላወ ቅሁትም ። ዳሩ ግን አንዳች አዲስ ነገር በእርግጥ መኖር አለ በት ። ከዚህም በስተቀር አጋጣሚና አደጋ መዝነላ በሚጀም ርበት ጊዜ በእንቅርት ላይ ጀሮ ደግፍን ያስከትላል» አለውና እንደገና እድሱን ሞከረ ፤ ፈተና አደረገ ። በዚህም ጊዜ አገፋፉ ላይ ስለቀናው እንደበፊቱ ድዝታ ሳያሰማ በጣም ወጥሮ ያስጨነቀውን ጭንት አራግፎ ነፃ ለመሆን ቻለ ። ዶን ኪሾት ግን በጀሮው ከሰማው ይልቅ ባፍንጫው ያሸተተው ማጠንት ምንነቱን ይበልጥ ስለአሳመነውና ያኛውም አጠባቡ ተለጥፎና ተሰፍቶ የሚገኝ በመሆኑ ከታች ወደ ላይ የሚነሳው የትኩስ ጢስ ብናኝ አንዳች ነገር ሳያግደው በቀጥታው መስመር ወደ አፍንጫው ያርሶ ስለአጠነው በቶሎ አፍንጫውን በጣቱ ያዘና በመነፋነፍ እንዲህ ሲል ጠየቀው።

«ሳንቾ እንደምስማው አለመጠን የፈራህ ይመስለኛል?» አለው ።

«አዎን መፍራትስ በጣም ፈርቻለሁ ፤ ለመሆኑ እርስዎስ ከቅድሙ ይልቅ አሁን መፍራቴን እንደምን አድርገው ተረዱት» ሲል ጠየቀ ።

«ከቅድሙ ይልቅ አሁን የምታሰማው ሽታ በውነቱ የቢ ርሞኬ አይደለም ? ።

«ላይሆንም ይችላል» ሲል መለሰ ሳንቾ «ዳሩ ግን ጥፋቱ የኔ አይደለም ፤ በዚህ በበረሃ ቀበሌ ውስጥ ጊዜ አለጊዜ አስ ከትለው የሚያንከራትቱኝ እርስዎ በመሆንዎ ጥፋቱ የርስዎ መሆን አለበት » አለው ።

«እባክህን ወዳጄ ወግድልኝ ከዚህ» አለ ዶን ኪሾት ፤ ጣቱን ከአፍንጫው ላይ ሳያነሳ «ከአጠገቤ ሦስት ወይም አራት እር ምጃ ያህል ፈቀቅ ብለህ ጉዳይህን ፈጽም ። ከዛሬ ጀምረህ ወደ ፊት ደንበኛውን ቦታህን ፈልገህ ያዝ ። ለኔም የሚገባኝን የክ በሬታ አሰተያየት አድርግልኝ ። ይህ የአክብሮት መጓደል ካንተ ጋር ዘወትር በጓደኝነት መንፈስ እየተናገርሁ ፊት በመስጠቴ የተ ገኘ ፍሬ ነው» አለው ።

«አሁን» ሲል መለሰ ሳንቾ «እኔ ማድረግ የማይገባኝን ነገር ያደረግሁ እንደመሰለዎት ተረድቼዋለሁ» አለው ።

«አፍህን አሳርፍና ፈቀቅ በል ! አለበለዚያ ወዮልህ አለው ዶን ኪሾት ።

ይህንንና ይህን የመሰለውን ንትርክ እየተነታረኩ ጌታና አሽከር እንደተጋሰሱ ሴሊቱን አዋገዱት ።

ዳሩ ግን ሳንቾ ሌሊቱ ሊነጋ መቃረቡን ተመለከተና በፍጥነት የሮንዘናንቴን እሥር ፈትቶ የራሱንም ሱሪ ታጠቀ ። ሮንዘና ንቴም የእግሮቹ ነፃ መሆን በተሰማው ጊዜ ምንም እንኳ በተ ፈጥሮው ፎሌ ባይሆን እግሩን ለማፍታታት ያህል ጥቂት ፈነ ጫጨ ። ይህም ሲባል ደንገላሳ አይደለም ምክንያቱም እሱን ለማኳሰስ ሳይሆን ደንገላሳ የሚባል ነገር ጨርሶ የማያውቅ በመ ሆኑ ነው ። ዶን ኪሾትም ሮንዘናንቴ መነቃነቁን አየና ይህን

ከፊቱ እያጉረመረመ የሚዝትበትን አደጋ ለመግጠም የሚያ በረተታ ምልክት መሆኑን ተረዳው ።

በዚህን ጊዜ ጀንበር ጮራዋን መፈንጠቅ ስለጀመረች እነሱም በዙሪያቸው የከበባቸውን ነገር በግልጥ ለማየት ቻሉ ። እዚህ ላይ ዶን ኪሾት በጣም የከበደ ጥላ ያላቸው የብር ብራና የሰሰ ዛፎች ሥር የሚገኝ መሆኑን አወቀ ። ዳሩ ግን የፏፏቴው ጉርምርምታ አውንም ፀጥ አለማለቱን ሰማ ። ምክ ንያቱም ምን እንደሆነ ሊገባው አልቻለም ነበር ። ስለዚህም ያላንዳች ዝግያቴ ለሮንዜናንቴ ኩርኩራ አሰማውና ከሳንቾም ጋር እንደገና ተሰነባበተና ካሁን ቀደም እንዳስታወቀው ግፋ ቢል እስከ ሦስት ቀን ድረስ እዚሁ እንዲጠብቀው ነገረው ። ከሦስት ቀንም በኋላ ያልተመለሰ እንደሆነ ግን በዚህ አደገኛ መጋፈጥ ላይ ሕይወቱን እንዲያሳልፍ በተፈጥሮ የተወሰነ መሆ ኑን እንዲያረጋግጥ አሰረዳው ። እንዲሁም በርሱ ስም ሆኖ ለእ መቤት ሆይ ዱልቼኒያ ሊያደርስ የሚገባውን መልዕክት ደጋ ግሞ አሰጠነቀቀው ። ስለውዝፍ ደመወዙም ጉዳይ በፍጹም እን ዳያስብ ተሰፋ ሰጠው ። ምክንያቱም ከአገሩ ከመውጣቱ በፊት ባደረገው ኑዛዜ ላይ በተጻፈው መሠረት በጋሻ ጃግሬነት አገ ልግሎት ላይ በሚቆይበት ጊዜ መጠን ታስቦ የሚደርሰው ድርሻ አንድም ነገር ሳይቀርበት የሚከፈለው መሆኑን የምነት ቃሉን ሰጠው ። ምናልባት ደግሞ እግዚአብሔር በሠፊው ምሕረቱ ከዚህ ከብርቱ አደጋ አትርፎ በሰላምና በሕይወት የመለሰው እንደሆነ ከብዙ ጊዜ አንስቶ ተስፋ የሰጠው ደሴት አውንም ቢሆን ያላንዳች ጥርጥር የራሱ ገንዘብ መሆኑን ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ እርግጠኛ እንዲሆን ነገረው ።

ሳንቾም ይህን ልብ የሚቀሰቅስ (የደንቆን) ጌታ ንግግር በሰማ ጊዜ ሃዘን ስለአንሰፈሰፈው እንደገና በለቅሶ እየተንሰቀ ሰቀ እርሱም በበኩሉ በዚህ አደገኛ ግጥሚያ ላይ ለመገኘትና እስከመጨረሻው ወሰን ድረስ ጌታውን ተከትሎ አብሮ ለመ ሞት ቁርጥ ሃሳብ ማድረጉን ገለጠለት ።

ሆኖም የዚህ እውነተኛ ታሪክ ደራሲ ይህን አስተያየት በማ ስተባበል ይህ የሳንቾ ለቅሶና አብሮ የመሞት ቁርጥ ሃሳብ ሊሆን

የቻለው ከመልካም ቤተሰብ ተወልዶ ያደገ በመሆኑ ወይም ደግሞ ከመሠረቱ የሐቀኛ ልጅ በመሆኑ በርህራሄ ስሜት ተገፋፍቶ ነው እንጂ በቀጥታ ከደፍረት መንፈስ የመጣ ቁርጥ ሐሳብ አይ ደለም በማለት ተከራክሯል ። ስለዚህ ይኸው ያልተጣራው የር ህራሄ ስሜቱ የዶን ኪሾትን ልብ ሊያገራው ቢችልም ተግባሩን የሚያስተው አንዳች ማመንታትና የሃሳብ ገመምተኛነት ዝን ባሌ እንዲፈጠርበት ለማድረግ አልቻልም ነበር ። እንዲያውም አፍራሻውን የደፋርነት ወኔውን የተቻለውን ያህል አነቃቅቶ የውሀው ድንፋታና የመውቀሪያው አስተጋቢ ድምጽ የሚመጣ መስሎ በተሰማው አኳያ አመራ ። ሳንቾም እንደወትሮው ልማዱ ያቺን የክፉም ሆነ የደግ እድሉ ተካፋይና የልብ ጥብቅ ጓደ ኛው የሆነችውን አህያውን በሉከዋ እየሳበ በስተኋላው ተከ ትሎ በንዚያ ብርበራ ዛፎች መካከል አቋርጠው ደህና ርቀት መንገድ ከሄዱ በኋላ ረዘም ወዳለ ቋጥኝ የሚዘረጋ መስክ ላይ ደረሱ ። በቋጥኙም አናቃ መካከል ከየመመንጫው ፉካ ውስጥ ከመጠን ያለፈ ይዘታ እየተፋ የሚወጣውን ፏፏቴ አዩ ። ከቋ ጥኙም ግርጌ ካንድ ደልዳላ ሥፍራ ላይ አንድ የወለለቀ አሮጌ ቤት አገኙ ። ይህም ቤት ከቤትነት ይልቅ በውነቱ የጥንት ፍራሽ የሚመስል ነበር ። እዚያም አጠገብ እንደደረሱ የማያባራው ወቃሪ ድምጽ የሚወጣው ከዚያው ከቤቱ ውስጥ መሆኑን ለማ ወቅ ቻሉ ። ሮንዜናንቴም የፏፏቴውን መንቧቸትና የወቃሪውን ድምጽ ማደንቆር በሰማ ጊዜ ፉር እያለ ደንብሮ ቆመ ።

ዶን ኪሾትም ፈረሱን በተቻለው መጠን እያባበለ ቀስ በቀስ እያለ ወደ አሮጌው ቤት ቀረበ ፣ ከዚያም በኋላ ከዚህ እጅግ አስፈሪ ከሆነው አደጋ በድል አድራጊነትና በሕይወት እንዲመለስ የእ መቤቱን የዱልቼንያን ውቃቢ በሙሉ ልቡ ተለማመነና እግረ መንገዱንም ውለታውን እንዳይረሳው ተግጠና በቁርጠኝነት መንፈስ ወደፊት ቀጠለ ። ሳንቾም ከአጠገቡ አልተነጠለም ነበ ርና አልፎ አልፎ የተቻለውን ያህል አንገቱንና አስተያየቱን እያስረዘመ በሮንዜናንቴ እግር መካከል አሸጋግሮ በመመልከት ይህን ያህል ታሳቅ ፍርሃት በሆዱ ውስጥ ለማሳደር የቻለውና አሰጨንቆም የያዘው ድብልቅልቅ ያለ ጩኸት ምናልባት ሊከ ሰትለት ይችል እንደሆነ በማለት ይመራመር ጀመር ። በማምት

አንድ መቶ የሚሆን እርምጃ ሄደው የአንዲት ገብታ አግድ መት ካለፉ በኋላ ለነሱ አስፈሪ ጉርምርምታ ሆኖ የተሰማቸው እና ሌሊቱን በሙሉ ሲያስጨንቃቸው ያደረው የዚህ አደንቋሪ ጩኸት ምክንያት በግልጥ ተከስተላቸው ። ይኸውም (አንባቢ ሆይ ቅር አይበልህና) በውሀ ኃይል የሚንቀሳቀሱ የስድስት ወፍጮ መጅት መፋጨት ስለሆነ እየተከታተለ በሚያስገመግመው ዣርዳፊ ድምፃቸው ያንን ጉርምርምታ ሲፈጥሩ መኪናውን የሚያንቀሳቅሰው ፏፏቴ ደግሞ ከየቋጥኙ ጋር እየተደራገመ ሲወ ርድ በጅውታው ስለሚያስተጋባው መሆኑን ያላንዳች ጥርጣሬ ለማመን ቻሉ ። ዶን ኪሾት ይህን ሁሉ አሸባሪ ጉርምርምታ ለመፍጠር ምክንያት የሆነውን ነገር ባወቀ ጊዜ አለመጠን የማ ፈሩ ብዛት ኩምሽሽ ብሎ ጨፍ አከለ ። ሳንቾም ጠጋ ብሎ ቢመ ለከተው እንደኳሽ ሰው አንገቱን ከደረቱ ላይ ደፍቶ አየው ። ዶን ኪሾትም በበኩሉ ቀና ብሎ ሳንቾን ቢመለከተው በጌታው ሁኔታ ተደንቆ በሳቅ ታፍኖ ኖሮ በተቻለው መጠን ሳቁን ለመ ግታት ሲል ጉንጩን አሳብጦ ከንፈሩን ነክሶ አይኑን እያቁለ ጨለጨ ለመፈንዳት ደርሶ አየው ። ዶን ኪሾት ይህን በማየቱ ምንም እንኳ በሐፍረት የተሸማቀቀ ቢሆን ከመሳቅ ለመታ ገድ ስላልቻለ አስቀድሞ መሳቅ ግዴታ ሆነበት ። ሳንቾም ጌታው በጀማሪነት መንገዱን በከፈተለት ጊዜ እሱም በቋፍ ነበርና እስ ቲንፈራፈር ድረስ ከት ብሎ ሳቀበት ። የመሳቁም ኃይል እን ዳያፈነዳው በመሥጋት በሁለት እጁ አንዴ ወገቡን አንዴ ጉል በቱን መመርከዝ ግዴታ ሆነበት ።። በዚህ አኳኋን አራት ጊዜ ያህል እየሳቀ አባርቶ እንደገና ደግሞ እያስታወሰ በመጀመሪ ያው ዓይነት አሳሳቅ ሲንከተከት ቆየ ። ዶን ኪሾት ይህ የሳንቾ አሳሳቅ የፌዝ መሆኑ ገብቶት ገና ከቅድሙ አንስቶ ተዶርሮ ነበርና ሳንቾ ጌታውን በማሽሚጠጥ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ከሣቁ ጋር እያቀላቀለ ሲናገር በሰማው ጊዜ ነገሩ ወደ መሣረር አዘነበለ ።

ይኸውም ባለፈው ጊዜ በጉራና በፉከራ የተናገረውን ቃል በማስታወስ «ወዳጄ ሳንቾ እኔ በእግዚአብሔር ፈቃድ በዚህ በብ ረት ዘመናችን ውስጥ የተወለድሁት ያንን የወርቁን ዘመን ለማ ስነሳት መሆኑን ማወቅ አለብህ ። የጀግንነት ተግባሮችና ታላ

ላቅ ግጥሚያዎች ፣ አስፈሪ አደጋዎች ሁሉ በተለይ ለኔ የተደ ገሱ ናቸው» እያለ ነበር ።

ይህንንና ሌላውንም ዶን ኪሾት ያንን አስደንጋጭ እና አደንቋሪ ጉርምርምታ በሰማበት በመጀመሪያው ጊዜ በፉከራ መንፈስ የተናገረውን ቃል እየመላለሰ ከሳቁ ጋር እያቀላቀለ በመ ተቸት አፈዘበት ። ዶን ኪሾትም ሳንቾ እንዳሳገጠበት በመገን ዘብ ገና ከቅድሙ አንስቶ ኩርፊያ ላይ ነበርና ።

ወዲያውኑ ባንድ አፍታ ግልፍ ስላለው በቁጣ እንደነደደ ቦሩን እነሳና በዛቢያው ወገን ሁለት ጊዜ ጀለጠው ። በትሩ ያረፈው በጀርባው ላይ መሆኑ ቀርቶ ለጥቂት አናቱን አማኝ ቶት በነበን ኖሮ እስካሁን ድረስ ያገለገለበትን ደመወዙን ለወ ራሾቹ ካልሆነ በስተቀር ለሱ ለመክፈል አይጨነቅም ነበር ። ሳንቾም ከዚህ ከሳቁና ከቀልዱ የለቀመው ፍሬ መራራ መሆኑን ቀምሶ ስለተረዳውና ወዲህም ድንጥ ሰው በመሆኑ ጌትዬው እንደገና የዱላውን መጠን እንዳያበዛበት በመፍራት እንዲህ ሲል በብዙ ትሕትና አነጋገረው ።

« ጌታዬ ሆይ ተዳፍሬ በመሳቁ አጥፍቻለሁና አይቆጡ ፣ ይተውት ተቀናጥቼ ለቀልድ ያህል የተናገርሁ መሆኔን ይመ ኑኝ » አለው ።

«እርግጥ ነው አንተ መቀለድህ ነበር እኔ ግን አልቀለድ ሁም» ሲል ዶን ኪሾት መለሰለትና ንግግሩን በመቀጠል «እኽ አቶ ቀልደኛው ፣ በል እስቲ ልጠይቅህና ንገረኝ? እነዚያ የታ ዩት የወፍጮ መጅዎች መሆናቸው ቀርቶ እውነተኛዎቹ አደ ገኛ አጋጣሚዎች ሆነው ቢገኙ ኖሮ አስፈላጊውን ድፍረት ለማ ሳየት እና ግጥሚያም አድርጌ ተግባሬን በድል አድራጊነት ለማ ከናወን ራቴን የምመልሰው ኑሬአለሁን? ወይስ ደግሞ ፈረሰኛ በመሆኔ ምክንያት ይህ የሚሰማው ድብልቅልቅ የመገርደፊያ ወፍጮ መጅ ወይም የፏፏቴ ጉርምርምታ ድምጽ መሆን አለ መሆኑን እንዳውቅ አገዶድ ኖሮአልን? መቸም በውነቱ እንደማስታ ውሰው በሕይወቴ እርዝማኔ ውስጥ አስከዛሬ ድረስ እንዲህ ያለ ነገር አጋጥሞኝ አይቸም ሰምቸም ስለማላውቅ እንግዳ ነገር እንደ

ሚሆንብኝ ግልጥ ነው ። እንዳንተ ያለ ቀፎ ስቃይ ባላገር ግን ይህን ከመሳሰለው መሣሪያ ጋር አብሮ ተወልዶ አብሮ ያደገ በመሆኑ በቶሎ ሊለየው ስለሚችል አንተም በድምጹ ለይተህ ልታውቀው እንደምትችል አምናለሁ ። ዳሩ ግን የሚሆንልህ ከሆነ በል እስቲ እነዚህ ስድስት የወፍጮ መጅቶ በስድስት ጠርብ ጃሞዛዎች ለውጣቸውና አንድ ባንድ ወይም ሁሉንም አን ነት እየነጋጋህ ገፍትረህ በላዩ ላይ ጣላቸውና ይግጠሙኝ ። በዚያን ጊዜ ሁሉንም ወደ አየር እያንገሁ ሳልፈነቸራቸው የቀ ረሁ እንደሆነ የፈለግኸውንና የመስለህን ያህል እያፈዝህ ብት ስቅብኝ በጭራሽ ቅር አይለኝም ።

«ጌታዬ ሆይ ! መቆጣቱ ይብቃዎት ለዛሬው ጥፋቴ ይቅ ርታ ያድርጉልኝ ። እኔም ተዳፍሬ በመሳቄ ለክቡርነትዎ መስ ጠት የሚገባኝን ያክብሮት ወሰን እንዳለፍኩት አውቄአለሁ ። መቼም ታርቀናልና እባክዎን አንዴ ይፍቀዱልኝና እኔም በፍ ጅታዬ አንድ ነገር ልጠይቅዎት» እግዚአብሔር በምህረቱ ክዚህ አደጋ ሰውሮ እንዳተረፍዎት ሁሉ እንዲሁም ለወደፊቱ ከሌ ሎች ገና ተከታትለው ከሚመጡት አደጋዎች ያትርፍዎትና ይህ የዛሬውአጋጣሚና እሱም ያሳደረብን ታላቅ ፍርሃት ይህ ነንም ስል በተለይ እኔን እጅግ አድርጎ ያስፈራኝን ነው እንጂ እርስዎ እንደሆኑ ፍርሃት የሚባለውን እንኳንስ እሱን እራሱን መኖሪያ ቤቱ የት እንደሆነ ስለማያውቁት ነገሩን ሲመለ ከቱት የሚያስቅና ሊወራም የሚገባው አይመስልዎትምን? ሲል ጠየቀው ።

ዶን ኪሾትም መለሰ ፣ « ይህ የደረሰብን ነገር የሚያስቅ መሆኑን አልክድም ፣ ዳሩ ግን ሊወራ የሚገባው አይደለም ። ምክንያቱም ወሬውን ከሚሰሙት ሰዎች መካከል ሁኔታውን ከትክክለኛው መስመር ሳያዛንፉ በቀጥታ ለማስተላለፍ የሚ ችሉ ሐቀኞች ጥቂቶች ከመሆናቸው የተነሳ አንዳንዶቹ ወሬ ያዳ መቂ እየመሰላቸው የስሙትን ካልሰሙት ጋር እያዳቀሉና እያ ቀጣጠሉ ከውነተኛው ድርጊት አዘልለው ሌላ ትርጓሚና ፍቺ በመስጠት ታሪክ ጸሐፊዎችን ስሜን ወደሚያሰብር ስህተት ላይ እንዲደርሱ ያደርጓቸዋልና ለሰው አውራው ብዬ በፍጹም አልፈ ቅድልህም» አለው ።

ሳንቾም እንዲህ አለ ፣ «ክቡርነትዎ የጦርዎን ዛቢያ ለአ ናቴ አልመው ትከሻዬ ላይ በማሳረፍዎ ከትክክለኛው መስመር ሳይወጡ ስለቀሩ በሐቀኝነትዎ አመሰግንዎታለሁ ፣ እንዲሁም ለእግዚአብሔርና ለእኔም በፍጥነት ዘወር ብዬ አደጋው ማም ሳጥን ለአወቅሁት ምስጋና ይግባንና እንደርስዎ ዒላማ ቢሆን ኖሮ እስካሁን ድረስ ሌላ መኖሪያ ቦታ ለውጬ ነበር ። የሆነው ሆኖ የማያልፍ ነገር የለምና ይህን የዛሬውን ድርጊት « የሚ ያስቅና የማይወራ» ብለን ያስከተልነውን ጠንቅ በትዕግሥት እን ለፈው ። ከዚህም በስተቀር የዱሮ ሽማግሌዎች ሲተርቱ እንደ ሰማሁት « የማይወዱትን ሰው አይቆጡትም » ያሉት በመደ ብደቤ ሆድ እንዳይብሰኝ ያጽናናኛል ። ይህም ሆኖ ጥንት ታላ ላቆቹ ጌቶች በሚቆጡበት ጊዜ አንድ የስድብ ቃል አምልጧ ቸው አሽከሮቻቸውን የተሳደቡ እንደሆነ ቆየት ብለው ሙሉ ልብስ ካሣ ይክሏቸዋል ። ዳሩ ግን በዱላ ከተደባደቡ በኋላ ምን እንደሚከሱ አላውቅም ። ለኔ እንደሚመስለኝ ግን ዘዋሪ ፈረ ሰኞች ጋሻ ጃግሬአቸውን ከደበደቡ በኋላ ካሣውን አንድ ደሴት ወይም በረጋ መሬት ላይ የሚገኝ የተንጣለለ ሠፊ ግዛት ሳይ ሰጡዋቸው እንደማይቀሩ አምናለሁ » አለ ።

«ይህ ሊሆን የሚችል ነው » አለ ዶን ኪሾት ይህን አሁን ያልከውን ካሣ የምታገኝበት ጊዜ ላንተም የሚርቅ አይደለም ። አሁን ግን ለጊዜው ማናቸውንም የደረሰውን ሁኔታ እርሳውና እለፈው ። ግሳጼዬንም በትእግሥት በመቀበልህ አስተዋይ ሰው መሆንክን መዝኘዋለሁ ። አንተም እንደምትገነዘበው ሰው ሆኖ የተፈጠረ ሁሉ ከደም ፍላት የወጣውን ግልፍታ በመጀመ ሪያው ላይ ለመዳኘት ስለማይችል በአፍላው ጊዜ ከፊቴ ተገ ኝተህ በመመታትህ አትዘንብኝ፣ ዳሩ ግን ከዛሬ አንስተህ ወደ ፊት ከኔ ጋር እኩል ከመነጋገር እንድትቆጠብ በተቻለህ መጠን ተመከር ። እኔ ካነበብኳቸው ከብዙዎቹ የፈረሰኛነት ታሪክ መጻሕ ፍት ውስጥ እንዲህ እንዳንተ በሙሉ ስድነት ከጌታው ጋር የሚከ ራከርና ከእፍ የሚናጠቅ ጋሻ ጃግሬ መኖሩን የሚያሰረዳ ምዕራፍ አላገኘሁበትም ። እውነቴን ስነግርህ እስከዚህ ድረስ ባለጌ ለመሆን የበቃኸው ባንተና በኔ ጥፋት ነው ። ያንተ ጥፋት ነው ያል ኩህ የሚገባኝን ያህል በደንብ ስለማታከብረኝ ነው ። የኔ ጥፋት

ነው የምለው ደግሞ ይበልጥ እንድትአከብረኝ አድርጌ ስላላ ስለጠንኩህ ነው ። ስለዚህም ጉዳይ ምናልባት ሊገባህ ይችል እንደሆነ ሁለት ምሳሌዎች ጠቅሼ ላስረዳህ እፈቅዳለሁ ። ባለ ፈው ዘመን ጋላዲኖ የሚባለው የጋውላው አማዲስ ጋሻ ጃግሬ በአገልግሎቱ መልካምነትና በሰው አክባሪነቱ የፊርሜ ደሴት መስፍን ሆኖ ነበር ። ስለርሱም የትሕትና ጠባይ ታሪክ እንደ ሚመሰክርለት ከጌታው ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ ዘወትር ባር ኔጣውን አውርዶ በእጁ ይዘ እንደቱርከችና ዓረቦች የመከባበር ፈሊጥ ከደረቱ ጐንበስ ብሎ አንገቱን ደፋ አድርጐ ጌታው የሚ ነግረውን ያዳምጥ እንደነበር ተጽፏል ። ጋስባል የሚባለው የዶን ጋላዎር ጋሻ ጃጋሬ ደግሞ በጣም ዝምተኛ ከመሆኑ የተነሳ ይህ እጅግ አስደናቂ የሆነ ዝምታው እምን ወሰን እንደደረሰ ሃሳብ ለመስጠት ያህል በዚያ በተጻፈው እውነተኛና ሰፊ ታሪክ ውስጥ እሱ ከጌታው ጋር ሲነጋገር የተሰማው አንድ ጊዜ ብቻ መሆ ኑን ስትረዳው ያንተ ለፍላፊነት ባለመቶ ምላስ መሆንክን የሚ መስክር አይደለምን ? ስለዚህ በዚህ በሰጠሁህ ማስረጃ አስገን ዛቢነት እራስህን በራስህ ታገዝበህ ፣ በፈረሰኛና በጋሻ ጃግሬ በጌታና በአሽከር ፣ በገርና በጓባር መካከል የተራራቀ ልዩነት መኖሩን አውቀህ ጠባይህን ለማረም መጣጣር አለብህ ። ሁለ ታችንም ከእንግዲህ ወዲያ ልጓማችንን ስናላላ በበለጠ መከባበ ርና አንጋፋነት መተያየት ይገባናል ። ምክንያቱም ባንተ የም ናደድበት ስበብ ማናቸውም ዓይነት ቢሆን «የሸክላ ድስት ዘወ ትር በሥጋት » እንደሚባለው ነውና ተጠንቀቅ ። ተስፋ ያደረ ግህልህ ወሮታና ችሮታ ጊዜው ሲደርስ እንደምፈጽምልህ እመነኝ ። ምናልባት ጊዜው ርቆ ቢዘገይ እንኳ አስቀድሜ እን ደነገርኩህ ደመወዝህ እንደማይቀርብህ እርግጠኛ ሁን ።

«ክቡርነትዎ የነገሩኝ ሁሉ መልካም ነው» ሲል መለሰ ሳንቾ « ዳሩ ግን ለማወቅ የምፈልገው ምናልባት የተስፋው መፈጸሚያ ጊዜ እንዳሉት ዘግይቶ ደመወዜን በማግኘት ብቻ የምወሰን የሆንኩ እንደሆነ በዱሮው ዘመን የዙዋሪ ፈረሰኛ ጋሻ ጃግሬ በወር ደመወዝተኛነት ወይም ደግሞ እንደቀን ሠራተኛ በቀን አገልግሎት ሂሣብ ምን ያህል ደመወዝ ይከፈለው ኖሯል ?

«እኔ እንደማውቀው» ሲል መለሰ ዶን ኪሾት «የዱሮዎቹ ጋሻ ጃግሬዎች ስለአገልግሎታቸው ዋጋ ወሮታ ይከፈላቸዋል እንጂ የተወሰነ ደመወዝ ተቆርጦላቸው በወር ወይም በቀን የሚ ከፈላቸው አይመስለኝም ። እኔ በኑዛዜው ወረቀት ላይ በደመ ወዝ ስም ድርሻህን ለይቼ በማህተሜ አጽድቄ እቤት የተው ኩበት ምክንያት ምናልባት ካንድ ቀን አንድ ቀን ሊደርስብኝ በሚችለው ድንገተኛ አደጋ የሞትኩ እንደሆነ ያንተ አገልግ ሎት ያለ ዋጋ እንዳይቀር ለመጠንቀቅ ስል ነው ። ይህንንም ጥንቃቄ እንዳደርግ ያሳሰበኝ በዚህ አደገኛ በሆነው ዘመናችን ውስጥ ዙዋሪ ፈረሰኞችን ምን ዓይነት ዕድል ሊያጋጥማቸው እንደሚችል ደህና አድርጌ ባለማወቄ የተነሳ በዚህ በጥቂት ነገር ነፍሴ በሌላው ዓለም በዕዳ እንድትጠየቅ ስለማልፈቅድ ነው ። ውድ ሳንቾ ! በነዚህ በሁለቱ ዓለሞች ላይ ዙዋሪ ፈረሰኞች ከሚጠየቁበት የበለጠ አደገኛ ግዳጅ እንደማይገኝ ልታውቀው ይገባሃል » አለው ።

«ይህ የተረጋገጠ እውነት ነው » አለ ሳንቾ « የመገርደፊያ ወፍጮ መጀች ጉርምርምታ እንኳ ክቡርነትዎን የመሰለ የጀግና ዙዋሪ ፈረሰኛ ልብ ለማናወጥና ለማመሳቀል ሲችል ዕድሜያ ችሁ ሁሉ ከአደጋ ጋር የተቆራኘ መሆኑን ለማስረዳት ይሽው ብቻ በቂ ነው ። የሆነው ሆኖ ከእንግዲህ ወዲህ የክቡርነትዎን ክብር በሚነካ በማናቸውም ጥፋት ላይ እንደማልወድቅ ፣ በመ ቀለድም ስሜት አንዳች ነገር እንደማልተነፍስ ፣ ብተነፍስም እንኳ አንድ ጌታ ሊከበር በሚገባው መንፈስ ብቻ መሆኑን ። አረጋግጥልዎታለሁ» አለው ።

«በዚህ መንፈስ ከተመራህ » ሲል መለሰ ዶን ኪሾት «ከወ ላጆች ቀጥለው የሚከበሩት ጌቶች ስለሆኑ ከነሱ በምትቀበለው ምርቃንና ቡራኬ ዕድሜህ ረዝሞ በደስታና በተድላ ትኖራለህ» አለው ።

ምስጋና

ከተረጉምኩ በኋላ የእንግሊዝኛውን ሐረግና የአማርኛውን አሰካክ ገጽ በገጽ ያለአንዳች ድካም የተመለከተልኝን ጓድ ታደሰ ወልዴን አመሰግናለሁ ።

አ. ተ. ወ. መ.

Pdf by Meysor Bro(Ppp)

ከታደሰ ወልዴ

ስለመጽሐፉ ትርጉም የተሰጠ አስተያየት

ልዩ ግንዛቤ በሚል ከላይ የተገለፀው በትክክል ከሰርቫንቲስ መጽሐፍ መቅድም ከሳሙኤል ፑትናም በቀጥታ የተተረጐመ ነው ። ይህንኑ ትርጉም አቶ አስፋው ተፈራ (ተርጓሚው) ምናልባት ታማኝ ሁኜ ተርጉሜ እንደሆነ ወይም የአገር አነጋገር ፈሊጥ ዘልዬ እንደሆነ በማለት በሐምሌ 1975 ካለው የሥነጽሑፍ ሥራ ውስጥ ይህን የዶን ኪሾትን የመጀመሪያ ክፍል መጽሐፍ እንግሊዝኛውንና የአማርኛውን ትርጉም ሰጠኝ ። የትርጉሙን ትክክለኛነት ለመመልከት ማመሳሰሉ ብዙ ጊዜ ከፈጀብኝ በኋላ ተርጓሚውን እኔ ግር ባሉኝ ሐረጐች አተረጓጐም ላይ ተወያየን ። በትርጉሙ አሠራር የተርጓሚው ስሜት ሳይነካ ለማረም በመጋበዜ እጅግ ተደስቻለሁ ።

ይህም አጋጣሚ የዚህን የታላቅ ደራሲ ጽሑፍ አንድ በአንድ አረፍተ ነገሮችን ጭምር እንድመለከት ስለገፋፋኝ ታሪኩ ይበልጥ እንዲገባኝና እንድ መረምረው አድርጐኛል ።

ይህ ጽሑፍ በታወቁት የዓለም ቋንቋዎች የተተረጐመና በሥነ ጽሑፍም ትምህርት ላቅ ብለው የሚገኙ ምሁራን ሳያነቡትና ሳያደንቁት የሰርቫንቲስን አስተሳሰብ ከየዘመናቸው ግንዛቤ ጋር ሳያመዛዝኑ የቀሩ ሊኖሩ አይችሉም ፤ ለዚህ ያልታደሉት የሥነ ጽሑፍን ክምር ሳያስተውሉ ያለፉ ብቻ ናቸው ። በተለይ በእስፔን የታላቅነት ዘመንና አውሮፓም በታላቅነቷ ባረጀችበት ዘመን የሰርቫንቲስ ሥራ በመወለዱ ያንን ዘመን ታላቁ ሰርቫንቲስ ቁልጭ አድርጐ አቅርቦታል ።

ሰርቫንቲስም በአስፔይን እውነተኛ ልጅዋ አድርጋ በየኒቨርስቲዎችዋና በተለይም የቀድሞ ግዛቶችዋ የነበሩት የብዙ የላቲን አሜሪካ የሥነ ጽሑፍ ተቋሞች የሰርቫንቲስን ሥራ በመጀመሪያ ደረጃ ያስቀምጡታል ።

በዚህ ለሞን ሃገራችንን የጐበኘው የታላቁ የሞስኮ ባልቮይ ቴያትር የባሌ ቡድንም የዚህን ታላቅ ጸሐፊ ሥራ የሚገልጽ አንድ የባሌ ውዝዋዜ ማቅረቡ የሰርቫንቲስን ሥራ ተደናቂነትና ተወዳጅነት ያረጋግጥልናል ።

የሰው ልጅ ከቀድሞው ዘመን ሰዎች አለመማሩ ነገም ተነገወዲያም ሥራ ምቾቹ ያልተሠሩ እየመሰለው ጀግሬነት ማብዛቱ የብረት ብስኪሌት መሠራቱን ያላወቀ የእንጨት ብስኪሌት እንደሚሠራው የዋህ ዓይነት ነውና ከዶን ኪሾት ብዙ እንማራለን ።

አቶ አስፋው ተፈራ ዶን ኪሾትን ለአማርኛ አንባቢዎች አቅርቦአል ። በዚህ ሳይገታ ክፍል ሁለትንም ቢነካ እጅህ አንለዋለን ።

ዋጋው

ብር 3.25